አዲስ ዘመን
ኢፕድ
እሁድ 84ኛ ዓመት ቁጥር 110 ታኅሣሥ 20 ቀን 2017 ዓ.ም ዋጋ 34.50 ብዕራችን ለኢትዮጵያ ህዳሴ ይተጋል!

# “ሁሉም ወገን አማራጭ ለማይገኝለትና አትራፊ ለሆነው ሠላም እጁን መዘርጋት አለበት”

- አረጋዊ በርሔ (ዶ/ር)

የቀድሞው የሕወሓት ታጋይና የህዳሴው ግድብ ማስተባበሪያ ጽሕፈት ቤት ዋና ዳይሬክተር

**ምሕረት ሞገስ**



አዲስ አበባ፡- የቅርቡም ሆነ የሩቁ ታሪክ እንደሚያሳየው ችግሮችን በጦር መሣሪያ ለመፍታት መነሳት ኪሳራ እንጂ ትርፍ ስለሌለው ሁሉም አማራጭ ለማይገኝለት ሠላም እጁን መዘርጋት እንዳለበት የቀድሞ የሕወሓት ታጋይ እና የህዳሴው ግድብ ማስተባበሪያ ጽሕፈት ቤት ዋና ዳይሬክተር አረጋዊ በርሔ (ዶ/ር) ገለጹ፡፡


የቀድሞ የሕወሓት ታጋይና የህዳሴው ግድብ ማስተባበሪያ ጽሕፈት ቤት ዋና ዳይሬክተር አረጋዊ በርሔ (ዶ/ር) ከአዲስ ዘመን ጋዜጣ ጋር ባደረጉት ቃለ ምልልስ ላይ እንደተናገሩት፤ እስከ አሁን ድረስ ብዙ ጠመንጃ ተመዟል፤ ብዙ ጦርነት ተካሂዷል፡፡ ብዙ ሕዝብ አልቋል፤ ብዙ ንብረት ወድሟል፡፡ በልማት ላይ መዋል ይችል የነበረ ብዙ ሀብት ተቃጥሎ በኖ ቀርቷል። ይህ የሚያሳየው ጦርነት ኪሳራ እንጂ ትርፍ የለውም። በዚህ መነሻነትም ምንም አማራጭ ለማይገኝለትና አትራፊ ለሆነው ሠላም እጁን መዘርጋት አለበት፡፡

ጦርነት መግደል ወይም መሞት ነው፡፡ ይህ ደግሞ ለሀገርም ሆነ ለሕዝብ ኪሳራ ነው፡፡ በጦር መሣሪያ የሚፈታ ችግር ስለሌለ ሠላምን መፈለግ ይሻላል ብለዋል። ይህንን ያሉት ከቅርብ ከራሳቸው ተሞክሮ መሆኑን የተናገሩት አረጋዊ (ዶ/ር) ፤ መሣሪያ ይዞ መዋጋት ያለ እልቂት ያመጣው ምንም ፋይዳ እንደሌለው መላው ኢትዮጵያዊ ማስታወስ እንዳለበት አውስተዋል፡፡

ሌሎች አገሮች ችግር የለባቸውም ማለት አይደለም። እያደጉ ያሉት ችግሮቻቸውን በሠላማዊ መንገድ እየፈቱ ነው፡፡ በኢትዮጵያ ጦር የመዘዙ ኃይሎች ወደ ሠላማዊ መፍትሔ ፍለጋ ቢገቡ፤ ለራሳቸውም ሆነ እንዋጋለታለን ለሚሉት ወገናቸው በአጠቃላይ ለሀገራቸው ጠቃሚ በመሆኑ ሠላምን መምረጥ ይገባል ብለዋል፡፡

ሠላምን ማስከበር የየትኛውም መንግሥት ግዴታ ነው። የኢትዮጵያ መንግሥት ለሕዝቡ ሠላም የማምጣት ሕገ መንግሥታዊ ኃላፊነት አለበት፡፡ ይህንን መሠረት በማድረግ መንግሥት ለሠላም ያልተቆጠበ ጥረት በማድረግ ላይ ይገኛል ያሉት ዋና ዳይሬክተሩ፤ መንግሥት በሰሜን

“ሁሉም ወገን አማራጭ ... ወደ ገጽ 5 ዞሯል



## ከአትሌት ወኪሎች ያልተጠቀመው ፌዴሬሽን

ገጽ 5

## ባለፉት አምስት ወራት ከወጪ ንግድ 2 ነጥብ 7 ቢሊዮን ዶላር ገቢ ተገኘ

ገጽ 5

# በሁሉም ኢንዱስትሪ ፓርኮች ከሚገኙ ሼዶች 90 በመቶ በባለሀብቶች መያዛቸው ተገለጸ

## - በፓርኮቹ ለ100 ሺህ ዜጎች የሥራ ዕድል ተፈጥሯል

**ወርቅነሽ ደምሰው**



አዲስ አበባ፡- ኮርፖሬሽኑ በሚያስተዳድራቸው ኢንዱስትሪ ፓርኮች ከሚገኙ 177 ማምረቻ ሼዶች 90 በመቶ ያህሉ በባለሀብቶች የተያዙ መሆናቸውን የኢንዱስትሪ ፓርኮች ልማት ኮርፖሬሽን አስታውቀዋል። በፓርኮቹ ለ100 ሺህ ዜጎች የሥራ ዕድል መፈጠሩንም ጠቁሟል፡፡

የኮርፖሬሽኑ ኮሙኒኬሽን መምሪያ ኃላፊ አቶ ጳውሎስ በለጠ ለአዲስ ዘመን ጋዜጣ እንደተናገሩት፤ ኮርፖሬሽኑ በሚያስተዳድራቸው 13 ፓርኮች ውስጥ ከሚገኙ ማምረቻ ሼዶች 90 በመቶ በባለሀብቶች ተይዘዋል፡፡

ኮርፖሬሽኑ በሚያስተዳድራቸው በሁሉም ፓርኮች 177 የሚሆኑ የማምረቻ ሼዶች እንዳሉ ገልጸው፤ ከ3ሺህ ሜትር ስኩዌር ጀምሮ እስከ 11ሺ ሜትር ስኬዌር ወይም አንድ ነጥብ አንድ ሄክታር ስፋት ያላቸው ትላልቅ የማምረቻ ሼዶች መኖራቸው አመላክተዋል፡፡

ካሉት ሼዶች 90 በመቶ ያህሉ በባለሀብቶች የተያዙ መሆኑን የሚገልጹት አቶ ጳውሎስ፤ ወደ ቀሪዎቹ 10 በመቶ ሼዶች ለመግባት የተዋዋሉና በሂደት ላይ ያሉ ባለሀብቶች

በሁሉም ኢንዱስትሪ ... ወደ ገጽ 5 ዞሯል












ዜና

SHAGGAR

## ሸገር ከተማን ለነዋሪዎቿ ምቹ ለማድረግ እየተሠራ ነው

**ነፃነት ዓለሙ**

አዲስ አበባ፡- የሸገር ከተማን መሠረተ ልማቶችን እና የአገልግሎት ተቋማትን በማሟላት ለነዋሪዎቿ ምቹ ለማድረግ እየተሠራ መሆኑን ከተማ አስተዳደሩ አስታወቀ።

በሸገር ከተማ ከንቲባ ጽሕፈት ቤት የኢኮኖሚ ዘርፍ አስተባባሪ አቶ ጉዮ ገልገሎ እንደገለጹት፤ ሸገር ከተማን ለነዋሪዎች ምቹ ለማድረግ የመንገድ ሥራ፣ የጤና ተቋማት ግንባታ፣ የትምህርት ቤቶች ግንባታ፣ ዘመናዊ ግብርና ሼዶችንን መሰል የግንባታ ሥራዎች እየተከናወኑ ይገኛል።

ከባለፉት ሁለት ዓመታት ጀምሮ በርካታ የልማት ሥራዎች ሲሠሩ ነበር ያሉት አቶ ጉዮ፤ ከእነዚህ መካከልም በኮዬ ፈጬ እየተገነባ ያለው የሸገር ከተማ ሳይንስና ቴክኖሎጂ ማዕከል አንዱ እንደሆነ ጠቅሰዋል።

ባለፈው በጀት ዓመትም ስምንት ደረጃቸውን የጠበቁ ትምህርት ቤቶች ስለመገንባታቸውም አውስተው፤ ከተማ አስተዳደሩ በተያዘው በጀት ዓመትም ከአምስት ቢሊዮን ብር በላይ በሆነ ወጪ ደረጃቸውን የጠበቁ 100 ትምህርት ቤቶችን በመገንባት ላይ እንዳለ ገልፀዋል።

በሰበታ እና በቡራዩ ክፍለ ከተሞች ሁለት ሆስፒታሎች እየተገነቡ መሆኑን የገለጹት አቶ ጉዮ፤ እነዚህ ሆስፒታሎች ተጠናቀው ሥራ ሲጀምሩ ነዋሪዎች ርቀው ሳይሄዱ የጤና አገልግሎትን በስፋትና በጥራት እንዲያገኙ ያስችላሉ ብለዋል።

ከተማ አስተዳደሩ በሥራ ዕድል ፈጠራ ላይ አጠናክሮ እየሠራ እንደሚገኝም ጠቁመው፤ በተያዘው ሁለተኛ ሩብ ዓመት ከ120 ሺህ በላይ የሥራ ዕድሎች መፈጠራቸውን አስታውሰዋል። እስከ በጀት ዓመቱ መጨረሻ የሥራ ዕድሉን 300ሺህ ለማድረስ ታቅዶ እየተሠራ እንደሚገኝም አስረድተዋል።

ከ475 ሚሊዮን ብር በላይ ለብድር አቅርቦት እንዲሁም ተጨማሪ 10 ሚሊዮን ብር የፋይናንስ ዘርፉን ለመደገፍ በጀት መያዙንም አመልክተዋል።

የምግብ ዋስትናን ከማረጋገጥ አንጻር የከተማ ግብርና መርሐ-ግብሮችን ተግባራዊ በማድረግ ከተማዋን ልምድ የሚቀሰምባት ማዕከል ለማድረግ ጥረት እየተደረገ ስለመሆኑም ተናግረዋል። ለዶሮ እርባታ፣ ለከብት እርባታና ለንብ ማንባት ሥራ የሚያገለግሉ ከአምስት ሺህ በላይ የግብርና ሼዶች መገንባታቸውንም፤ ሁለት ሺህ ሙያተኞች በ65ሺህ ሄክታር መሬት ላይ የጎጆ ኢንዱስትሪ እያለሙ መሆኑንም አቶ ጉዮ አብራርተዋል።

# ከአስከፊው የጎዳና ሕይወት የሚያወጣው ማዕከል

**ነፃነት ዓለሙ**

**ዜና ሐተታ**




ቤተሰቦቻቸው ንብረታቸውን ቀምተው ከቤት በመባረራቸው ምክንያት ወደ ጎዳና እንደወጡ የሚናገሩት አቶ ገብረሚካኤል ገ/ብርሃን፤ ይኖሩበት የነበረው ክፍለ ከተማ ለመቄዶንያ ባደረሰው ጥቆማ መሠረት ወደ ማዕከሉ እንደመጡ ያስታውሳሉ። እኚህ አባት ወደ ማዕከሉ ገብተው መጦር ከጀመሩ ስምንት ዓመት ሆኗቸዋል።

የተለያዩ የጤና እክሎች እንዳሉባቸው የሚገልፁት አቶ ገ/ሚካኤል፤ ማዕከሉ ባይቀበለኝ ኖሮ ጎዳና ወድቄ ተበላሽቼ እቀር ነበር። አሁን ማዕከሉ ግን እያበላ፣ እያጠጣ፣ እያከመና እየተንከባከበ በወጉ ይዞኛል። አሁን ላይ በተለያየ መንገድ ማዕከሉን እያገዙ መሆኑን ይገልፃሉ።

በቅርቡም አረጋውያኑን በመወከል አዲግራት ድረስ በአውሮፕላን የሄዱበትና የማዕከሉን በከተማው የሚገኝ ቅርንጫፍ ጉዳይ ያስፈፀሙበት አጋጣሚ እንደነበር ያስታውሳሉ።

ቅርንጫፉ የተከፈተው አንዲት የውጭ ዜጋ ባበረከተችላቸው ቤት እንደነበርና የእሱን ካርታ ለመጨረስ እየሠሩ ባሉበት ወቅት የከተማ አስተዳደሩም የሕንፃ መሥሪያ ቦታ እንዳበረከተላቸው ይገልፃሉ።

ከዚህ ባሻገር በተለያዩ ጊዜያት አረጋውያኑን በመወከል ከማዕከሉ መሥራች አቶ ቢኒያም በለጠ ጋር በመሆን በማዕከሉ ድጋፍ ዙሪያ እንቅስቃሴ እንደሚያደርጉ የገለፁት አቶ ገ/ሚካኤል፤ በእነዛ አጋጣሚዎች ቤታቸውን ሳይቀር ለማዕከሉ የሰጡ በጎ አድራጊዎች እንደነበሩ ያነሳሉ።

መቄዶንያ ገመናችንን ሸፍኖልናል የሚሉት አቶ ገ/ሚካኤል፤ በመቄዶንያ ማዕከላት ከሚገኙት ከስምንት ሺህ በላይ አረጋውያንና የአዕምሮ ሕሙማን የቅርብ ክትትል የሚሹ ናቸው። ቀለብና ሕክምናም ሌላኛው ወጪ መሆኑን ገልፀው፤ በሀገር ውስጥም ሆነ በውጭ ሀገራት የሚገኙ ኢትዮጵያውያን ድጋፍ አይለየን የሚል ጥሪያቸውን ያስተላልፋሉ።

የማዕከሉ መሥራች የሆኑት አቶ ቢንያም በለጠ በበኩላቸው የጎዳና ኑሮ ከመታረዝና ከመራብ ባሻገር ብዙ መከራዎች እንዳሉት ይገልፃሉ። ተገዶ መደፈርና ሕይወትን ማጣት የመሳሰሉ ጉዳቶችን እንደሚያስከትል ገልጸው፤ በቅርቡም አራት ወይም አምስት ሴቶች ተደፍረው ወደ ማዕከሉ እንዲገቡ የተደረገበት አጋጣሚ እንደነበር ይገልፃሉ።

በተለይ በክረምት ወቅት በብርድ ምክንያት ጎዳና ላይ እንደሚሞቱ አንስተው፤ መቄዶንያ ከጎዳና አንስቶ በሰው ድጋፍና ሸክም ያስገባቸው ሰዎች ከሕመማቸው ድነው ድርጅቱን በተለያየ ሥራ እያገዙ መሆኑን ይጠቁማሉ።

ወገኖቻችንን ከእንዲህ ያሉ ችግሮች መታደግ ከፈጣሪም ትልቅ ዋጋ ስላለው ሁሉም ሰው ባለው አቅም እንዲሳተፍ ጥሪ አቅርበው፤ እገዛችሁ አልጋ ላይ የቀረውን ሰው እንዲሄድ የሚያደርግ፣ ምንም አያደርግም የተባለ ሰው የተለያዩ ሥራዎችን በመሥራት የሚለውጥ ነውና ድጋፋችሁ አይለየን ይላሉ።

ቋሚ ገቢ በሌለበት ሁኔታ የማዕከሉ የቀን ወጪ ሁለት ሚሊዮን ብር መድረሱን የገለጹት አቶ ቢኒያም፤ የግለሰቦችና የተቋማት እገዛ ከመቼውም ጊዜ በላይ እንደሚያስፈልግ ይገልፃሉ። በተለይም የካቲት 1 ቀን 2017 ዓ.ም ለሚጀመረው የማዕከሉ ባለ15 ወለል ሕንፃ ማጠናቀቂያ ገቢ ማሰባሰቢያ መርሐ ግብር ላይ ሁሉም አካላት ተሳታፊ እንዲሆኑ ጥሪ ያቀርባሉ።

የሆስፒታሉን ግንባታ ለማጠናቀቅ አራት ነጥብ ሦስት ቢሊዮን ብር እንደሚያስፈልግ ገልፀው፤ የካቲት 1 በሰይፉ ኦንላይና ኢቢኤስ ሾው ዩትዩብ ቻናል የቀጥታ ስርጭት ገቢ ማሰባሰቢያው እንደሚጀመር ይገልፃሉ። ለዚህ የገቢ ማሰባሰቢያ መርሐ ግብርም አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ከወዲሁ ሁለት ሚሊዮን ብር ገቢ ማድረጉን አስታውሰው፤ ኮተቤ ዩኒቨርሲቲና ሌሎችም ተቋማት በስማቸው ድጋፍ ማድረግ መጀመራቸውን አንስተዋል።

ጠቅላይ ሚኒስትሩን ጨምሮ የተለያዩ የመንግሥት የሥራ ኃላፊዎች እንደሚጎበኟቸው ገልጸው፤ ለዚህም ምስጋናቸውን በመግለፅ አሁንም የግለሰቦች እንዲሁም የተቋማት ድጋፍ እንደሚያስፈልጋቸው አፅንዖት ሰጥተዋል።

መቄዶንያ የአረጋውያንና የአዕምሮ ሕመምተኞች መርጃ ማዕከል ከተጨናነቁ የአዲስ አበባ ጎዳናዎች አንስቶ እስከ 44 ከተሞች ድረስ ጎዳና የወደቁ ወገኖችን በማንሳት ሕይወታቸው መልሶ እንዲያገግም ዕድል እንደሚሰጥ ከማዕከሉ ያገኘነው መረጃ ያሳያል።

በቀጣይም በሌሎች የሀገሪቱ ከተሞች ለመሥራት እና የቅርጫፉን ቁጥር 240 ለማድረስ እንቅስቃሴ መጀመሩን መረጃው ይገልፃል። ባሉት ማዕከላትም አልጋ ቁራኛ የሆኑ እንዲሁም የአዕምሮ ሕሙማንን ጨምሮ ከ8ሺህ በላይ ሰዎችን እየረዳ ይገኛል።

# ባንኩ በአነስተኛ ሥራ ለተሠማሩ ዜጎች ከ13 ቢሊዮን ብር በላይ አበደረ

**ኢያሱ መሰለ**

አዳማ፡- ባንኩ ባለፉት ሁለት ዓመታት በአነስተኛ ሥራ ለተሠማሩ የኅብረተሰብ ክፍሎች ምቹ የብድር አገልግሎት ሥርዓትን በመዘርጋት ከ13 ቢሊዮን ብር በላይ ማበደሩን የኦሮሚያ ኅብረት ሥራ ባንክ ገለጸ።

የኦሮሚያ ኅብረት ሥራ ባንክ በተቋም ደረጃ ለ6ኛ ጊዜ የኅብረት ሥራ ቀንን ሰሞኑን በአዳማ ከተማ ባከበረበት ወቅት የባንኩ ዋና ሥራ አስፈጻሚ አቶ ደርቤ አስፋው በሰጡት ማብራሪያ፤ ባንኩ በዝቅተኛ የኑሮ ደረጃ ላይ ለሚገኙ የኅብረተሰብ ክፍሎች በተዘጋጀው ምቹ የብድር አገልግሎት ሥርዓት ባለፉት ሁለት ዓመታት ከ13 ቢሊዮን ብር በላይ አበድሯል።

አብዛኛዎቹ የብድሩ ተጠቃሚዎች ወጣቶች እንደሆኑና ከእነዚህም ውስጥ የሴቶች ቁጥር 65 በመቶ እንደሆነ ተናግረዋል። የብድር አገልግሎቱን ከክልሉ ውጭ ያሉ የኅብረተሰብ ክፍሎችም ጭምር ሲጠቀሙበት እንደነበር አስታውሰው፤ በአጠቃላይ ከ700 በላይ የሚሆኑ ዜጎች መበደራቸውን አብራርተዋል።

ባንኩ ሲመሠረት የግብርና ሥራን መሠረት አድርጎ እንደነበር ጠቅሰው፤ በአሁኑ ጊዜ የፋይናንስ እጥረት ላለባቸውና በተለያየ ሥራ ለተሠማሩ ጥቃቅን፣ አነስተኛና



**አቶ ደርቤ አስፋው**

መካከለኛ ኢንተርፕራይዞች የብድር አገልግሎት እየሰጠ ነው ብለዋል። የምቹ ብድር አገልግሎት ሥርዓት ተበዳሪዎች ቴክኖሎጂን በመጠቀም ባሉበት ቦታ ሆነው የብድር አገልግሎት እንዲያገኙ የሚያስችል መተግበሪያ ስለመሆኑም ጠቅሰዋል።

የኤሌክትሪክ መሠረተ ልማት በሌለባቸው ገጠራማ አካባቢዎች አገልግሎቱን ተደራሽ ለማድረግም በፀሐይ ብርሃን ኃይል በማመንጨት ኅብረተሰቡ ኢንተርኔት አግኝቶ የአገልግሎቱ ተጠቃሚ እንዲሆን ስለመደረጉም ጠቅሰዋል። በዚህም 70 የሚሆኑ የኢንተርኔት አገልግሎት መስጫ ጣቢያዎች ተዘጋጅተው ጥቅም እየሰጡ መሆኑን አስረድተዋል።

ምቹ የብድር አገልግሎት፤ አርሶ አደሩ የራሱን የባንክ ደብተር (አካውንት) እንዲያወጣና ከባንክ ጋር እንዲለማመድ ያደረገ፤ የፋይናንስ እጥረት ያለባቸው የኅብረተሰብ ክፍሎች ወደ ሥራ እንዲገቡ ያስቻለ፤ የሥራ ፈቃድ የሌላቸው ዜጎች በብድር ሥራ ጀምረው ከተደራጁ በኋላ ፈቃድ አውጥተው እንዲሠሩ ያደረገ መሆኑን አቶ ደርቤ ገልጸዋል።

በኦሮሚያ ኅብረት ሥራ ባንክ የእርሻ እና የማኅበራት ክፍል ምክትል ፕሬዘዳንት አቶ ዮሐንስ ሀምቢሳ በበኩላቸው ፤ የኦሮሚያ ኅብረት ሥራ ባንክ የዛሬ 20 ዓመት የተቋቋመ እንደሆነ እና 60 በመቶ የሚሆነው የባንኩ ድርሻ የማኅበራት እና የአርሶ አደሮች ሀብት እንደሆነ ተናግረዋል። ማኅበራቱ ቀደም ሲል ከነበሩበት ደረጃ አሁን ትልቅ ሃብት ወደ ማፍራት እንደተሸጋገሩም ገልጸዋል።

የግብርናው ዘርፍ የፋይናንስ ችግር አለበት ያሉት አቶ ዮሐንስ፤ ለዚህም አንዱ ችግር ባንኮች ለዘርፉ ብድር የመስጠት ፍላጎት ማጣት እንደሆነ ተናግረዋል። የግብርና ሥራ ለተፈጥሮ አደጋ የተጋለጠ መሆኑ እና አርሶ አደሮች አነስተኛ መሬት ይዘውና ተበታትነው ያሉ መሆናቸው ባንኮች ባላቸው የፋይናንስ አሠራር መሠረት እንዳያስተናግዷቸው ምክንያት ነበሩ ብለዋል።

የኦሮሚያ ኅብረት ሥራ ባንክ ትኩረቱን አርሶ አደሩ ላይ አድርጎ ምቹ የብድር አገልግሎትን በመዘርጋት በነባሩ የብድር አገልግሎት መበደር ለማይችሉ ዜጎች አገልግሎቱን እንዲያገኙ ዕድል መፍጠሩን ተናግረዋል።

በዚህም የሙከራ ጊዜውን ጨምሮ በሁለት ዓመት ውስጥ በርካቶች ወደ ሥራ እንዲገቡ ማስቻሉን አስረድተዋል። የምቹ ብድር አገልግሎት ተጠቃሚዎች ተንቀሳቃሽ ስልካቸውን (ሞባይላቸውን) በመጠቀም ብቻ፣ ምን አይነት ነገር ሳያሲዙ ብድር የሚያገኙበት አሠራር እንደሆነም አቶ ዮሐንስ አስረድተዋል።

በመርሐ-ግብሩ የኦሮሚያ ክልላዊ መንግሥት ፕሬዚዳንት ጽሕፈት ቤት ኃላፊ አብዱላዚዝ ዳውድ (ዶ/ር)፣ የኢትዮጵያ ኅብረት ሥራ ኮሚሽን ኮሚሽነር አምባሳደር ሽፈራሁ ሽጉጤ፣ የፌደራልና የክልል ሥራ ኃላፊዎች እና ጥሪ የተደረገላቸው እንግዶች ተገኝተዋል።

# ርዕሰ አንቀፅ

## አዲሱ አመራር የአትሌቲክሱን ችግሮች ለመቅረፍ ሊተጋ ይገባል!

የኢትዮጵያ አትሌቲክስ በየጊዜው የሚገጥመውን አስተዳደራዊ ፈተና በተገቢው መንገድ ባለመመራቱ በስፖርቱ ሁለንተናዊ ዕድገት ላይ እንቅፋቶች ሲፈጠሩ ቆይተዋል። ኢትዮጵያ በዓለም ታላላቅ መድረኮች ዘመን ተሻጋሪ ከዋክብት አትሌቶች መፍለቂያ ብትሆንም ስፖርቱ ወደዘመናዊው የአስተዳደር ደረጃ መሻገር ያልቻለውም በዚሁ ምክንያት ነው። በዚህ የተነሳ ኢትዮጵያ በአትሌቲክስ ያላትን ትልቅ ስም የሚመጥን ፌዴሬሽንና ተቋሙን ወደፊት የሚያራምዱ የአመራር ብቃቱ ያላቸው ሰዎች ወደ ኃላፊነት እንዲመጡም የስፖርት ቤተሰቡ ሲጠይቅ ኖሯል። ይሁን እንጂ ስፖርቱን ለመምራት በተለያየ ጊዜ ዕድሉን ያገኙ የአትሌቲክሱን ችግሮች ሳይፈቱ የሥራ ዘመናቸውን ጨርሰው ከመሰናበት የዘለለ ታሪክ ማኖር አልቻሉም።

ፌዴሬሽኑ በቅርቡ ባደረገው ጠቅላላ ጉባዔ ባለፉት ዓመታት ስፖርቱን ሲመሩ የቆዩ ግለሰቦች ተሰናብተው በአዳዲስ አመራሮች ተተክተው በይፋ ሥራ ጀምረዋል። እነዚህ አዳዲስ አመራሮች ወደ ፌዴሬሽኑ ኃላፊነት ሲመጡ የመጀመሪያ ቢሆንም በስፖርቱ ውስጥ ያለፉ ወይም ለስፖርቱ ቅርብ መሆናቸውን ተከትሎ የሚስተዋሉ ችግሮችን ይቀርፋሉ የሚል ተስፋ ተጥሎባቸዋል። ያም ሆኖ ትልቅ የቤት ሥራ እንደሚጠብቃቸው ግልፅ ነው።

በአትሌቲክስ ፌዴሬሽኑ አመራር ዙሪያ ባለፉት ጥቂት ዓመታት ውስጥ የታዩት የአስተዳደር ግድፈቶች ከምንጊዜውም የበለጠ በጎሉበት ወቅት ኃላፊነቱን መረከባቸው ችግሮችን በአጭር ጊዜ ለመፍታት ቀላል ላይሆንላቸው ይችላል፡፡ ስፖርቱን ለመምራት ያገኙትን ዕድል በአግባቡ ተጠቅመውና ተግባብተው መሥራት ከቻሉ ግን ጊዜውና አቅሙ አላቸው። ለዚህም የስፖርቱን ችግሮች ነቅሰው በማውጣት ከወዲሁ በትኩረትና በትጋት መሥራት ይጠበቅባቸዋል።

በቀደሙት ዓመታት በፌዴሬሽኑ አመራር ዙሪያ ደካማ የውሳኔ አሰጣጦች፣ አቅዶ የመተግበር ችግር እና ግልፅ ያለመሆን፣ እንዲሁም አትሌቶቻችን እና አጠቃላይ ስፖርቱን የሚመለከቱ ችግሮችን አግባብ ባለው መንገድ መፍታት ያለመቻል ችግሮች በተደጋጋሚ ታይተዋል። እነዚህ ከአስተዳደር ብቃት እና ቁርጠኝነት ማነስ ጋር የተያያዙ ችግሮች የፈጠሯቸው ክፍተቶችም የኢትዮጵያን አትሌቲክስ እድገት ከማደናቀፍ በዘለለ ከጊዜ ወደጊዜ በፌዴሬሽኑ፣ በአትሌቶች፣ በአሠልጣኞች እና በስፖርቱ እውነተኛ ደጋፊዎች ዘንድ መተማመን እንዲጠፋ እያደረጉ መጥተዋል። አዲሱ አመራር እነዚህን ችግሮች ለመቅረፍ ቅድሚያ ሰጥቶ መሥራት ይኖርበታል።

በፓሪስ ኦሊምፒክ ዝግጅት እና በውድድሩ ወቅት እንዲሁም ከዚያም በፊት በነበሩት ጊዜያት በአትሌቲክስ ፌዴሬሽኑ አመራር ዙሪያ አስተዳደራዊ ድክመቶች በስፋት ተስተውለዋል፡፡ ከድክመቶቹ አብዛኞቹ በቀደሙት የአትሌቲክስ ፌዴሬሽን መሪዎች ግዜም የነበሩ እና ባሉበት ሲንከባለሉ እዚህ የደረሱ ናቸው፡፡ ከዚህ በኋላ ግን መቀጠል የለባቸውምና አዲሱ አመራር ሊቀርፋቸው ግድ ይላል።

የሀገር ውስጥ ውድድሮች የጥራት ደረጃ፣ ከጊዜ ወደጊዜ እየተባባሰ የመጣው የልምምድ እና የውድድር ማዘውተሪያ ስፍራዎች እጥረት፣ ዓለም አቀፍ የውድድር መድረኮች በተቃረቡ ቁጥር ከአትሌቶች ምርጫ ጋር በተያያዘ የሚታየው ውዝግብ፣ የአትሌቲክስ ስፖርትን ለሚያስተዳድር ተቋም የጀርባ አጥንት ከሚባሉ ነገሮች መካከል አንዱ የሆነው የመረጃ ቋት አደረጃጀት ላይ የሚታዩ ክፍተቶችን መድፈንም ከአዲሱ አመራር የሚጠበቁ ቁልፍ ተግባራት ናቸው።

አትሌቲክሱን ለመምራት የሚወጡ የመተዳደሪያ ሕግ እና ደንቦችን በመከለስ ለስፖርቱ ባለድርሻ አካላት እና ለሕዝብ በይፋ ማስተዋወቅ እንዲሁም በአግባቡ ተግባራዊ እንዲሆኑ መከታተል ያስፈልጋል። ለዚህም በስፖርቱ ዙሪያ ትኩረት ሊሰጣቸው የሚገባቸውን ጉዳዮች ለይቶ የአጭር እና የረጅም ጊዜ ዕቅድ አውጥቶ ለመተግበር መንቀሳቀስ ይጠይቃል።

ውጤታማ ሥራን ለማከናወን የአጭር ጊዜ እና የረዥም ጊዜ ስትራቴጂክ ዕቅዶችን ከማዘጋጀት በተጨማሪ፣ ዕቅዶች ለማዘጋጀት የአትሌቲክስ ፌዴሬሽኑን ወቅታዊ ሁኔታ በጥልቀት በመፈተሽ ቁልፍ ጥንካሬዎችን፣ ድክመቶችን፣ ዕድሎችን እና ስጋቶችን መለየት አለበት። የአጭር ጊዜ ዕቅዱ ፈጣን ማሻሻያዎችና የቅድሚያ ትኩረት በሚያስፈልጋቸው በጊዜያዊ የልምምድ እና ውድድር ማዘውተሪያ ችግሮች መፍቻ፣ መቀየር ያለባቸው የአሠራር ሂደቶች፣ የአሠልጣኝነት ሥልጠና መርሐ ግብሮችን ማሳደግ፣ የገቢ ምንጮችን ማጠናከር፣ በቅርቡ ለሚካሄዱ ዓለም አቀፍ ውድድሮች የሚያስፈልጉ ቅድመ ዝግጅቶች እና ሌሎችም መካተት የሚያስፈልጋቸው ጉዳዮች ላይ ሊያተኩር ይገባል!


# አዲስ ዘመን

ኢፕድ

ግንቦት 30 ቀን 1933 ዓ.ም ተቋቋመ

**የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ዋና ስራ አስፈጻሚ**
ስልክ ቁጥር - 011-126-42-22
ኢሜል ፡- epa@press.et

**ዋና አዘጋጅ**
አንተነህ ኃ/ብርሃን ወ/መድህን

**አድራሻ**
ንፋስ ስልክ ላፍቶ ክ/ከ
ወረዳ 06
የቤት ቁጥር 319
ኢሜይል - anteneh.hailebirhan@press.et
ስልክ ቁጥር - 011-1-26-42-40

**የገበያ ልማትና ፕሮሞሽን ዘርፍ**
ኢሜይል - etpresspromotion@gmail.com
ስልክ - 011-126-43-41
ፋክስ - 011-811-13-15
የዝግጅት ክፍል ፋክስ - 251-011-1-56-98-62

**የአዲስ ዘመን ማኔጂንግ ኤዲተር**
ወንድወሰን ሽመልስ ታደሰ
ስልክ፡- 011 126 4200
Email:- wendweson.shimelis@press.et
wendwesonshimelis@gmail.com

**የዜና ማዕከል ዋና አዘጋጅ**
ወርቁ ማሩ
Email:- workumaru2@gmail.com

**የአዲስ ዘመን ምክትል ዋና አዘጋጆች**
- ኃይሉ ሣህለድንግል
- እስማኤል አረቦ
- ቦጋለ አበበ
- አልማዝ አያሌው

**የማስታወቂያ መቀበያ ክፍል**
ስልክ ቁጥር - 011-156-98-73
ፋክስ - 011-126-58-12
ቴሌግራም - 097- 608-47-07 - Press

**የማስታወቂያ ሽያጭ ማስተባበሪያ**
ስልክ - 011-1-26-43-39

**ማከፋፈያ** ፡- ስልክ ቁጥር - 011-157-02-70


# ነፃ ሃሳብ

ይህ አምድ በተለያዩ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጉዳዮች ዙሪያ ዜጎች ነፃ ሀሳባቸውን የሚሰጡበት ነው፡፡ በዓምዱ ላይ የሚወጡ ጽሁፎች የዝግጅት ክፍሉን አቋም አያመለክቱም፡፡

## ቻው የፕላስቲክ ከረጢት

ክብረ መንግሥት

የዓለም መንግሥታት ጠንከር ያለ እርምጃ ለመውሰድ ቁርጠኛ የማይሆኑ ከሆነ 11ነጥብ3 ቢሊዮን ቶን የሚመዝን ፕላስቲክ እአአ በ2040 በምድር እና በውሃ አካላት ላይ ሊገኝ ይችላል ሲል አንድ ጥናት አመላክቷል፡፡

ጥናቱ ፕላስቲክ ጥቅም ላይ የሚውልበት መጠን እና አወጋገዱ በተለያዩ የዓለማችን ክፍሎች የተለያየ መሆኑ መረጃዎች በቀላሉ እንዳይገኙ አድርጓል ይላል። የፕላስቲክ ምርቶች በውሃ አካላትና እንስሳት ላይ እያደረሰ ያለው ጉዳት በቀላሉ የሚታይ አይደለም።

እስከ 700 አይነት የባሕር እንስሳት እና ንጹሕ ውሃ ላይ የሚኖሩ ከ50 በላይ የዓሣ ዝርያዎች በአንድም ሆነ በሌላ መንገድ ፕላስቲክ ተመግበዋል ወይም በሰውነታቸው ውስጥ ይገኛል።

በተጨማሪም የፕላስቲክ ብክለት የሰዎችን ሕይወት እጅጉን ከባድ እያደረገው መጥቷል። በቀላሉ ማስተዋል የሚቻሉ ብዙ ጉዳቶችም አሉት። ለምሳሌ የውሃ መውረጃዎች መድፈን፣ ለተለያዩ ባክቴሪያዎችና ጎጂ ተህዋሲያን ምቹ የመራቢያ ቦታ መሆን፣ መሬት ውስጥ ውሃ እንዳይገባ መከልከል፤ ተክሎች እንዳያድጉ ማድረግ፤ ለረጅም ዘመን አለመበስበስና ወደ አፈርነት አለመለወጥ እና መሰል ተዘርዝረው የማያልቁ ጉዳቶች አሉት፡፡

ይህ ደግሞ በሚያደርሰው ጫና ዓለማችን በየዓመቱ እስከ 13 ቢሊዮን ዶላር እንድታጣ አድርጓታል፡፡ ስለሆነም ፕላስቲኮችን መልሶ ከመጠቀም ይልቅ የሚመረተውን ፕላስቲክ መቀነሱ አዋጭነት አለው ሲሉም ተመራማሪዎቹ ያሳስባሉ፡፡

ከዚህ አንጻርም መላ ማበጀት ጊዜ የሚሰጠው ጉዳይ አይሆንም፡፡ ኢትዮጵያም ብትዘገይም በቅርቡ ረቂቅ አዋጅ አውጥታ ለሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት እንዲፀድቅ አቅርባለች፡፡

የፕላስቲክ ጉዳይ እንደ ሀገር የተለያዩ መመሪያዎች ቀድመው የወጡበትና ሲሠራበት የቆየ ቢሆነው በሚፈለገው ልክ ለውጥ አልመጣም። እንዲያውም ይባስ ብሎ የሚመረቱ ፕላስቲክ ከረጢቶች ለአንድ ጊዜ እንኳን እቃ መያዣነት የማይሆኑ ጥንካሬ የሌላቸው። በማንኛውም ቦታ ላይ ምንም አይነት ሸቀጥ ለሚገዛ ሰው በገፍ የሚሰጡም ናቸው ይሄ መሆኑ ደግሞ አካባቢን በመበከል ለዓይን እይታም ጭምር አፀያፊ ሆኖ ቆይቷል።

> **እንዲያውም ይባስ ብሎ የሚመረቱ ፕላስቲክ ከረጢቶች ለአንድ ጊዜ እንኳን እቃ መያዣነት የማይሆኑ ጥንካሬ የሌላቸው። በማንኛውም ቦታ ላይ ምንም አይነት ሸቀጥ ለሚገዛ ሰው በገፍ የሚሰጡም ናቸው ይሄ መሆኑ ደግሞ አካባቢን በመበከል ለዓይን እይታም ጭምር አፀያፊ ሆኖ ቆይቷል**

በመሆኑም የፕላስቲክ ምርቶች አጠቃቀምና አወጋገድ ብዙ ችግር ያለበት በመሆኑና በጥብቅ መሻሻል ያለባቸው ጉዳዮች በመኖራቸው በአዲስ መልክ ረቂቅ አዋጁ እንዲዘጋጅ ተደርጓል፡፡ ረቂቅ አዋጅም ለሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት በቀረበበትም ጊዜ አስፈላጊነቱ በስፋት ተብራርቷል፡፡

ረቂቅ አዋጁ በርከት ያሉ ሀሳቦችን የያዘ ነው። በኢትዮጵያ የፕላስቲክ ከረጢት መጠቀምን፣ ማምረት እና ወደ ሀገር ውስጥ ማስገባት በገንዘብ እና በእስራት የሚያስቀጣ ድንጋጌ የተካተተበት ነው፡፡

ረቂቅ አዋጁ የተለያዩ መሠረታዊ ድንጋጌዎችን የያዘ ሲሆን፤ አንዱን የፕላስቲክ ከረጢት የተጠቀመ ወይም ለመጠቀም ይዞ የተገኘ ማንኛውም ሰው ከአምስት እስከ አስር ሺህ ብር ገንዘብ ይቀጣል የሚለው ነው። በተመሳሳይ የፕላስቲክ ከረጢት ማምረት፣ ወደ ሀገር ውስጥ ማስገባት፣ ለገበያ ማቅረብ፣ መሸጥ ወይም ለንግድ ዓላማ ማከማቸት ከሃምሳ እስከ መቶ ሺህ ብር እንደሚያስቀጣ ያብራራል።

ከዚህ በተጨማሪም ከአምስት ዓመት በማይበልጥ ጽኑ እስራት እንደሚያስቀጣም በረቂቁ ላይ ሰፍሯል፡፡ ይህ ድርጊት ከግለሰቦች አልፎ ሕጋዊ ሰውነት ባላቸው ድርጅቶች የሚፈጸም ከሆነ ቅጣቱ ይጠነክራል፡፡ ምን ያህል ነው ከተባለም እንደ ረቂቅ አዋጁ ከሆነ ሦስት እጥፍ ይጨምራል ተብሏል፡፡

ይህ ረቂቅ አዋጅ "የደረቅ ቆሻሻ አያያዝ እና አወጋገድ አዋጅ" ሲሆን፤ ስድስት ክፍሎች እና 28 አንቀጾች ያሉት ነው፡፡ የደረቅ ቆሻሻ አሰባሰብ እና አወጋገድን የተመለከቱ ድንጋጌዎችንም ይዟል። ከረቂቅ አዋጁ ሦስት መርሆዎች መካከል አንደኛው "የበከለን ማስከፈል" የሚለው ነው።

ይህ ደግሞ ቆሻሻን ከምንጩ እንዲቀንስ ያደርጋል፡፡ መልሶ ለመጠቀምም ያስችላል፡፡ ከዚያም ባሻገር መልሶ ዑደት ማድረግን ያስለምዳል፡፡ ለዚህ ግን የኅብረተሰብ ተሳትፎ የግድ ይላልና በረቂቅ አዋጁ አንዱ መርሕ ተደርጎ ተካቷል፡፡

አዋጁ ከ18 ዓመታት በፊት የወጣውን የደረቅ ቆሻሻ አያያዝ አዋጅ የሚሽር እንደሆነም በማሳያነት የሚጠቀሱ ሀሳቦችን ይዟል፡፡ አንዱ በአዲሱ ረቂቅ የተሻረው አዋጅ "በቀላሉ በስብሶ ወደ አፈር የሚደባለቅ መሆን አለመሆኑን የሚያሳይ ምልክት ያልተደረገበትን የፕላስቲክ ከረጢት ለገበያ ማቅረብ" ክልክል ነው የሚለው ነው፡፡

በሌላ በኩል አዲሱ ረቂቅ አዋጅ፤ ለአንድ ጊዜ ብቻ ጥቅም ላይ የሚውል ፕላስቲክ ማምረት፣ ለገበያ ማቅረብ፣ ወደ ሀገር ውስጥ ማስገባት፣ መሸጥ፣ ማከማቸት ወይም መጠቀምን ይከለክላል፡፡ ነገር ግን ይህ ድንጋጌ አዋጁ ከመውጣቱ በፊት በተመረተ፣ ወደ ሀገር ውስጥ በገባ፣ ለመግባት በሂደት ላይ ባለ ፕላስቲክ ላይ ተፈጻሚ እንደማይሆን በአዋጁ ተካቷል፡፡ ይሁን እንጂ ይህ ልዩ ሁኔታ ተፈጻሚ የሚሆነው ይህ አዋጅ ሥራ ላይ ከዋለበት ጊዜ ጀምሮ ለስድስት ወር ብቻ እንደሆነም ተቀምጧል፡፡

ማንኛውም ችግር ከተፈጠረ፤ ከአዋጁ ውጪ የሚወጣ ሰው አለያም ድርጅት ከተገኘ ቅጣቱን ወይም እርምጃውን የሚወስደው አካል ማን እንደሆነ በረቂቅ አዋጁ የተቀመጠ ሲሆን፤ ይህም የአካባቢ ጥበቃ ባለሥልጣን ነው፡፡ በዚህም አንድ ጊዜ ብቻ ጥቅም ላይ የሚውል ፕላስቲክን የተመለከቱ በአዋጁ ድንጋጌዎች መሠረት አፈጻጸሙን ይቆጣጠራል፡፡

ጥሰት ሲያጋጥምም ተገቢውን የእርምት እርምጃ የሚወስድ ይሆናል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ረቂቅ አዋጁ ባለሥልጣን መሥሪያ ቤቱ አንድ ጊዜ ብቻ ጥቅም ላይ የሚውሉ ፕላስቲኮችን ግለሰቦች ወይም ድርጅቶች እንዲመረቱ፣ ወደ ሀገር ውስጥ እንዲገቡ ወይም ጥቅም ላይ እንዲውሉ በመመሪያ ሊወስን እንደሚችልም በረቂቅ አዋጁ ሥልጣን ተሰጥቶታል፡፡

ይሁን እንጂ ባለሥልጣኑ ይህን ውሳኔ ማስተላለፍ የሚችለው በዘፈቀደ አይደለም፡፡ ፕላስቲክ ማሸጊያው በቀላሉ በሌላ ምርት የማይተካ መሆኑ እና ፕላስቲኩ ለዚህ ዓላማ ብቻ የሚውል መሆኑ ሲረጋገጥ ነው፡፡

ይህ ጉዳይ ብዙዎች ያልተመለከቱት ነው፡፡ አደጋው ግን ከጊዜ ወደጊዜ እየጨመረ ሄዷል፡፡ እናም መጀመሪያ ስለ እራሳችን በማሰብ ልንጠነቀቅ ይገባል፡፡ በተለይ ለልጆቻችን የሚተርፈው ችግር በቀላሉ የምናልፈው አይሆንም፡፡ በተለያየ መልኩ ጤናቸው ላይ ጉዳት ያደርሳል፡፡ እኛም ቢሆን ከዚህ ችግር የምናመልጥበት ሁኔታ እንብዛም ነው፡፡ እናም ነገ በሳንባ በሽታ፤ በደም ካንሰርና በሌሎች አሰቃቂ በሽታዎች ተይዘን ከመጮኻችን በፊት ዛሬ ላይ ጥንቃቄ ማድረጉ፤ የተባሉትን መፈጸሙ አዋጭነት አለው፡፡

# ከአትሌት ወኪሎች ያልተጠቀመው ፌዴሬሽን

ብርሃን ፈይሳ

**ዜና ትንታኔ**

ከቅርብ ዓመታት ወዲህ ኢትዮጵያውያን አትሌቶች በማናጀሮችና ወኪሎች ስር ሆነው የተለያዩ የግል ውድድሮችን ማድረጋቸው የተለመደ ነው። ይህ አሠራር በሌላው ዓለምም የተለመደ ሲሆን፤ እንደ ኬንያ ያሉ ሀገራትም ናይኪ እና ግሎባል ስፖርትስ ኮሙዩኒኬሽን የተባሉ ትልልቅ ማኔጅመንቶች ካምፕ በመገንባት አስፈላጊው ነገር ሁሉ ተሟልቶላቸው ለውድድሮች ይዘጋጃሉ። አትሌቶቹ በግል ውድድሮቻቸው ከሚያገኙት ውጤት በገንዘብና በሌሎች የሀገራቸው ፌዴሬሽን ተጠቃሚ ነው። በርካታ ኢትዮጵያውያን አትሌቶችም በእነዚህና በሌሎች ማኔጅመንቶች ታቅፈው ውጤታማ ቢሆኑም የኢትዮጵያ አትሌቲክስ ፌዴሬሽን በሚገባው ልክ ተጠቃሚ አለመሆኑን ሲገልፅ ይስተዋላል።

የፌዴሬሽኑ የአትሌቲክስ ፋሲሊቲ ማኅበራት አገልግሎት የሥራ ሂደት መሪ አቶ አሰፋ በቀለ፤ ከኢትዮጵያውያን አትሌቶች ጋር የሚሠሩ በተለምዶ ማናጀር የሚባሉ የአትሌት ተወካዮች እንደየጊዜው ቁጥራቸው ቢለያይም 20 እንደሚደርሱ ይናገራሉ። እንደ አቶ አሰፋ ገለፃ፣ አብዛኞቹ ማናጀሮች የውጭ ሀገር ዜጎች ሲሆኑ ኢትዮጵያውያኑ በቁጥር እጅግ ጥቂት ናቸው። እነዚህ የአትሌት ወኪሎች ከዓለም አትሌቲክስ ዕውቅና ያላቸውና በኢትዮጵያ ከፌዴሬሽኑ ጋር ውል አስረው ሲሠሩም ቆይተዋል፡፡ ከዚህ ቀደምም በፌዴሬሽኑ ተገኝተው ውል (ዕውቅና) የሚያድሱም ሲሆን፤ በዚህም ፌዴሬሽኑ በዓመት እስከ አምስት ሚሊዮን ብር ገቢ ሲያገኝ ቆይቷል፡፡

ይሁን እንጂ የዓለም አትሌቲክስ ባለፈው የፈረንጆቹ ዓመት ባካሄደው ጠቅላላ ጉባኤ የትኛውም ማናጀር መሥራት ያለበት ከየሀገራቱ ፌዴሬሽኖች ጋር ሳይሆን ከዓለም አቀፋ ተቋም ጋር መሆን እንዳለበት ማሳወቁን ተከትሎ ከኢትዮጵያ አትሌቲክስ ፌዴሬሽን ጋር የሚሠሩ ማናጀሮች ያላቸው ውል ተቋርጧል። ያም ሆኖ የትኛውም አትሌት ለውድድር የውጭ ሀገር ጉዞ በሚያደርግበት ወቅት አስፈላጊውን ሁሉ አሟልቶ ከተገኘ ፌዴሬሽኑ ድጋፍ ማድረጉን አላቋረጠም፡፡

ይህም ያለምንም ክፍያ አትሌቶችን ለመርዳት ሲባል የሚደረግ ቢሆንም ፌዴሬሽኑ ከአትሌት ወኪሎች ምንም አይነት ጥቅም እያገኘ አይደለም፡፡ ማግኘት የሚገባቸው ጥቅሞች መኖር እንዳለባቸው ግን ያምናል፡፡ ጥያቄው እንዴት? ወይም በምን መልኩ የሚለው ነው፡፡

የኢትዮጵያ አትሌቶች ማኅበር ፌዴሬሽኑ ከአትሌት ወኪሎች የሚያገኘው ክፍያ ቢቀርም አትሌቶች ከወኪሎች ጋር በመሥራታቸው ብቻ ተጠቃሚ መሆኑን ያምናል፡፡ የማኅበሩ ፕሬዚዳንት አትሌት የማነ ፀጋይ እንደሚናገረው፤ ማናጀሮች ተሰጥዖ ያላቸውን አትሌቶች አፈላልገው በመመልመል፣ ቤት ተከራይተው፣ አስፈላጊውን ሁሉ በማሟላትና ውድድር አፈላልገው በማሳተፍ ገቢ ያገኛሉ። ይህ የስፖርት ቢዝነስ አንዱ አካል ሲሆን፤ በየትኛውም ዓለም የተለመደ የወቅቱ አሠራር ነው፡፡ በዚህ ብቻ ፌዴሬሽኑን እየጠቀመ መሆኑን ከመረዳት ይልቅ ከማናጀሮች ክፍያና ሌሎች ጥቅሞችን መጠበቁ ተገቢ አይደለም፡፡

አትሌት የማነ ይህንን ሲያብራራም፣ የአትሌቲክስ ብሔራዊ ቡድን እና ጠንካራ ክለቦች በሌሉበት ሁኔታ የኢትዮጵያውያን አትሌቶች ውጤታማነት ማናጀሮች በሚያመቻቹት ውድድሮችና ሥልጠናዎች ምክንያት እንደቆየ መገንዘብ ያስፈልጋል ይላል፡፡

ግዙፉ የስፖርት ትጥቅ አምራች ናይኪ በራሱ ማኔጅመንት ስር የተለያዩ አትሌቶችን አቅፎ ይሠራል፡፡ የናይኪ ኢንተርናሽናል ተወካይ ከሆኑት አንዱ ዮናስ አያና አትሌቲክስ ፌዴሬሽን ከማናጀሮች የሚያገኘው ጥቅም መኖር አለበት ብሎ ያምናል፡፡ የኢትዮጵያ አትሌቲክስ ፌዴሬሽን በዚህ ረገድ እየተጠቀመ አለመሆኑ የፈጠረበት ቁጭትም ለአዲስ ሥራ ያነሳሳው ኢትዮጵያዊ ባለሙያ ነው፡፡ የናይኪ ተወካይ በመሆን ከኢትዮጵያ አትሌቲክስ ፌዴሬሽን ጋር ለዓመታት ከሠሩ ባለሙያዎች መካከል ብቸኛው ኢትዮጵያዊም ሲሆን፤ በርካታ ወጣትና ስኬታማ አትሌቶችንም ማፍራት ችሏል፡፡ ዮናስ ከወከለው የናይኪ ማናጅመንት ስር ሆነው የሚሠሩ አምስት ኢትዮጵያውያን ማናጀሮች አሉ፡፡ ከኢትዮጵያ አትሌቶች ጋር የሚሠሩ ማናጀሮች ግን የውጭ ሀገር ዜጎች መሆናቸውን ይናገራል።

እንደ ዮናስ ገለፃ፣ ኬንያ ውስጥ የሚሠሩ ማናጀሮች በሀገሪቱ ከሰባት ያላነሱ የአትሌቲክስ ካምፖችን ገንብተው አትሌቶችን በመመልመልና በማዘጋጀት በውድድሮች ላይ ያሳትፋሉ፡፡ በአንጻሩ ከ20 ዓመታት በላይ በሠሩባት ኢትዮጵያ ለስፖርቱ አንድም አስተዋፅዖ ሲያደርጉ አይታይም፡፡ አትሌቶችንም አይደግፉም፡፡ እንዲያውም ውጤታማ የሆኑ አትሌቶችን ከየስፍራው ተሻምተው በመያዝ ነው ውድድሮች ላይ የሚያሳትፉት፡፡ ይህ ሁኔታ በፈጠረበት ቁጭትም ማራቶንን ከ2 ሰዓት በታች ማጠናቀቅ የሚችሉ አትሌቶች ማፍራትን ዓላማው ያደረገና የራሱ የአትሌቲክስ ካምፕ ያለው ፕሮጀክት በቅርቡ ኢትዮጵያ ውስጥ ከፍቶ አትሌቶችን በመመልመል ለሌሎች አርዓያ የሚሆን እርምጃ ወስዷል፡፡ ሌሎችም ማናጀሮች በሀገሪቱ አትሌቶች እስከተጠቀሙ ድረስ ፌዴሬሽኑን የሚጠቅሙበት መንገድ ሊኖር ይገባል የሚል አቋም አለው፡፡

ከማናጀሮች መጠቀም አለብኝ የሚለው የኢትዮጵያ አትሌቲክስ ፌዴሬሽንም በዮናስ ሀሳብ ይስማማል። ማናጀሮች በሌሎች ሀገራት የማሠልጠኛ ማዕከላትን የሚገነቡ ቢሆንም በኢትዮጵያ ግን በተግባር የታየ ነገር አለመኖሩን ነው ፌዴሬሽኑ የሚጠቁመው፡፡ በዚህም ምክንያት የአትሌት ባለቤት ከሆኑት ክለቦች ከፍተኛ ቅሬታ በተደጋጋሚ እንደሚቀርብም አቶ አሰፋ ያስረዳሉ። ይህንን ሲያብራሩም አትሌቶችን የሚያሳድጉት፣ ትጥቅ የሚሰጡትና ደመወዝ የሚከፍሉት ክለቦች ሆነው ሳሉ ማናጀሮች ከስር ጀምረው ታዳጊዎችን ከማፍራት ይልቅ ብቁና ዝግጁ የሆኑ አትሌቶችን ከክለቦች በመንጠቅ ያልተገባ ጥቅም እያገኙባቸው ይገኛሉ ባይ ናቸው፡፡

በተወዳዳሪነት ዘመኑ በማናጀሮች ስር ሲሠራ የቆየው አትሌት የማነ በበኩሉ በአቶ አሰፋ ሀሳብና በፌዴሬሽኑ አቋም አይስማማም፡፡ ፌዴሬሽኑ መጠቀም ካለበትም ሌሎች ማናጀሮችን የሚስብ አሠራር ከኬንያ ተሞክሮ በመውሰድ ማዘጋጀት እንደሚያስፈልግ ነው የሚሞግተው። ለዚህም የአትሌቲክስ ካምፖች መገንቢያ የመሬት አቅርቦትም ሆነ ሌሎች ሁኔታዎችን ማመቻቸት ማናጀሮች በሌሎች ሀገራት የሚሠሩትን በኢትዮጵያም ለመሥራት ፍላጎት ያሳድርባቸዋል ይላል፡፡ ይህን ለማድረግም ማናጀሮች ፍላጎት አላቸው የሚል እምነት አለው፡፡

ያም ሆኖ የኢትዮጵያ አትሌቲክስ ፌዴሬሽን አሠራር ለዚህ ክፍት አይደለም ሲል ይወቅሳል፡፡ ከዚህ ይልቅ ፌዴሬሽኑ ማናጀሮችን በአስር ሺዎች የሚቆጠር ዶላር እንዲከፍሉ በመጠየቅ ተስፋ አስቆራጭ መንገድ ለመከተል እንደሚሞክር የሚጠቁመው አትሌት የማነ፣ ከዚህ ቀደም ይህ ገንዘብም በሚገኝበት ጊዜ ለአትሌቲክሱ በሚጠቅም ጉዳይ ላይ ውሏል የሚል እምነት እንደሌለው ያስረዳል። «ክለቦችም ቢሆኑ ለአትሌቱ ውድድር በማመቻቸት ምን ያህል እየሠሩ ነው» ሲልም ይጠይቃል፡፡

አዲሱ የፌዴሬሽኑ ሥራ አስፈጻሚም በዚህ ጉዳይ ላይ ትኩረት በመስጠትና አሠራሩን በማስተካከል ማናጀሮቹን መመለስ እንዲቻል መሥራት እንዳለበት የሚጠቁመው አትሌት የማነ፣ ክለቦችም ቅሬታ እንዳያድርባቸው ከማናጀሮች ጋር በማቀራረብ አብረው እንዲሠሩ ማድረግ ተገቢ መሆኑን ይጠቁማል፡፡

ማናጀሮች የኢትዮጵያ ሃብት በሆኑት አትሌቶች ተጠቃሚ ይሁኑ እንጂ ፌዴሬሽኑም ሆነ ሀገሪቷ ከእነሱ የሚጠቀሙት ነገር እንዳይኖር እንቅፋት የሆኑ ችግሮች መቀረፍ እንዳለባቸው አቶ አሰፋ ይናገራሉ፡፡ ይህንን ወደ መስመር ሊያመጣ የሚችል አሠራር በማዘጋጀትና ለዓለም አትሌቲክስ በማሳወቅ ስፖርቱ የሚያድግበት ሁኔታ መመቻች ይገባልም ይላሉ፡፡ ለወደፊትም ይህንን ሊያስታርቅ የሚችልና ሀገሪቷንም የሚጠቅም መመሪያ ማዘጋጀት አስፈላጊ እንደሚሆንም አመላክተዋል፡፡



# ባለፉት አምስት ወራት ከወጪ ንግድ 2 ነጥብ 7 ቢሊዮን ዶላር ገቢ ተገኘ

ሰሚራ በርሀ እና መክሊት ወንድወሰን

አዲስ አበባ፡- ባለፉት አምስት ወራት ከወጪ ንግድ 2 ነጥብ 7 ቢሊዮን የአሜሪካን ዶላር ገቢ መገኘቱን የንግድና ቀጣናዊ ትስስር ሚኒስቴር አስታወቀ፡፡ ወደ ኢትዮጵያ መጥተው ኢንቨስት ማድረግ ለሚፈልጉ የውጭ ሀገር ባለሀብቶች በፖሊሲ አስቻይ ሁኔታዎችን ለመፍጠር በትኩረት እየተሠራ እንደሆነም አመልክቷል፡፡

የንግድና ቀጣናዊ ትስስር ሚኒስቴር የወጪ ምርቶች ፕሮሞሽን መሪ ሥራ አስፈጻሚ አቶ በረከት መሠረት በተለይ ለአዲስ ዘመን እንደተናገሩት፤ ባለፉት አምስት ወራት ከወጪ ንግድ 2 ነጥብ 7 ቢሊዮን ዶላር ገቢ ተገኝቷል፤ ገቢው ከዚህ ቀደም በአንድ ዓመት የሚገኝ እንደነበር አስታውቀዋል፡፡

በበጀት ዓመቱ ከ178 ሺህ ቶን በላይ የቡና ምርት፣ በጥራጥሬና ቅባታማ እህሎች 140 ሺህ ቶን ኤክስፖርት መደረጉን ያመለከቱት አቶ በረከት፤ ላኪዎች ምርቶቻቸውን ለማጓጓዝ የሚያጋጥሟቸውን የፀጥታ ችግሮች ለመፍታት ሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ ድጋፍ ማድረጉን ጠቁመዋል ።

ላኪዎች ምርቶቻቸውን ከተመረተበት ቦታ ወደ ወደብ ለማምጣት በሚፈልጉበት ጊዜ ከወረዳ ጀምሮ አስፈላጊው የፀጥታ ድጋፍን እንዲያገኙ በማድረግ ውጤት ማምጣት ተችሏል ያሉት አቶ በረከት፤ ለዚህም ከክልል ጀምሮ እስከ ታችኛው የፀጥታ መዋቅር ድረስ በቅንጅት መሠራቱን ጠቁመዋል።

የሀገር ውስጥ ላኪዎች ከውጭ ሀገር ኩባንያዎች ጋር አብረው መሥራት የሚችሉበትን እና የሚያጋጥሟቸውን የፋይናንስ፣ የቴክኖሎጂ፣ የብቃትና የአፈጻጸም ችግሮች መፍታት የሚያስችላቸውን የፖሊሲ ማሻሻያዎች ተደርገው ወደ ሥራ መገባቱንም አስታውቀዋል፡፡ ማሻሻያው የኤክስፖርት የሥራ ዘርፍን ሽፋን በማድረግ ከባንክ ብድር በመውሰድ በሥራው ላይ ያልተሠማሩ ከሴክተሩ እንዲወጡ መደረጉን ገልጸዋል፡፡

እንደ አቶ በረከት ገለጻ፤ ላኪዎች ምርቶቻቸውን ለመሸጥ ያነሱት የነበረው የግብይት አማራጮችን በተመለከተ ከኢትዮጵያ ምርት ገበያ በተጨማሪ ሌላ አዋጅ ፀድቆ ወደ ሥራ ገብቷል ብለዋል፡፡ የግብይት አማራጭ ላኪዎች ወጪ ቆጣቢ በሆነ መንገድ ሳይገደቡ ግብይት እንዲያከናውኑ ማድረግ የሚያስችል እንደሆነ አመልክተዋል፡፡

በሀገር ውስጥ ኤክስፖርት ሥራ ላይ የተሰማሩ ላኪዎች በብዛት ምርቶችን ገዝተው ከመላክ ባለፈ፤ በእርሻው ዘርፍ ለመሠማራት ያላቸው ተነሳሽነት እምብዛም ነው ያሉት ኃላፊው መሬት ወስደው አልምተው መሥራት ለሚፈልጉ ላኪዎች አሁን ላይ ያለውን የኢንቨስትመንት ሪፎርሙ መልካም ዕድል ይዞላቸው እንደመጣ አስታውቀዋል ፤

እነዚህ ባለ ሀብቶች መሬት በቀላሉ እንዲያገኙ ሆነ፤ ወደ ንግድ ሥራ በቀላሉ እንዲገቡ የሚያስችሉ ምቹ ሁኔታዎችን ለመፍጠር እየተሠራ መሆኑን ገልጸዋል፡፡ ወደ ኢትዮጵያ መጥተው ኢንቨስት ማድረግ ለሚፈልጉ የውጭ ሀገር ባለሀብቶች በፖሊሲ አስቻይ ሁኔታዎችን ለመፍጠር በትኩረት እየተሠራ እንደሆነም አመልክተዋል።

# “ሁሉም ወገን አማራጭ ለማይገኝለትና...

ከገጽ 1 የዞረ

ብዙ ትንኮሳዎች ቢኖሩም ችግሮች በሠላም እንዲፈቱ ከሚገባው በላይ መንቀሳቀሱ ሊያስመሰግነው እንደሚገባም አመልክተዋል፡፡

እንደ ዋና ዳይሬክተሩ ገለፃ፤ መንግሥት የሠላም እንቅስቃሴው የበለጠ ትርጉም ሊያመጣ በሚችል መልክ አጠንክሮ መቀጠል አለበት። ነገር ግን በአንድ እጅ ማጨብጨብ የማይቻል በመሆኑ፤ መሣሪያ ያነገቱ ወገኖች ለሕዝብ እና ለሀገር ካሉ የሠላም አማራጩን ሊጠቀሙበት ይገባል፡፡

መንግሥት የሠላም ጥሪ ሲያደርግ የታጠቁ ኃይሎች ለመወያየት ፈቃደኛ ሆነው በሠላማዊ መንገድ ችግሮችን ለመፍታት ቁርጠኛ ሊሆኑ እንደሚገባ አመልክተው፤ እነዚህ ወገኖች እውነት ሕዝባዊ አቋም ካላቸው በሠላማዊ መንገድ ቢንቀሳቀሱ ሠላም ፈላጊ በሙሉ ይደግፋቸዋል የሚል እምነት እንዳላቸው አብራርተዋል፡፡

መንግሥትም የሠላማዊ መንገድ ላይ አጠንክሮ ቢገፋበትም በአንድ እጅ ስለማይጨበጨብ፤ ሁሉም ቢተባበር ትልቅ ለውጥ ሊመጣ እና መፍትሔ ሊገኝ ይችላል ብለዋል፡፡

በአሁኑ ወቅት የትግራይ ሁኔታ በውዥንብር መካከል መሆኑን እና ከውዥንብር የሚወጣበት ሁኔታ ላይ እንደሚገኝ አመልክተው፤ የፌዴራል መንግሥት በዚህ ላይ መፍትሔ ለማምጣት እየጣረ መሆኑንም አንስተዋል።

መንግሥት ጣልቃ ገብቶ አካታች የፖለቲካ ድርጅቶች የሚሳተፉበት ጊዜያዊ አስተዳደር እንዲመሠረት ግፊት ማድረግ ይጠበቅበታል ያሉት አረጋዊ (ዶ/ር)፤ ይህ የመደማመጥ ሁኔታ ከተፈጠረ እና አሁን ያለው የለውጥ አዝማሚያ ከተደገፈ በትግራይ ውስጥ ዘላቂ ሠላም ሊሰፍን እንደሚችል አመልክተዋል፡፡

# በሁሉም ኢንዱስትሪ ፓርኮች...

ከገጽ 1 የዞረ

መኖራቸውን ገልጸዋል፡፡ እንዲሁም ባለሀብቶች የለማ መሬት በሊዝ ወስደው በራሳቸው ግንባታው የሚሠሩባቸው ሼዶች እንዳሉ ጠቁመው፤ ሼዶች በሙሉ ሥራ ላይ እንዲውሉ ለማድረግ እየተሠራ መሆኑን አስታወቀዋል፡፡

በአሁኑ ጊዜ ሁሉም ፓርኮች ሥራ ላይ መሆናቸውን ገልጸው፤ በፓርኮቹ ለ100 ሺህ ዜጎች የሥራ ዕድል መፍጠር መቻሉን አስታወቀዋል፡፡ ቦሌ ለሚ ኢንዱስትሪ ፓርክ ብቻ ለ26ሺ ዜጎች የሥራ ዕድል ተፈጥሯል ብለዋል፡፡

የኢንዱስትሪ ፓርኮች 13 የኢንዱስትሪ ፓርኮችን ያስተዳድራል ያሉት አቶ ጳውሎስ፤ በቅርቡ የኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት ቦርድ ፓርኮቹ ያሉበትን ደረጃ በመገምገም አስራ አንዱን ወደ ልዩ ኢኮኖሚ ዞን እንዲሸጋገሩ መደረጉን አስታውሰዋል፡፡

የድሬዳዋ ነፃ የንግድ ቀጣናን ጨምሮ 10 ኢንዱስትሪ ፓርኮች አስፈላጊውን መስፈርት በማሟላታቸው ወደ ልዩ ኢኮኖሚ ዞን የተሸጋገሩ መሆናቸው አስታውቀዋል። ይህም ወደ ኢትዮጵያ ዓለም አቀፍ ኢንቨስተሮችን ለመሳብ ትልቅ ፋይዳ እንዳለው አመልክተዋል፡፡

የተቀሩት ሁለቱ ፓርኮች (አረርቲ ኢንዱስትሪ ፓርክ እና አዲስ ኢንዱስትሪ ቪሌጅ) አሁን ላይ መሟላት ያለባቸው መሠረተ ልማቶች ያላሟሉ መሆኑን ጠቅሰው፤ ወደ ልዩ ኢኮኖሚ ዞን ማደግ አለመቻላቸው ገልጸዋል፡፡

በቀጣይ ወደ ልዩ ኢኮኖሚ ዞን ያልተሸጋገሩ የኢንዱስትሪ ፓርኮችን የማሸጋገር ሥራዎች እየተሠሩ ነው ያሉት አቶ ጳውሎስ፤ አረርቲ ኢንዱስትሪ ፓርክ ያልተሟሉለትን መሠረተ ልማቶች የማሟላት ሥራዎች እየተሠሩ መሆኑን ተናግረዋል፡፡ አዲስ ኢንዱስትሪ ቪሌጅ ግን መሐል ከተማ ላይ የሚገኝ እንደመሆኑ ልዩ ኢኮኖሚ ዞን ለማድረግ የማይቻልባቸው ሁኔታዎች መኖራቸው አመላክተዋል፡፡

ወደ ልዩ ኢኮኖሚ ዞን ያደጉት የኢንዱስትሪ ፓርኮችም ቦሌ ለሚ ኢንዱስትሪ ፓርክ፣ አዳማ ኢንዱስትሪ ፓርክ፣ ባሕርዳር ኢንዱስትሪ ፓርክ፣ ደብረ ብርሃን ኢንዱስትሪ ፓርክ፣ ሀዋሳ ኢንዱስትሪ ፓርክ፣ ቂሊንጦ ኢንዱስትሪ ፓርክ፣ ኮምቦልቻ ኢንዱስትሪ ፓርክ፣ መቀሌ ኢንዱስትሪ ፓርክ፣ ጅማ ኢንዱስትሪ ፓርክ እና ሰመራ ኢንዱስትሪ ፓርክ መሆናቸውን የኮርፖሬሽኑ መረጃ ያሳያል፡፡

ማህበራዊ

# የሕይወት ገጽታ

## ‹‹በመልካምነት የሰዎችን ሕይወት ማቅናት እንችላለን››

- ሰዓሊና የሥነ ጥበብ መምህር ዓለም ጌታቸው



ዳግም ከበደ

**ሰዓሊ ናት፤ የህፃናት መጻሕፍት ደራሲም ጭምር። ትውልድ በሥነ ምግባር ታንጾ ያድግ ዘንድ ብርታት ለመሆን ያላትን ለማካፈል ትተጋለች። ‹‹ዓለም የሥነ ጥበብ ማዕከል›› የተሰኘ የስዕል ትምህርት ቤት በአዲስ አበባ ገርጂ አካባቢ በመክፈት ለዓመታት እያስተማረች ትገኛለች። ‹‹አብረን›› የተሰኘ የበጎ አድራጎት ድርጅትም አቋቁማ በመልካም ምግባር ላይ ተሰማርታለች። በርካታ የስዕል ኤግዚቢሽኖችን በጋራና በግል አዘጋጅታለች። ይህቺ ሴት ሰዓሊ ዓለም ጌታቸው ትባላለች።**

**በቅርቡ በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ አለፈለገ ሰላም የሥነ ጥበብ ትምህርት ቤት ‹‹ነገን ዛሬን እንሳል›› በሚል ርእስ የአካል ጉዳተኞችን የሚገጥማቸውን አስቸጋሪ ሕይወት በጥበብ ለታዳሚያን ለማሳየት ችላለች። ዛሬ እዚህ ለመድረሷ ትናንት በብዙ ትግል ውስጥ ልታልፍ የግድ ነበር። ዓለም ገና በ12 ዓመቷ ነበር ለአካል ጉዳት የተጋለጠችው። ይህ አጋጣሚ አበረታት እንጂ ተስፋ ለመቁረጥ ምክንያት አልሆናትም። የዝግጅት ክፍላችን የዓለም የሕይወት መንገድ ለትውልድ አንዳች እውነት እንደሚገልጥ በማመኑ እንግዳችን እንድትሆን ጋብዟታል። መልካም ቆይታ!**

### ትውልድና እድገት

ለብዙዎች የብርታትና ምሳሌ የሆነች ሰዓሊና የሥነ ጥበብ መምህር ዓለም የተወለደችው በሰሜኑ የኢትዮጵያ ክፍል በጎንደር አዘዞ ነው። አባቷ ኢንስፔክተር አቶ ጌታቸው ወርቁ ትውልዳቸው አዲስ አበባ ይሁን እንጂ በውትድርና በሜካኒክነት ይሠሩ ስለነበር ከባለቤታቸው ጋር ተዋውቀው ትዳር የመሠረቱት በጎንደር ነው። በውትድርና ግዳጅ ከቦታ ወደ ቦታ መዘዋወር የግድ ነውና ታዳጊዋ ገና በህፃንነቷ ቤተሰቦቿን ተከትላ ወደ ኤርትራ መሄድ ነበረባት። አባቷ የተበላሹ ወታደራዊ አውሮፕላኖችን ጨምሮ የሜካናይዝድ መሳሪያዎችን በመጠገን የሚታወቁ ሜካኒክ መሆናቸው አንድ ቦታ ተቀምጦ ቤተሰቡ ሕይወትን እንዲመራ እድል የሚሰጥ አልነበረም።

በዚህ ምክንያት ቤተሰቦቿ ዓለምን በድጋሚ ወደ አያቶቿ ለመመለስ አስገደዳቸው። አያቷ ነበሩ ወደ ኤርትራ አቅንተው ብዙም ሳትቆይ በሰባት ዓመቷ ወደ ጎንደር ይዘዋት የተመለሱት። ዓለም በልጅነቷ ዝምተኛ ነበረች። የካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን አዘውትራ ትሄድ ነበር። ከተፈጥሮ ጋር ጥብቅ ቁርኝት ነበራት፤ ለቤት እንስሳት በተለይ ለድመት ልዩ ፍቅር አላት፤ አትክልቶችን መትከልና መንከባከብም እንዲሁ የልጅነት ልዩ ዝንባሌዋ ነበር። ለጥበብ ቅርብ እንድትሆንና ስስ ልብ እንዲኖራት ይህ ዝንባሌዋ መሠረት ነበር። ነገር ግን ዝምተኛ መሆኗና ይበልጥ ከቤት እንስሳት ጋር ቅርበት መፍጠሯ በቤተሰቦቿ እምብዛም አይወደድላትም ነበር።

ሰዓሊና መምህር ዓለም በጎንደር ቀያምባ የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤት ለሶስት ዓመታት ተምራለች። ኤርትራ በቆየችባቸው ዓመታት ቤት መኻ የሚባል ትምህርት ቤት ገብታ ነበር። ከሌሎች ተማሪዎች በተለየ የስዕል ልዩ ዝንባሌ ነበራት። የደረጃ ተማሪ ባትሆንም ጎበዝ ከሚባሉ መካከል ነበረች። በተለይ መምህሮቿ በብላክ ቦርድ ላይ የሚሳሉ ማስተማሪያዎችን እንድትሠራ ያበረታቷት ነበር። በቀያምባ ለተከታታይ ሶስት ዓመት በዚህ ተግባሯ ቀጥላ ልዩ እውቅናን አትርፋበታለች።

‹‹የስዕል ተሰጥኦዬን የወረስኩት ከአባቴ ነው። ኤርትራ በነበርኩበት ወቅት ስዕል ብቻ ሳይሆን መጻሕፍትንም እንዳነብ ያበረታታኝ ነበር›› ትላለች፤ አባቷ ለጥበብ ቅርብ እንደነበሩና የእርሳቸውን ፈለግ እንደተከተለች በመግለጽ። እርሳቸው ግን ቤተሰብ ለመምራትና ሀገርን ለማገልገል በሌላ የሙያ መስክ ላይ በመቆየታቸው ልክ እንደ እርሷ ለጥበብ ቅርብ አልሆኑም።

### ዳግም ወደ ኤርትራ-ያልታሰበው አጋጣሚ

ሰዓሊ ዓለም ወደ ኤርትራ ዳግም ተመልሳ ከወላጆቿ ጋር መኖር የግድ አላት። አያቶቿን ተሰናብታ ከስምንተኛ ክፍል ትምህርቷን አቋርጣ ወደ አስመራ አቀናች። ጊዜው የደርግ ወታደር ከኤርትራ አማፂያን እና ከወያኔ ጋር ከፍተኛ ጦርነት የሚያደርግበት ወቅት በመሆኑ ሀገሪቱ ላይ መረጋጋት አይታይም ነበር። የዓለም ቤተሰብ ያረፈው አስመራ ከተማ ፀፀራት አካባቢ (ቃኘው የሚባል ወታደራዊ ካምፕ በሚገኝበት ሥፍራ) ነበር። ይሁን እንጂ በዚያም ከአንድ ዓመት በላይ መቆየት አልቻለችም። ምክንያቱ ደግሞ ጦርነት እየተባባሰ በመምጣቱ ነበር። በተለይ መኖሪያ ቤታቸው የወታደር ካምፕ አካባቢ ስለነበር የከባድ መሳሪያም ሰለባ ሆኖ ነበር።

ከጦርነቱ ባሻገር የዓለም የአስመራ ቆይታ እንደ ቀድሞው የልጅነት ጊዜዋ አልነበረም። አስመራ ወላጆቿ ጋር እንደደረሰች በሰውነቷ (እግሯና የጀርባ አጥንቷ አካባቢ) የተለየ ህመም ታስተናግድ ጀመር። ጎንደር እያለች የሰውነቷ መገጣጠሚያ አካባቢ ህመም ይሰማት የነበረ ቢሆንም እንዳሁኑ የከፋ አልነበረም። ይህ ህመም ተባብሶ በእግሯ መሄድ እንዳትችል አስገደዳት። አጋጣሚው ከጦርነቱ ጋር ተደምሮ የቤተሰቡን የሕይወት አቅጣጫ የቀየረ ፈተናን ፈጠረ።

የሻዕቢያና ወያኔ አማፂያን ከደርግ ጋር የሚያደርጉት ጦርነት መባባሱ ቤተሰቡ ዳግም ከነበረበት ስፍራ እንዲለቅ አስገደደው። አባታቸው እዚያው መቅረት ስለነበረባቸው እናታቸው እሷንና አራት እህት ወንደሞቿን ይዘው በወታደር አውሮፕላን ወደ አዲስ አበባ መጡ። ዓለም ወደ ትራንስፖርት ቦታ ስትጓዝ በእግሯ እየተራመደች አልነበረም፤ ባጋጠማት የአካል ጉዳት ምክንያት ለመንቀሳቀስ የቤተሰብ ድጋፍ (መታዘል) ያስፈልጋት ነበር። ይህን ጊዜ ነበር የአካል ጉዳት ያስከተለባትን ፈተና ለመጋፈጥ አዲሱን ማንነትና የሕይወት ውጣ ውረድ ለመቀበል የሚያስችል ግዴታ ውስጥ የገባችው።

### ፈተናን የመጋፈጥ ፅናት

በአዲስ አበባ ሕይወት ለዓለም አልጋ በአልጋ አልሆነችም። የተረጋጋ መኖሪያ ለማግኘት የአክስትና አጎታቸውን ድጋፍ ቢያገኙም ለመረጋጋት ጊዜ ወስዶባቸዋል። በዚያ ላይ ካልጠበቀችው የአካል ጉዳት ህመም ጋር የተጋፈጠችበት ወቅት መሆኑ የእርሷን ጨምሮ የቤተሰቡን ሕይወት ያከበደ ነበር። ብዙም ሳይቆዩ ካረፉበት ለገሀር አካባቢ በአክስታቸው ድጋፍ አሁንም ድረስ ወደምትኖርበት ሰፈር (ገርጂ ሮባ ዳቦ ቤት አካባቢ) በ50 ብር አንድ ክፍል ቤት ተከራይተው መኖር ጀመሩ። ዓለም በአዲስ ቤት በአዲስ የሕይወት መንገድ የሕይወት ገጿን መፃፍ ጀመረች።

በሀገሪቱ የሥርዓት ለውጥ ብዙም ሳይቆይ ነበር የመጣው። ይህ አጋጣሚ በእናቷ ላይ የኢኮኖሚ ጫና ይዞ የመጣ ነበር። በዚህ ምክንያት ልጃቸውን ወደ ሕክምና ለመውሰድ እና ለማመላለስ አስቸጋሪ አደረገባቸው። ዓለምም ትምህርቷን አቋርጣ ቤት ውስጥ ለስድስት ዓመታት ተቀመጠች።

‹‹የገጠመኝ ችግር ከትምህርት ቢያስቀረኝም በቤት ውስጥ በብዛት መጻሕፍትን ማንበብ ልምዴ አደረኩ። በተጨማሪ የስዕል ተሰጥኦዬን አዳብር ነበር›› የምትለው የዛሬው የሕይወት ገፅታ እንግዳችን ሰዓሊና መምህር ዓለም፤ የምታነባቸውን መጻሕፍት ለማግኘት በአካባቢው የሚገኙ ሰዎች በብድር በእህቶቿና በተለያዩ ሰዎች አማካኝነት ታገኝ ነበር።

በእነዚህ ዓመታት ከቤት መውጣት ስለማትችል በምትፈልግበት ጊዜ ከጎረቤትም ሆነ ዘመድ ጋር የመገናኘት አጋጣሚ አልነበራትም። በጊዜው ሲበዛ ዝምተኛ ከመሆኗ የተነሳ የአዕምሮ ህመም ያጋጥማታል ብለው ቤተሰቦቿ ይሰጉ ነበር። ለማንበብና ለመሳል ምክንያት የሆኗት አባቷ የሥርዓት ለውጡን ተከትሎ ወደ አዲስ አበባ መጥተው በሹፍርና ተቀጥረው እየሠሩ ከቤተሰቦቻቸው ጋር በአንድነት መኖር ጀምረዋል። አጋጣሚው የምታነበው ጋዜጣ ቶሎ ቶሎ እንድታገኝ እድል ፈጠረላት፤ (የችርቻሮ እቃ መጠቅለያ ሆነው የሚመጡ ጋዜጦችን ጭምር) በማንበብ እና የስዕል ሥራዋ ላይ በማተኮር እውቀቷን ታዳብር ነበር።

### ጓደኝነት- አዲስ አቅጣጫ

የሰዓሊ ዓለም የወጣትነት የሕይወት አቅጣጫ የቀየረ አንድ ክስተት ተፈጠረ። አሁን በሕይወት የሌለች መነን ልዑልሰገድ የተባለች በገርጂ እምቡጥ ትምህርት ቤት መምህር ጋር ተዋወቀች። መነን የዓለምን ታሪክ ከሰዎች ሰምታ ስለነበር ቤቷ ድረስ በመሄድ ነበር የተዋወቀቻት።

ስለ ትውውቃቸው በማስታወስ ‹‹መልካም ሰዎች የሰዎችን ሕይወት ያቀናሉ›› በማለት በጊዜው መምህር መነንም የሕይወት አቅጣጫዋን የቀየሩ ድጋፎችን ታደርግላት እንደነበር ትናገራለች። መጻሕፍትን በመከራየት፣ ጓደኛዋ በመሆን እና የምትወዳቸውን ምግቦች እየሠራች በማምጣት በቤት ውስጥ መቀመጧ የሚፈጥርባትን የብቸኝነት ስሜት ጫና እንዳይፈጥርባት አገዘቻት። በተለይ ለዓመታት አቋርጣው የነበረው ትምህርት በርቀት እንድትቀጥል ያበረታታቻትና እድሉን ያመቻቸችላት ይህቺ መልካም ሰው ነበረች።

> **የገጠመኝ ችግር ከትምህርት ቢያስቀረኝም በቤት ውስጥ በብዛት መጻሕፍትን ማንበብ ልምዴ አደረኩ። በተጨማሪ የስዕል ተሰጥኦዬን አዳብር ነበር**

‹‹መነን ለኔ እግሬ ማለት ነበረች›› ትላለች በጊዜው የሕይወት አቅጣጫዋን እንዴት እንደቀየረችው ስትናገር። መጻሕፍት እንዳትቸገር ከማድረግ ባሻገር ፓን አፍሪካን የርቀት ትምህርት ቤት (ኋላ ላይ ኮሌጅ የሆነው) ተመዝግባ ትምህርቷን እንድትማር ያደረገቻት እርሷ እንደነበረች እየመሰከረች። ቀለም ተጠቅማ በሸራ ላይ ስዕል መሳል እንድትጀምር ምክንያት የነበረችውም መነን ነች። በእሷ አማካኝነት የተዋወቀቻቸውን ሌሎች ወዳጆቿ የስዕል ቀለም ያመጡላት ነበር። በዚህ የመደጋገፍና የቀናነት ስሜት የሰዓሊ ዓለምና የመምህር መነን ጓደኝነት ለ17 ዓመታት መዝለቅ ችሏል።

ሰዓሊ ዓለም በጊዜው መልክዓ ምድሮችን የሚያሳይ (Landscape) የአሳሳል ዘይቤ ላይ ታተኩር ነበር። ለተፈጥሮ የቀረበ ነብስ ስላላት ሥራዎቿም ያንኑ የሚያንፀባርቁ ናቸው። በተለያየ የሕይወት ፈተና ውስጥ የሚያልፉ ሴቶችን የሚገልጽና መንፈሳዊነትን የሚያሳዩ የጥበብ ውጤቶችን ትሠራለች። በቀለምና ሸራ ላይ ስዕሎቿን መሥራት መጀመሯ ደግሞ ከበርካታ ሰዎች ጋር እንድትተዋወቅና ተሰጥኦዋን የሚያደንቁ ወዳጆች እንድታፈራ እድል ፈጠረላት።

የመጀመሪያ የሸራ ላይ ሥራዋን ለአንድ ካቶሊክ ካህን በ150 ብር እንደሸጠች የምታስታውሰው ሰዓሊ ዓለም፤ የምትወደውን እየሠራች ኑሮዋን መደጎም እንደምትችል ያረጋገጠችበት አጋጣሚ እንደተፈጠረ ትናገራለች። አንድም ጊዜ ቢሆን የስዕል ሥራዎቿን መሸጥ እችላለሁ የሚል እሳቤ አልነበራትም። የካቶሊክ ካህኑ የገዟት የእየሱስ ክርስቶስ የስቅለት ስዕል ግን ከሙያም ባሻገር በሰዓሊነት የኑሮ መሠረት መጣል እንደምትችል ተስፋ እንዲሰጣት በር ከፈተላት።

### ወደ ሻሸመኔ-ጂጌሳ

ሰዓሊና የሥነ ጥበብ ማዕከል መስራች ዓለም በጓደኛዋ ምክር የጀመረችውን የርቀት ትምህርት እስከ አስረኛ ክፍል ተምራ ወደ አስራ አንደኛ ክፍል የሚያሸጋግራትን የማለፊያ ውጤት አገኘች። ትምህርቱን ለመቀጠል በዝግጅት ላይ እንዳለች ግን አንድ የሕክምና እድል አገኘች። እድሉን የሰጣት በሻሸመኔ ጅጌሳ አካባቢ የሚገኝ በጣሊያኖች የተመሠረተ የካቶሊክ ቤተክርስቲያንና ድርጅት ነበር። ለዓመታት የፈተናት የአካል ጉዳት ህመም ‹‹መፍትሔ ይገኝለታል›› የሚል ተስፋ ስላሳደረባት በጉጉት ምንም ሳታቅማማ ነበር ወደዚያው ያቀናችው።

‹‹በማዕከሉ እየመጡ ሕክምና የሚሰጡ የውጭ ሀገር ሐኪሞች ነበሩ›› የምትለው ሰዓሊና የሥነ ጥበብ ማዕከል መሥራች ዓለም፤ ሕክምናውን ለማግኘት ስትል ለዓመታት መሸጋበት ከነበረው ቤት ለመውጣትና ወደ ሻሸመኔ ለመሄድ እንደቻለች ትናገራለች። በጊዜው አይደለም ከቤት መውጣት ይቅርና የአካል ጉዳተኞች የሚጠቀሙበት ዊልቸር (መጓጓዣ) አልነበራትም፤ ከናካቴውም ዊልቸር ምን እንደሆነ አታውቅም ነበር።

ወደ ገጽ 7 ዞሯል

# የሕይወት ገጽታ

## ‹‹በመልካምነት የሰዎችን...

ከገጽ 6 የዞረ

ዓለም ይህ ውሳኔ ወደ ሌላ የሕይወት አቅጣጫ የመራት እንደነበርም ታስታውሳለች።

‹‹ማዕከሉ በር ላይ ስደርስ ለመጀመሪያ ጊዜ ዊልቸር መጣልኝ›› ትላለች ወቅቱን እያስታወሰች። ግቢው ሰፊ ሲሆን የሙያ ማስተማሪያ ማዕከላትን ጨምሮ የአካል ጉዳት ያስተናገዱ ዜጎችን የሚታከሙበት ተቋም ያቀፈ እንደሆነ እየተናገረች። ወደ ግቢው እንደገባች ነበር እስከ ወዲያኛው አመለካከቷን የቀየረ ትዕይንት አጋጠማት። በማዕከሉ በጣም ብዙ አካል ጉዳት ያስተናገዱ ሰዎችን ተመለከተች። እሷ ካጋጠማት እክል በባሰ ሁኔታ ውስጥ የሚገኙ ያለ ሰው ርዳታ ምንም ማድረግ የማይችሉ ሰዎችን ተመለከተች።

‹‹በሁኔታው በጣም ነበር የደነገጥኩት፤ በዓለም ላይ እኔ ብቻ የአካል ጉዳተኛ የሆንኩ ይመስለኝ ነበር›› የምትለው ሰዓሊ ዓለም፤ በማዕከሉ ባየችው ነገር በእጅጉ መገረሟን ታነሳለች። እርሷ የተሻለ ሁኔታ ውስጥ እንደሆነችና መሥራት እንደምትችል እንድታምን ምክንያት የሆናትም ይሄው አጋጣሚ ነው። ሕክምናውን (ቴራፒ) በጀመረችበት ወቅት ለዓመታት ከጉዳቱ ጋር የቆየች በመሆኑ ከፍተኛ የሆነውን ህመም ልትቋቋመው አልቻለችም ነበር። በዚህ ምክንያት በማዕከሉ የተሰጣትን እድል ለመተውና ሕክምናውን ለማቋረጥ ተገደደች።

### ስዕል ትምህርት ቤት-አሰላ

ሰዓሊ ዓለም በሕክምናው ባትቆይም በሻሸመኔ ጂጌሳ ማዕከል ነበረች። በዚያ በቆየችባቸው ጊዜ ውስጥ በልምድና በተፈጥሮ ያዳበረችውን የስዕል ችሎታዋን ማሳየት ችላ ነበር። በግቢው ለሚገኙ ጣሊያኖች የተለያዩ ስዕሎችን እያዘጋጀች በስጦታ ታበረክትላቸው ነበር። ከእነዚህ ሰዎች መካከል አንዱ ጂኖ የሚባለው ጣሊያናዊ ይገኝበታል። በወቅቱ በሥራዎቿ በመደነቁና በችሎታዋ በማመኑ ወደ ፕሮፌሽናል ሰዓሊነት እንድትሸጋገር የሚያግዛት ትምህርት ሊያስተምራት ቃል ገባላት።

ጂኖ በቃሉ መሠረት ዓለምን ትምህርት ቤት አስገባት። የስዕል ትምህርት ቤቱ በአሰላ የሚገኝ ነበር። የመግቢያ ፈተናውን በቀላሉ አለፈች። የሥነ ጥበብ ትምህርት ቤቱ በካቶሊኮች የተከፈተ ሲሆን በአዳሪ ትምህርት ቤት የሚያስተምር ነበር። ዓለም ብቸኛ ሴት ተማሪ የነበረች፤ በዚያ ግቢ ውስጥ ለማደር አትችልም ነበር። በዚህ ምክንያት የአካባቢው ነዋሪዎች ተፈልገው እንደ ሞግዚት እያስተዳደሯት እንድትማር ሆነ። በጊዜው አንዳንድ ፈተናዎችን ማለፍ የግድ ቢላትም ለሶስት ዓመታት የዘለቀ የስዕል ትምህርቷን በስኬት አጠናቀቀች።

ከአሰላ ሥነ ጥበብ ማዕከሉ እንደወጣች ጣሊያናዊ ጂኖ እራሱ ቀጠራት። የተለያዩ የስዕል ሥራዎችን እንድትሠራለት ከማድረጉም በላይ ሥነ ጥበብ መምህር አደረጋት። ምክንያቱ ደግሞ በሚያስተምራት ወቅት ያወጣውን ወጪ እንደምትመልስ ውለታ ስለነበራቸው ነው። ጂኖ በሻሸመኔ የአርት ማዕከል ከፍቶ ስለነበር ለአራት ዓመታት በዚያ እንድትሠራ የግድ ሆነ።

በማዕከሉ ከምትሠራው የስዕል ሥራ ባሻገር አንደ ኩየራ፣ ጋምቦና ገጠራማ የሻሸመኔ አካባቢዎች በመሄድ ተሰጥኦ ያላቸውን ወጣቶችን ታስተምር ነበር። በጊዜው በሻሸመኔ ተከፍቶ በነበረው አርት ማዕከል ውስጥ ከማስተማር ጎን ለጎን ስዕሎችን በትእዛዝ እየሠራች ወደ ጣሊያን ይላክ እንደነበርም ትገልፃለች።

በጊዜው ሙያዋንና የወደፊት ህልሟን ለማሳካት የሚያስችል እውቀትና የሕይወት ልምድ ብታገኝም ፈታኝ ሁኔታዎችን ማለፍ የግድ ይላት ነበር። ለምሳሌ በገጠራማ አካባቢዎች በመሄድ በምታስተምርበት ወቅት የመንገዱንና የትራንስፖርት ውጣ ወረዱ አንዱ ፈተና ነበር።

‹‹ቀኑን ሙሉ ሳስተምር ውዬ ማታ ነበር ወደ ሻሸመኔ የምመለሰው። ይሁን እንጂ ይህ ፈተና ጠንካራ አድርጎ ቀርፆኛል›› የምትለው ሰዓሊ ዓለም በዚያ ውስጥ ከቤተሰብ በብዙ ኪሎ ሜትር እርቆ ሕይወትን መጋፈጥ፣ እራስን የማግኘት ሩጫና የሥራን ጥቅም መረዳት እንድትችል እድሉን እንደሰጣት ትናገራለች።

የጂኖ አባት ወደ ኢትዮጵያ ሲመጡ በዓለም ሥራ እና ተሰጥኦ በመደነቃቸው ወደ ጣሊያን ስፖንሰር አድርገው ለማስተማር ፍላጎት ነበራቸው። ነገር ግን በልጃቸው አለመስማማት ምክንያት እድሉን ሳታገኝ ቀየች። ነገር ግን እድሉን በማጣቷ ብዙም አልቆጫትም። ምክንያቱ ደግሞ በዓመታት ቆይታዋ የሙያን ጥቅም፣ ኃላፊነትን የመወጣት



**አዕምሮዬም ሰልጥኗል፤ እውቀትም አግኝቻለሁ። የመሥራት ፍላጎቴ ከፍተኛ ነበር**

እና የሰዓሊነት ችሎታን በተግባር መቅሰም በመቻሏ ነው። ስለ ሁኔታው መለስ ብላ ስታስብ ‹‹ይህ ለኔ በቂ ነበር፤ በጣሊያን ሀገር መማር ብችል መልካም የነበረ ቢሆንም የሚያስቆጨኝ ግን አልነበረም›› ትላለች።

### ዳግም ወደ አዲስ አበባ

የጣሊያናዊው ጂኖ የሥነ ጥበብ ማዕከል ከአራት ዓመት በላይ አልዘለቀም። ዓለምም በዚያ አልቆየችም። ከፍሎ ያስተማራትን እዳ ከመመለስ ባሻገር ተጨማሪ ሕይወቷን የምታሻሽልበት ጥሪት የሚያስቋጥር አጋጣሚ አላገኘችም። ነገር ግን ከእርሷ የማይለይ እውቀትና የሥራ ሥነ ምግባርን አዳብራ ነበር ወደ ቤተሰቦቿ ከዓመታት በኋላ የተመለሰችው።

‹‹አዕምሮዬም ሰልጥኗል፤ እውቀትም አግኝቻለሁ። የመሥራት ፍላጎቴ ከፍተኛ ነበር›› የምትለው ሰዓሊ ዓለም ከምንጊዜውም በተለየ የሞራል ስንቅን ይዛ እንደተመለሰች ትናገራለች። ይሁን እንጂ በቤተሰቦቿ ቤት መኖርና እንደልቧ በአካባቢው በዊልቸር ለመንቀሳቀስ ይከብዳት እንደነበር ትናገራለች።

ሰዓሊ ዓለም በመንፈሳዊ ሕይወቷ ጠንካራ መሆኗና አዘውትራ ከቤተክርስቲያን አለመጥፋቷ ሕይወቷ የተስተካከለ እንዲሆንና ለሚገጥማት ፈተና ሽብረክ እንዳትል እንደሚረዳት ትገልፃለች። ተስፋ ላለመቁረጧ ምክንያት የሆናት የመንፈሳዊ ሕይወቷ የሰጣትን መረጋጋት በምክንያትነት ታነሳለች።

### የግል ሥራን መጀመር

ከቀደመው ጊዜ በተሻለ ከሰዎች ጋር የነበራት ትውውቅና ህብረት ጠንክሯል። ዛሬ ብቻዋን አይደለችም፤ ብዙዎች ሕይወቷ የተቃና እንዲሆን ይሻሉ። በዚህ ምክንያት የኔ የምትላቸው ሰው በምትኖርበት አካባቢ አነስተኛ የግል ሱቅ እንድትከፍት ቤት ኪራዩን በመክፈል አገዟት። እኚህ ሰው አሁን የባህር ዳር አቡን የሆኑት ልሳነ ክርስቶስ ናቸው።

በጊዜው ሁለት በሁለት በሆነችው ሱቅ ውስጥ የስዕልና የጥበብ ሥራዎችን በመሥራት ለሽያጭ ማቅረብ ጀመረች። በምትሠራቸው የስዕል ሥራዎች የሚማረኩና የጥበብ ፍቅር ያላቸው ሰዎችን ትእዛዝ እየተቀበለች ማቅረብ ጀመረች። በዚያ እራሷን ከመደጎም አልፋ የቤት ኪራይ መክፈል ጀመረች። የዓለም ስኬትና ቀጣይ የተሳካ አቅጣጫ በዚህች ሱቅ አንድ ብሎ ጀመረ።

### የሥነ ጥበበ ማዕከል

በሱቋ ውስጥ የስዕል ሥራዎችን ስትሰራ በዚያው አካባቢ ያሉ ህፃናትና ታዳጊዎች ይመለከታሉ። በተደጋጋሚም ከእውቀቷ እንድታካፍላቸውና ስዕል እንድታስተምራቸው ይጎተጉቷት ጀመር። በዚያች ጠባብ ክፍል ጥያቄያቸውን እየተቀበለች ማስተማር ቀጠለች። ይህንን የተመለከቱ የአካባቢው ነዋሪዎችም ልጆቻቸውን ከፍለው ለማስተማር ጭምር ጥያቄ ያቀርቡላት ጀመር። ሶስት ልጆችን በመቀበል የተጀመረችው ትምህርት ቀስ በቀስ እያደገ መጣ። ቀደም ሲል በሻሸመኔ የነበራት የማስተማር ልምድን አገዛት። የማስተማር ሂደቱ እየሰፋ መምጣቱና በብዙዎች ዘንድ ተቀባይነት ማግኘቱ የሥነ ጥበብ ማዕከል በ2004 ዓ.ም በዚያው በገርጂ አካባቢ እንድትከፍት ምክንያት ሆናት።

ዛሬ ‹‹ዓለም የሥነ ጥበብ ማዕከል›› ከተመሠረተ 13 ዓመታትን አስቆጥሯል። በገርጂ አካባቢ ታዋቂና ብዙዎች ልጆቻቸውን የሚያስተምሩበት ተመራጭ ማዕከል ነው። ከተመሠረተ ጀምሮ እስካሁን አራት ሺህ ተማሪዎችን አስመርቋል። ይህ ማዕከል ለልጆች የጥበብ ትምህርት በመስጠትና ከፍተኛ ቁጥር ያላቸው ታዳጊዎችን በማሰልጠን ቀዳሚው ነው። ልጆቹ ሥራዎቻቸውን ለእይታ የሚያቀርቡበት ኤግዚቢሽንም በየጊዜው ያዘጋጃል።

ሰዓሊና መምህር ዓለም ዛሬ በዚያው በገርጂ አካባቢ መንግሥት ባመቻቸላት ሼድ ውስጥ ታዳጊዎችን ማስተማሯን ቀጥላለች። ዓለም ጋለሪም እንዲሁ ሥራውን ይሠራል። በተጨማሪነት በኪራይ ማዕከሉን በማስፋፋት ሌሎች ጥበባዊ መሰናዶዎችን ታዘጋጃለች። በማዕከሉ ብዙዎች የስዕል ትምህርት ከማግኘታቸውም ባሻገር መጻሕፍትን ያነቡበታል፤ በሳምንት አንድ ጊዜ የሥነ ጥበብ (አውደ ሃሳብ የውይይት መድረክ) ዝግጅቶች ይደረጋሉ። ልትደርስበት የምታስበው ራዕይ ትውልድ የሚያቀና ለብዙዎች መጠንከር ምሳሌ ስለሆነ ዛሬ ላይ ብዙዎች ከጎኗ ቆመዋል።

ሰዓሊ ዓለም የመጣችበትን መንገድ፣ የገጠማትን ፈተናና ውጣ ውረድ በጠንካራ መንፈስ እና አልበገር ባይነት አልፋዋለች። በዚህ ውስጥ ደግሞ ብዙዎች ቀና ትብብርና ድጋፍ አድርገውላታል። እሷ እዚህ ለመደረሷ ምክንያት ሰዎች የራሳቸውን ጡብ እንዳኖሩት ሁሉ እሷም በመሰል ችግር ውስጥ የሚያልፉ ዜጎችን መደገፍ የሁልጊዜ ምኞቷ ነው። ይህ ሀሳቧ ታዲያ ምኞት ብቻ ሆኖ አልቀረም።

በዚህ ምክንያት ከዛሬ አምስት ዓመት በፊት ‹‹አብረን›› የተሰኘ የበጎ አደራጎት ማዕከል አቋቁማለች። ‹‹በየሄድኩበት አካባቢ ችግር ውስጥ የሚገኙ አካል ጉዳተኞች ያጋጥሙኛል›› የምትለው ሰዓሊ ዓለም፤ በተለይ የሥነ ጥበብ ፍቅር ያላቸውን 40 የሚደርሱ አካል ጉዳተኞች በማሰባሰብ የሕይወት አቅጣጫቸው መስመር እንዲይዝ ድጋፍ እያደረገች መሆኑን ትገልፃለች። በአብረን ውስጥ 10 አባላት ያለው ቡድን ሲኖር የበጎ ምግባሩ በመደገፍ በጋራ ይሠራሉ።

‹‹አብረን ትኩረቱን ጥበብ ላይ አድርጎ የአስተሳሰብ ለውጥ እንዲመጣ እየሠራ ነው›› የምትለው ሰዓሊና መምህር ዓለም፤ አካል ጉዳተኞችን በማሰልጠንና የሕይወት ክህሎት በማስታጠቅ እንደሚሠሩ ትናገራለች። ከቀናት በፊትም በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ በአለ ፈለገ ሰላም የሥነ ጥበብ ትምህርት ቤት ውስጥ 60 ተፅዕኖ መፍጠር የቻሉ ጋዜጠኞች፣ ዶክተሮች፣ ሰዓሊዎች፣ መምህራን፣ የመንግሥት ኃላፊዎች የተሳተፉበት የስዕል አውደ ርዕይ በመክፈት ለበርካታ ቀናት ለእይታ በቅቷል። ‹‹አብረን ለትውልድ›› የሚል ርዕስ ያለው መጽሐፍም ታትሞ በቅርቡ ይመረቃል። መጽሐፉ አካል ጉዳተኛ ሆነው ተፅእኖ መፍጠር የቻሉ ሰዎች ግለ ታሪክን የያዘ ነው። በኢትዮጵያ ለመጀመሪያ ጊዜ ተፅዕኗቸው ከፍ ያለ የአካል ጉዳተኞችን እውቅና የሚሰጥ የሽልማት መርሀ ግብርም ከመጽሐፍ ምረቃው ጎን ለጎን ይካሄዳል።

ሰዓሊና መምህር ዓለም ከዚህም ያለፈ ራዕይ አላት። የስዕል ማስተማሪያ፣ ጋለሪ፣ የንባብ ማዕከሉንና የበጎ አድራጎት ሥራውን (አብረን ድርጅትን) በአንድ ሥፍራ ለማዋሀድና አቀናጅታ ግዙፍ የስብዕና ማዕከል የመክፈት እቅድ አላት። መንግሥት የሀሳቧ ተጋሪ በመሆን ተገቢውን ሥፍራ በማመቻቸት እንደሁልጊዜው ትብብር እንዲያደርግላትም ትጠይቃለች።

ሰዓሊና መምህር ዓለም ባለፉት በርካታ ዓመታት ለትውልድ ምሳሌ የሚሆኑ ሥራዎችን ለሀገሯ አበርክታለች። ለውለታዋ ልዩ ልዩ እውቅናዎችንና ሽልማቶችን አግኝታለች። በአውስትራሊያ በተካሄደ ውድድር ላይ ከአፍሪካ አንደኛ በመውጣት በማሸነፍ እውቅናን አግኝታለች። በጀርመን ሀገር በተካሄደ የአፍሪካን ካላንደር ውድድር አሸናፊና ተሸላሚ ነች። የባሕልና ስፖርት ሚኒስቴርን ጨምሮ ልዩ ልዩ የሀገር ውስጥ ሽልማቶችና እውቅናዎችን ማግኘት ችላለች። በአሜሪካን ኤምባሲ፣ የአፍሪካ አንድነት ድርጅትን ጨምሮ በሌሎች ዝግጅቶች ላይ እየተገኘች የሕይወት ልምዷን በማጣቀስ ለሴቶች፣ ለአካል ጉዳተኞችና ወጣቶች ሥልጠናዎችን ትሰጣለች።

### የዓለም መልዕክት

‹‹መንቀሳቀስ የምችለው በዊልቸር ነው›› የምትለው የዛሬው የሕይወት ገፅታ እንግዳችን፤ አካል ጉዳተኝነት የአካል አለመንቀሳቀስ፣ ማየት አለመቻል ሳይሆን የአስተሳሳብ ችግር እንደሆነ ትናገራለች። አካል ጉዳተኛ የምትለው ቅንነት የሌለውን፣ ሀገሩን ማገልገል የማይችለውን፣ እራስ ወዳድ የሆነና ኃላፊነቱን በአግባቡ የማይወጣውን እንደሆነ ትገልፃለች። በየትኛውም መንገድ ላይ በጠበበ አስተሳሰብ የሚኖር ሰው ለእርሷ አካል ጉዳተኛ እንደሆነ ታስባለች።

እርሷ እዚህ ስኬት ላይ የደረሰችው በመልካም ሰዎች እንደሆነ በመግለፅም ‹‹ሁሉም ኢትዮጵያዊ የሰዎችን ሕይወት ማቅናት የሚችለው በመልካምነትና በቅንነት መሆኑን ተረድቶ በሁሉም መስክ በኃላፊነትና በበጎነት መሥራት ይኖርበታል›› የሚል መልእክት አስተላልፋለች።

# ፋልሴቶ- ነጩ የሙዚቃ ድልድይ

ሙሉጌታ ብርሃኑ

"የነጭና የሰይጣን መልካም የለውም:: በእጅ ከሰጠህ የጭንቅላትህን ሊነጥቅህ ፈልጓል ማለት ነው" ያለኝን ወዳጄን አልዘነጋውም:: በዚህ አስተሳሰብ የሚስማሙ አይጠፉም። ይህን ስል የነጭ ጥላቻ አለብን ማለት ሳይሆን ለሀገራችን ካለን ፍቅርና አሳቢነት የመነጨ ጥርጣሬን ከግምት በማስገባት ነው:: በርግጥ በነጭ የሆነው እንጂ ያልሆነው ምን አለና እንዲያ ቢታሰብ አይፈረድም። ይሁንና ልክ እንደዛሬው ዝነኞችን ዓይነቱ ቅንም አለና "ከስንዴ የተገኘህ ሰሊጥ አብረህ ተወቀጥ" ብለን በጅምላ መፈረጅ አያስችለንም::

**መጥፎ መጥፎ ሽርቅ፤**
**ደግ ደጉን ሸምጥልን፤**
**ሚነጅሰን ሳይሆን፤**
**የሚመጅነንን::**

ማለት ለዚህ ሰው ነው:: ይህም ሰው ፍራንሲስ ፋልሴቶ ነው:: ሐበሻ ሳይሆን ፈረንጅ ነው:: ኢትዮጵያዊ ሳይሆን እልም ያለ ፈረንሳዊ ነው:: ከሙዚቃ ጨረቃ ጋር ብዙ ዓለማትን ዞሯል:: ጥንቅቅ ያለ የሙዚቃ ሊቅ ነው:: ሙዚቃን በጆሮው አሸትቶ፣ በልቡ ማጣጣም የሚችል ነው:: ከቀመሰውና ካጣጣመው ሁሉ ግን እንደ ኢትዮጵያ ሙዚቃ አንጀቱን ያራሰው የለም:: ለዚህም ነው ሀገራትን እያቆራረጠ መዝመቱ:: እየሰማው አድጎ እየሰማው ላለውና ለሚያውቀው የሀገሩ ሙዚቃ ያልሆነውን፣ ምን ጆሮው ቢቆረጥ ትርጉሙን ለማያውቀው የኢትዮጵያ ሙዚቃ ልቡን ከፍቶ በፍቅር ከነፈበት:: የወደቁትን የትናንትናዎቹን አበቦች አንስቶ ለዛሬ ፍሬዎች አደረጋቸው:: ድንገት ጆሮው የገባች አንዷት ሙዚቃ መላ ሰውነቱን አንዝራ፣ በፍቅር አነሆለለችው::

ለዚህ ሁሉ መነሻ ከሆነው የነጩ ሰው ፍራንሲስ ፋልሴቶ አጋጣሚ ስንጀምር፣ ከሆነው ነገር በፊት የሆነው ታሪኩ እንዲህ ነው...ዘመን ሲወሳ መቼም ያቺ ዘመን ከሁላችንም የትውስታ ማህደር ውስጥ ተሰንቅራ ዛሬም አለች:: ወርቃማው የሙዚቃና የኪነ ጥበብ ዘመን ጭምር ናትና:: እሷም በ1960ዎቹና 70ዎቹ አጋማሽ መካከል ተንፈላሳ እናገኛታለን።

የቁጥሯ ነገር በትክክልም ተሰልቶና ተቆጥሮ ባይሰፍርም የወርቃማዋ ዘመን ወርቆችን ጭና፣ በ70ዎቹ ድንበር አልፋ አጋማሹ ላይ የደረሰችው መርከብ ውጥንቅጧን ያወጣው እክል ገጥሟት ነበር:: በውጥንቅጡ መሃል የተፈጠሩ መልካም ነገሮች እንደነበሩ ባይካድም ወርቃማውን ለጫነች መርከብ ግን በመሃል የዘመን ቤርሙዳ እንዲፈጠር ሆኗል:: በሶሻሊስት ርዕዮተ ዓለም የተዋከበው ፖለቲካና ሌሎችም ውስጣዊና ውጫዊ ማዕበሎች እየተንቀሳቀሱ መርከቧን ከኤርትራም፣ ከሙት ባህርም አንኮታኩተዋታል:: አባላቱ ሁሉ የወርቃማውን ዘመን የመጨረሻ ወርቃማ ጽዋ ከተጎነጩ በኋላ ገሚሱ በስደት፣ ገሚሱም በሞትና በድብርት ከሆነው ሁሉ ቀሪውም ቤርሙዳውን ተሻግሮ ለማስታወሻነት ታየ::

ይሄን ሁሉ ያነሳነው ነጩን ፋልሴቶ ዘንግተን አይደለም፤ ይልቁንስ ይህ ክስተት ከእርሱ መነሻ ጋር የሚገጣጠም ነገር ስላለው ነው:: የወርቃማው ዘመን መጨረሻና የእርሱ መጀመሪያ ሳይተዋወቁ የተላለፉ ናቸው ለማለት አይቻልም:: በአንድም ሆነ በሌላ ያ ታሪክ የርሱም ታሪክ ሊሆን ነው:: እንዴት? ካስባለን... የ1970ዎቹ አጋማሽ ብርጭቆ አንስተው እንኳን "ቺርስ ለሶሻሊዝም" የሚባባሉበት ጊዜ ነበር:: እያንዳንዱ ሰው፣ ሁሉም በየሙያው መስክ አንድ አዲስ ነገር ይዞ ለመምጣትና ለመሥራት ተጣምሮ ወደተባለበት ሁሉ የሚሯሯጥበት እንጂ ቁጭ ብሎ ስለቀድሞ ትዝታው ለማሰብም ሆነ ለማስቀጠል የሚችልበት አልነበረም:: ሁሉም ነገር አዲስ፣ ብዙ ነገርም የማፍረስና የመገንባት አብዮት ነበር::

ይህ እጣፈንታ ለኪነ ጥበብም ደረሰና ለመርከቧ ተንሳፎ መቅረት ምክንያት ሆነ:: እኚያን የሙዚቃ ሸክላዎች እያፈራረቁ ማጫወቱ ከአሸሼ ገዳሜ እንዳይቆጠርበት የፈራም ብዙ ነው:: ቀድሞ ሲደመጡ የነበሩ ሙዚቃዎች ሁሉ በገጠር ከተማው ድር ያደራባቸው ጀመረ:: ... እያሉም ጉዟቸው ወደመጥፋት ነበር:: ለእንስፍስፏ የጥበብ አንጀት፣ አትሙቺ ያላት ሙዚቃ ነብስ የጣለው ደጉ ሰው፣ ነጩ ፈረንጅ ፋልሴቶን አንከላውሶ ከፈረንሳይ አስነስቶ አዲስ አበባ ምድር ላይ ጣለው:: ያቺ "መላ መላ" ናት ለዚህ ያበቃችው:: አሁንም ዕድሜ ለርሷ! ዕድሜ ለማህሙድ አህመድ!...



**በ1989ዓ.ም መባቻ ላይ አስቀድሞ በነበሩት የማህሙድ ሥራዎች ቀሪዎቹንምበማከል፣ ከሙላቱ አስታጥቄና ሙሉቀን መለሰ እንዲሁም የሌሎችንም ሰብሰብ አድርጎ "ኢትዮጲክስ" የተሰኘውን ማህደረ ሙዚቃ ለዓለም ገለጠው**

ጊዜው በ1970ዎቹ መጀመሪያ ነው። ነጩ ሰው ፈረንሳዊው ፋልሴቶ አዲስ አበባን ሳይረግጥ በፊት በሀገሩ ውስጥ "ፖይተርስ" በሚሏት ትንሽ ከተማ ውስጥ እየኖረ በአንድ ለትርፍ ባልተቋቋመ ድርጅት ውስጥ ይሠራ ነበር:: የሚኖርባት ፖይተርስ ከፓሪስ አንጻር ስትታይ ምንም እንኳን ትንሽና ጥቂት ሕዝብ የነበራት ብትሆንም የዋዛ ግን አልነበረችም:: በአዲስ አበባ መነጽር ቢመለከቷት ውቤ በረሃን ማለት ናት:: በከተማዋ ውስጥ የሚደገሰው የሙዚቃ ድግስ ሽታው ፓሪስ ላይ ያውዳል:: የዚህ ድግስ አዘጋጆች ደግሞ ፍራንሲስ ፋልሴቶና ሌሎች ወዳጆቹ ናቸው::

ፖይተርስም በነፋልሴቶ ሙዚቃዎች ቀውጢ ነበረች:: ታዲያ ግብዣው እዚያው ለዚያው የሆነ አልነበረም:: በአውሮፓ ቢሉ በአሜሪካ በጊዜው አሉ የተባሉ ሙዚቀኞች ሁሉ የሚሳተፉበት ነው:: ከእኚህ ትልልቅ የሙዚቃ ፈርጦች ጋር ሲቀራረብና ሲጋብዛቸው የፋልሴቶ ትልቁ ዓላማው ታዳሚዎቹን ለማስደሰት በማሰብ ብቻ አልነበረም:: ይልቁንስ በሌላ ሀገራት ውስጥ ያለውን የሙዚቃ ጥበብ ለማወቅና ምርምሮችንም ስለማድረግ እያሰላሰለ ነበር::

የነጩን ሰው የሙዚቃ እጅና እግር ያበቀለች፣ ያቺ የሸክላ ሙዚቃ አጋጣሚ የተፈጠረችው እንዲህ ነበር:-

እንደሌላ ጊዜው ሁሉ ከውጭ የተጋበዙ እውቅ አቀንቃኞች ለዝግጅት ተሰናድተዋል:: ሁሉም ቦታ ቦታውን እየያዘ ቀውጢው የፖይተርስ ከተማ ጨረቃ ቁልቁል ማዘቅዘቅ ጀምራለች:: ገና ከጅምሩ መዓዛው የተለየ ድግስ መደገሱን የሚያሳብቅ ነበር:: በድግሱ ለመገኘት ትኬት ቆርጦም፣ ተገፋፍቶም ለመግባት የሚተናነቀው ብዙ ነው:: ወደዚያ የድግስ ስፍራ ከመጡ ሰዎች ሁሉ የተለየው ሰው ግን አንድ ነገር ይዞ መጣ:: ሲያዩት እንደነገሩ የሚመስል ግን ደግሞ ውስጡ ሌላ ተአምር የያዘ ሸክላ ነበር:: ያ ሰው ሸክላዋን በእጁ እንደያዘ፣ በሰው መሃል አልፎ፣ ፋልሴቶና ሌሎች እንግዶች ሰብሰብ ብለው ወዳሉበት አመራ:: ወደ ፋልሴቶ ጠጋ ብሎም "እንካ ይቺን ነገር ስማት" ሲል እንደ ልዩ መልእክት አቀበለው:: ፋልሴቶ ምንም ጊዜ ለማባከን አልፈለገም:: እየተጣደፈ ሄዶ የሸክላውን ሲዲ ማጫወቻው ላይ አኖረው:: ጠቅ! አደረገና እያጠነጠን ድምጽን እስኪያሰማ አፍታ ጠበቀው:: ማጫወቻው ቴፐ ድምጽ አወጣ...

**"ኧረ መላ መላ፤**
**መላ መላ**
**"ኧረ መላ መላ..."**

ገና በመጀመሪያው መግቢያ የሰማውን ለማመን አቃተው:: የማያውቀውን ሰምቶ ለዘመናት ሲፈልገው የኖረውን ነገር እንዳገኘ ያህል ልቡ በሀሴት ሲመታ ታወቀው:: ሲከንፍ ተመልሶ መጣና አብረውት ለነበሩት ወዳጆቹና የሙዚቃ ባለሙያዎች አስደመጣቸው:: እነርሱም ሙዚቃ እንጂ ስለምን እንደሆን ባያውቁም አጃኢብ ነው! አሉ:: አሁንም ጊዜ ሳያጠፋ፣ ሸክላውን ሬዲዮ ጣቢያ ለሚሠራ ለአንድ ጋዜጠኛ ላከው:: በአይቤክስ ባንድ ተሠርቶ የነበረው የማህሙድ አህመድ "ኧረ መላ መላ" የሬዲዮ ሞገዱን ሳይቀር አነዘረው:: የሰማ ሁሉ "ኧረ ከወዴት አመጣችሁት?" ነበር ጥያቄው::

እንዴት እንደመጣ እንጂ፣ ከወዴት እንደመጣ ፍራንሲስ ፋልሴቶም አያውቀውምና ምላሹ እርሱም ጋር አልነበረም:: ግን ሰማይ ቧጦም ቢሆን የዚህን መነሻ ምንጭ ማግኘት ግዴታው ነበር:: አንድም ጊዜ የመርገጥ አጋጣሚውን አላገኘምና አፍሪካን የሚያውቀው በስም ብቻ ነው:: ስለአፍሪካ ሙዚቃም ጫፍ ጫፉን ያውቃል:: "ኢትዮጵያ" ስለምትባል ሀገር ግን ከዚያ ቀደም በካርታ ላይ ስለመኖሯ እንኳን የሚያውቀው የለም:: የማያውቃት ሀገር፣ በማያውቀው ቋንቋ ልቡን ያስፈነደቀችውን ሀገር ሳያይ ነግቶ ቢመሽ ሞት ነውና ሻንጣውን ብድግ አድርጎ ሊነሳ ሲል ግን ሌላ አንድ ነገር ገጠመው:: ኢትዮጵያ አርማዋን ቀይራ በሶሻሊስትነት ተጠምቃ ነበርና ከኢምፔሪያሊስት ሀገር ዘሎ እንዲሁ መግባቱ የማይታሰብ ነበር:: ዋጋ ከፍሎም ቢሆን ሊኖሩት የሚችሉትን አማራጮች ሁሉ ለመጠቀም ሲያስብ ራሺያን አማላጅ አድርጎ በርሷ በኩል ለመምጣት ወሰነ:: ከፈረንሳይ ራሺያ፣ ከራሺያም ወደ ናፈቃት ሀገር ኢትዮጵያ ገባ::

ፋልሴቶና አዲስ አበባ። ከአዲስ አበባ ሰማይ ላይ፣ ከቦሌ አውሮፕላን ጣቢያ ከወረድክበት ሰዓት አንስቶ የነበረው ነገር እንደምን ነበር? ብላችሁ ብትጠይቁት፤ "እሱንስ አታንሱት፣ ብቻ አይነገር..." ብሎ ዝም ባላችሁ ነበር:: ለዚህ ምክንያቱ እንግዳ ሰው ሲገጥሙት የነበሩት አስቸጋሪ ሁኔታዎች ናቸው:: ለወትሮ እንግዳ በእቅፏ የምትቀበለው እናት ሀገር ኢትዮጵያ፣ በጊዜው የነበረው የፖለቲካ አየር አውሎ ንፋሱ የበረታበት ነበር:: ከአየር ማረፊያው ብቅ ካለበት ቅጽበት አንስቶ በየፌርማታው፣ መንገዱ ላይ ያለው የፍተሻ አጀብ ውስጡን ሳይቀር ተፈታትኖታል:: ይዞ የሚንቀሳቀሰው ካሜራና መቅረጸ ድምጽ የተከለከሉ በመሆናቸው ሌላ ጣጣ ሆነበት::

አመጣጡና ዋነኛ ግቡ "መላ መላ" ሲል በሙዚቃው ልቡን ያሸፈተውን ማህሙድ አህሙድን ማግኘት ነበርና የማህሙድ ያለህ ማለቱን ጀመረ:: ከዚህም ከዚያም ፈልጎ አስፈልጎ በመጨረሻም አገኘው:: ሁለቱም ከአንድ ጠረጴዛ ፊት ተቀምጠው አወጉ:: ፋልሴቶም የፖይተርስን ግብዣ ለማህሙድ አቀረበለት:: እንኳንስ ለእንዲህ ዓይነቱ ለሚጠቀምበት ዕድል ቀርቶና ለሌላ ለማያገኝበት ነገርም ቢሆን እምቢታን የማያውቀው ትሁቱ ማህሙድም በእሺታ ተቀበለው:: የዓለም ክዋክብት በደመቁባት የፈረንሳይዋ ፖይተርስ መድረክ ላይ ፍንትው ለማለት ተመካክረው ጨረሱ:: በአንድ ወቅት ላይ ጋዜጠኛዋ ብሌኔ "ያንን አጋጣሚ፣ በዚያን ሰዓት ይሰማህ የነበረውን ስሜት ታስታውሰዋለህ?" ስትል በእንግሊዝኛ አፍ ጠየቀችው:: ፋልሴቶ ቃል ከማውጣቱ አስቀድሞ፣ በትዝታ ቅጽበት ሄድ መለስ ካለ በኋላ ነበር "እንዴታ! አሁን ድረስ ዓይኔ ላይ ነው:: አሁንም ድረስ ከውስጤ እንዳለ አለ" ሲል መለሰላትና አሁንም በአፍታ ትዝታ ደፍቆ ወጣ::

ፋልሴቶ የመጣበትን የመጀመሪያ ጉዳዩን ከማህሙድ ዘንድ አሳክቷል:: ግን እቅዱ ማህሙድንና የማህሙድን ሥራዎች ማግኘት ብቻ አልነበረም:: ረዘም ባለ ቆይታ ውስጥ በሁሉም የኢትዮጵያ መንደሮች ውስጥ እየዞረ፣ ሁሉንም የኢትዮጵያን ባሕልና ሙዚቃ ማጥናት ነበር እቅዱ:: ሆኖም ግን ከመጀመሪያው አንስቶ ምቾት የነሳው የፖለቲካው አቀበት አሁንም አልሆንልህ አለው:: ወደ ባለሥልጣናቱ ተመላልሶ እቅዱን ቢተርክላቸውም በጄ! ሳይሉት ቀሩ:: ይህን ለማድረግ እንደማይችል ደጋግመው ነገሩት::

ከተወሰኑ ጊዜያት በኋላም እቃውን ሸካክፎ፣ ከአስቸጋሪው ሁኔታ ውስጥ እንኳን ይባስ ከመጀመሪያው ፍቅሩ የጠነከረበትን የኢትዮጵያን ባሕልና ሙዚቃ ዞሮ በናፍቆት እየተመለከተ ወደ ሀገሩ ፈረንሳይ ተመለሰ:: ቅሉ እንዲህ ቢሆንም ሲሄድ ግን ባዶ እጁን አልነበረም:: በተቻለው ሁሉ እያነፈነፈ፣ ከያሉበት ያደናቸውንና አሁን እንድናወራለት ያደረጉትን የተወሰኑትን የሙዚቃ ሸክላዎች ይዞ ነበር የተመለሰው::

በእጁ የገቡት የሙዚቃ ሸክላዎች ቀላል የሚባሉ አልነበሩም:: የምርምር ሥራውን ለመጀመርም በትንሹም ቢሆን በቂ ነበሩ:: ቀጣይ ለመሥራት ላሰበው ሥራም ለጅምር የሚሆኑት ያህል ናቸው:: ነገር ግን ፋልሴቶ ስለሙዚቃና ሙዚቀኛ ጠንቅቆ የሚያውቅ ሰው ነው:: አገኘሁ ብሎ ያለፈቃድ፣ በሌሎች ልፋት እንዳሻው ለማድረግ እንደማይችል ያውቀዋል:: በጣም ተጨንቆበትም ነበር:: ሸክላዎቹ ግን አንድ መላውን ሹክ ብለው፣ ወደ አንድ ሰው አመለከቱት::

በአብዛኛዎቹ ውስጥ አሳታሚ ሆኖ ስሙ ወደሰፈረው አምሀ እሸቴ ዘንድ ነበር:: ሲያጠያይቅ አምሀ የሚገኘው አሜሪካን ውስጥ መሆኑ ተነገረው:: ልፋቱ ሳይታየው ይበልጥ ደስ አለው:: ጊዜ ሳያባክን ተነስቶ፣ አምሀን ፍለጋ አሜሪካ ገባ:: እምብዛም ሳይንከራተት ዲሲ ውስጥ አገኘውና ያሰበውን ነገር አዋየው:: አምሀ ግን ሥራው የበርካታ ሙዚቀኞች እንደመሆኑ ብቻውን ለመወሰን እንደማይችልና ይህን ቢያደርግ እንደሚያስወቅሰው ገለጸለት:: ሆኖም ምንም ለማድረግ አልችልም ብሎ ሳይተወው ወደ ኢትዮጵያ ተመልሶ ከሌሎች ጋር አብሮ እንደሚመክርና የደረሱበትን እንደሚያስታውቀው ነግሮት ተለያዩ::

"ጊዜ ለኩሉ" ይለዋል የሀገሬ ሰው:: ለሁሉም ጊዜ አለውና የሚሆነውም በጊዜው ነው:: ፖለቲካ ፖለቲካን፣ ጊዜም ጊዜን ገርስሶ ከሀገሬው ሰማይ ጥላ ስር ሁሉም ነገር ተለዋወጠ:: የደርግ መንግሥት ዙፋኑ በኢህአዴግ ተነጥቆ 1983ዓ.ም የሚነፍሰው ነፋስ ሌላ ነበር:: ቀደም ሲል ከመርከቧ ተጓዦች የነበረው አምሀ እሸቴም ከ19 ዓመታት በኋላ ተመልሶ ሀገሩ ለመግባት በቃ:: ይህን የሰማ ፋልሴቶም ተከትሎ ከፈረንሳይ ከተፍ አለ::

ዲሲ ላይ መክረው እስቲ ጊዜ እስኪፈታው ተባብለው የነበሩትን ነገር ለመጀመርም መልካሙን የጊዜ አጋጣሚና ሁኔታ ፈጠረላቸው:: የተገናኙት ከምንጩ ላይ ነውና የሥራዎቹን ባለቤት ለማግኘትም ዳገት የሚሆን ምንም ነገር አልነበረም:: ከዳግም ምክክር በኋላም አምሀን የቀኝ እጁ አድርጎ አንድ ሲል ፋልሴቶ ሥራውን ጀመረ::

በ1989ዓ.ም መባቻ ላይ አስቀድሞ በነበሩት የማህሙድ ሥራዎች ቀሪዎቹንም በማከል፣ ከሙላቱ አስታጥቄና ሙሉቀን መለሰ እንዲሁም የሌሎችንም ሰብሰብ አድርጎ "ኢትዮጲክስ" የተሰኘውን ማህደረ ሙዚቃ ለዓለም ገለጠው:: በዓለም ዙሪያ ባሉ ሚዲያዎች ሁሉ እኚህን የኢትዮጵያን ሙዚቃዎች ተቀባበሉት:: ከሙዚቃ ተንታኞች ዘንድ ሊገጥመኝ ይችላል ሲል የፈራው ትችትም ሳይሆን ቀረና በምትኩ አድናቆትና ዝነኝነት ጎረፈ:: በሰሟቸው የኢትዮጵያ ሙዚቃዎች ልባቸው መለከፉን የሚናገሩ አድማጮችም በዙ:: በጊዜው አሉ ከተባሉት ዓለም አቀፍ ፈርጦች መካከል አንዱ የሆነው፣ ሙዚቀኛው ኤልቪስ ካስቴሎ ሳይቀር ይሄስ የጉድ ነው! ሲል መደነቁን ከፍ አድርጎ ተናገረው:: ለፋልሴቶም ሆነ ለኢትዮጵያ ሙዚቀኞችም ትልቁን የዓለም በር የከፈተ አጋጣሚ ሆነ::

ከዚህ በኋላም ያለምንም እረፍት በየስርቻው ሁሉ እየገባና እያነፈነፈ ሙዚቀኛው ሳይቀር የዘነጋውን ሙዚቃ ማደኑን ተያያዘው:: ለማግኘት አዳጋች ከሆነው የደቡብ ክፍል ድረስ እየወረደ ከወደ ኮንሶ መንደር ሁሉ አልቀረም:: የኢትዮጵያ ሙዚቃዎችም እየተከታተሉና እየተግተለተሉ ወደ ዓለም ጆሮ መትመማቸውን ቀጠሉ:: "Abyssinia swing" ሲልም በመጽሐፍ ሰድሮታል::

ፋልሴቶ በትውልዱ ፈረንሳዊ፣ በማንነቱ ነጭ ነው:: ይሁንና በሥራው ግን ኢትዮጵያዊ ልንለው ግድ ሆኗል:: ምናልባትም ንፍገት ብናበዛበት እንኳን አንድ ኢትዮጵያዊ የጥበብ ሰው ለእናት ሀገሩ አበርክቶ፣ ውለታን ውሎላታል ብለን በትንሹ ልንነግርለት ከምንችለው ጋር በሚነጻጸር መልኩ ሠርቷልና:: ዛሬ ላይ የምናደምጣቸውን አብዛኛዎቹን የወርቃማ ዘመን ወርቆችን ስናጣጥም "እድሜ ለፋልሴቶ! እድሜ ለነጩ ሰው!" እያልን:: ማንም ይሁን ምን... ነጩ ሰው ፍራንሲስ ፋልሴቶ ለኢትዮጵያ ሙዚቃ ድልድይ ሆኖ ከዓለም አድማጮች ጋር እንዲደርስ መልካሙን ሠርቶልናልና እናመሠግናለን!! ረዥም ዕድሜና ጤና ለሰማንያ ዓመቱ አዛውንቱ ፍራንሲስ ፋልሴቶ!!

ኢኮኖሚ

# ባህልና ቱሪዝም

# ተገልጠው ያልታዩት - የጋምቤላ ክልል የቱሪዝም መስህቦች

ኃይሉ ሣህለድንግል

የጋምቤላ ብሔራዊ ክልል ሊጎበኙ በሚችሉ ሀብቶቹ በእጅጉ ይታወቃል፤ ወደ ክልሉ ዋና ከተማ ጋምቤላ በየብስ ወይም በአውሮፕላን በመጓዝ እነዚህን የተፈጥሮ፣ ሰው ሠራሽና ባሕላዊ የቱሪዝም ሀብቶች መጎብኘት ይቻላል።

ክልሉ በተለይ በተፈጥሮ ሀብቶቹ በእጅጉ ይታወቃል። ለጋምቤላ ብሔራዊ ፓርክ ጥበቃና ልማት ለማድረግ መንግሥት፣ የዱር እንስሳት ጥበቃ ባለሥልጣንና በአፍሪካ 12 ሀገሮች 23 ፓርኮችን በማስተዳደርና በማልማት ሥራ ላይ ከተሰማራው መንግሥታዊ ያልሆነ ድርጅት ጋር በቅርቡ ስምምነት በተፈጸመበት እለት እንደተጠቆመው፤ የጋምቤላ ክልል ለቱሪዝም አገልግሎት ሊውሉ በሚችሉ በርካታ የተፈጥሮ ሀብቶች የበለጸገ ነው።

ከእነዚህ የተፈጥሮ ሀብቶች መካከል የሚጠቀሰው አብዛኞቹን የተፈጥሮ ሀብቶችን አካቶ የያዘው ይሄው የጋምቤላ ብሔራዊ ፓርክ ነው። ፓርኩ በሚሊዮኖች የሚቆጠሩ የዱር እንስሳትና አእዋፋት እንዲሁም በርካታ ወንዞች፣ ሐይቆች፣ ኩሬዎችና ፏፏቴዎች ይገኙበታል።

በመድረኩ ላይ የተገኙት የክልሉ ርእሰ መስተዳደር ወይዘሮ አለሚቱ ኡሞድ ከጋዜጠኞች ለቀ‹ረቡላቸው ጥያቄዎች ምላሽ በሰጡበት ወቅት የጋምቤላ ብሔራዊ ፓርክ ከሌሎች የሀገሪቱ ፓርኮች ጋር ሲነጻጸር የጋምቤላ ክልል ሙሉ ለሙሉ ፓርክ ነው ሊባል እንደሚችል ገልጸዋል። ሌላ አንድ የክልሉ ባለሥልጣን ሰሞኑን ከገለጹት መረዳት እንደቻልነውም፤ በክልሉ አንድ ዞን ያለው የደን ሀብት ሲታሰብ ዞኑን ሙሉውን ፓርክ ሊያሰኘው ይችላል።

የጋምቤላ ብሔራዊ ፓርክ ከደቡብ ሱዳን ሁለት ፓርኮች ጋር የሚዋሰንና የዱር እንስሳቱም ወቅቶችም መሠረት ባደረገ መልኩ አንዴ በኢትዮጵያ ሌላ ጊዜ በደቡብ ሱዳን እንደሚገኙ ከክልሉ ያገኘነው መረጃ ያመለክታል። ይህ ሁኔታም የዱር እንስሳት ድንበር የላቸውም ለሚለው እንድ ማሳያ ተደርጎ ይወሰዳል።

በጋምቤላ ክልል ባሕልና ቱሪዝም ቢሮ የቱሪዝም መዳረሻና ጥናት ልማት ከፍተኛ ባለሙያ አቶ ደርባቸው ሽዋለም እንደሚሉት፤ ክልሉ ለቱሪዝም መዳረሻነት ሊያገለግሉ የሚችል የተፈጥሮ፣ ሰው ሰራሽና የባሕል ሀብቶች ባለጸጋ ነው።

የጋምቤላ ቱሪዝም ሲነሳ በዋናነት የሚጠቀሰው የጋምቤላ ብሔራዊ ፓርክ መሆኑን ጠቅሰው.፣ ፓርኩ የሀገሪቱ ግዙፉ ፓርክ መሆኑን ተናግረዋል። ይህ ፓርክ በውስጡ አያሌ የዱር እንስሳትና አእዋፋትን አቅፎ ይዟል። በያዛቸው በርካታ የእንስሳት እና የአሳ ዝርያዎችም በእጅጉ ይታወቃል ሲሉም አብራርተዋል።

እሳቸው እንዳሉት፤ የዱር እንስሳቱ ክረምት ላይ ከኢትዮጵያ ወደ ደቡብ ሱዳኑ ቦማ ብሔራዊ ፓርክ ይሰደዳሉ፤ ወደ ደቡብ ሱዳን ከሚገቡት እንስሳት መካከል የአንቴሎፕ ዝርያዎች ይገኙበታል፤ ሌላው ብርቅዬ የሚባለው የአጋዘን ዝርያ ነው። እንስሳት በበጋ ወቅት፣ ውሃ ሲጎድል ወደ ጋምቤላ ብሔራዊ ፓርክ ይመለሳሉ።

ሌላው የክልሉ የተፈጥሮ ቱሪዝም መዳረሻ በመዥንግ ብሔረሰብ ዞን ሜንጊሽ ወረዳ የሚገኘው ቡሬ ሀይቅ ይጠቀሳል፤ በኢትዮጵያ ውስጥ ከሚገኙ አምስት በዩኔስኮ ከተመዘገቡ አያሌ ብዝሀ ሕይወቶች /ባዮስፌሮች / ከሚገኙባቸው ባየስፌሮች መካከል የጋምቤላው የመዥንግ ባዮስፔር አንዱ ነው። ባዮስፌሩ በርካታ የዱር እንስሳት፣ አእዋፋት፣ ወንዞችና ፏፏቴዎች ይገኙበታል።

አቶ ደርባቸው እንዳብራሩት፤ ክልሉ ባሮ፣ አኮቦ፣ ጊሎና አልዌሮ የተሰኙ ክረምት ከበጋ የሚፈሱ አራት ትልልቅ ወንዞች ባለቤት ነው፤ በርካታ ኩሬዎችና ረግራጋማ ቦታዎች መገኛም ነው፤ በኢታንግ ወረዳም ሀይቅ በርካታ የአሳ ዝርያ የሚገኝበት ትልቅ ሀይቅ አለ። ታዬ የሚባል ሀይቅም አለ።

ሌላው የክልሉ መስህብ የታታ ሀይቅ ነው፤ ከዚህ ትልቅ ሀይቅ አቅራቢያ የጊሎ ወንዝ ይገኛል፤ የአኙዋክ ብሔረሰብ አባላት በዚህ ወንዝ በመጠቀም በባሕላዊ መንገድ አሳ ያስግራሉ። ሀይቁ ከጋምቤላ ከተማ 119 ኪሎ ሜትር ርቀት ላይ ይገኛል።

ከፍተኛ ባለሙያው በአበቦ ወረዳ የሚገኘው የአልዌሮ ግድብ ለቱሪስት መስህብነት እየዋለ እንደሚገኝ ተናግረዋል። ይህ ሰው ሠራሽ ሀይቅ ለመስኖ ልማት በሚል በደርግ መንግሥት በተገነባ ግድብ የተፈጠረ ሀይቅ ነው



ከክልሉ የቱሪዝም መስህቦች መካከል በጋምቤላ ብሔራዊ ፓርክ የሚገኙት የዱር እንስሳት ይጠቀሳሉ፤

ሲሉ አመልክተው፣ ከጋምቤላ ከተማ 47 ኪሎ ሜትር ርቀት እንደሚገኝና በርካታ የአዞና የአሳ ዝርያዎች ያሉበት መሆኑንም አመልክተዋል።

ክልሉ በአሳ ሀብት ዝርያዎቹም እንደሚታወቅ ተናግረዋል፤ በክልሉ ወደ 102 ዓይነት የአሳ ዝርያዎች ይገኛሉ። ከሀገሪቱ የአሳ ዝርያዎች 75 በመቶው በዚህ ክልል እንደሚገኙ ይናገራል። ከእነዚህ ውስጥ ናይል ፐርች የሚባለው የአሳ ዝርያ በክልሉ ይገኛል፤ አሳው ከ100 እስከ 110 ኪሎ ይመዝናል ሲሉም አብራርተዋል።

ባሮ ወንዝ ሌላው የቱሪስት መዳረሻ ነው፤ ከተማዋን ለሁለት ከፍሎ ያልፋል፤ ድልድዩ 315 ርዝመት 15 ስፋት 12 ሜትር ጥልቀት አለው። የአግዜር ድልድይ የሚባል ለቱሪስት መስህብ ሊሆን የሚችል ሥፍራም በክልሉ ይገኛል። እንግሊዞች ከኢትዮጵያ መንግሥት ጋር በተመባበር የገነቡት ታሪካዊ ወደብም ሌላው መስህብ ሊሆን የሚችል ሲሆን፣ በሀገሪቱ የውሃ ላይ ትራንስፖርት ታሪክ ሲነሳ የጋምቤላው የባሮ ወንዝ አብሮ ይጠቀሳል። አሁን በእዚህ ወንዝ ላይ የጀልባ ጉዞ ይደረጋል።

ባሕላዊዎቹን ስንመለከት ደግሞ የክልሉ ነባር ብሔረሰቦች የሆኑት የአኝዋክ፣ ኑዌር፣ መዠንገር፣ ኮሞ፣ ኑዌርና አፓና ብሔረሰቦች አኗኗር፣ ባሕላዊ ቁሶች፣ ዘፈኖችና ውዝዋዜዎች እና ሌሎች ባሕላዊ ሥርዓቶች የቱሪስቶችን ቀልብ የሚስቡ ናቸው።

በጋምቤላ ከተማ የተለያዩ መካነ መቃብሮች በቅርስነት ተይዘዋል። ከእነዚህም መካከል የኮንጎና ቤልጂየም ወታደሮች የተቀበሩት ስፍራ አንዱ ነው፤ ከ1900 እስከ 1941 ድረስ አርመኖች ግሪኮች አረቦች የተቀበሩበት ስፍራም አለ። እነዚህም ለቱሪስት መስህብ በመሆን ያገለግላሉ።

ከክልሉ የቱሪስት መስህቦች የለማ ተብሎ የሚታሰበው የቡሬ ሀይቅ መሆኑን ጠቅሰው፣ ሀይቁ ውብ ኢኮሎጂ እንዳለው፣ መጎብኘት ለሚፈልግም መንገድና ሎጅ የተገነባለትም መሆኑን ጠቁመዋል።

ኢታንግ ወረዳ የሚገኘው ሀይቅ መንገድ ያለውና ሊጎበኝ የሚችል መሆኑን ጠቅሰው፣ ባሮ ወንዝ ለመዝናናትም ለውሃና ስፖርትም ምቹ መሆኑን፣ የአልዌሮ ግድብም እንዲሁ ከጋምቤላ ከተማ ቅርብ ርቀት ላይ የሚገኝ፣ መንገድ ያለውና ሊጎበኝ የሚችል ነው።

ኮቪድ እና ከሰሜኑ ጦርነት ጋር ተያይዞ ክልሉን የሚጎበኙ ቱሪስቶች ቁጥር በተለይ የውጭ ሀገር ቱሪስቶች ፍሰት የተቀዛቀዘበት ሁኔታ እንደነበርም ጠቅሰው፤ የሀገር ቱሪስት ፍሰቱ ግን ተስፋ ሰጪ መሆኑን ገልጸዋል። በክልሉ መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች በብዛት ይንቀሳቀሳሉ፤ ኮንፈረንሶች በብዛት ይካሄዳሉ፤ ይህም ለሀገር ቱሪዝም ተስፋ ሰጪ መሆን አስተዋጽኦ እያበረከተ ነው ሲሉም አስታውቀዋል።

የክልሉን የቱሪዝም ዘርፍ የሚያነቃቁ ሥራዎች እየተሠሩ መሆናቸውን ጠቅሰዋል። በቅርቡ በአንዳንድ ቴክኒካል በሆኑ ጉዳዮች ላይ እገዛ የሚያደርግ ከቱሪዝም ሚኒስቴር የመጡ ባለሙያዎች በክልሉ እንደሚገኙ ገልጸዋል።

በባሮ ወንዝ ዳርቻ ላይ የመረጃ ማዕከልና ወጣቶች ተደራጅተው ወደ ሥራ የሚገቡበትን ሁኔታ ለመፍጠር ሰሞኑን ውል በመፈራረም ወደ ሥራ እየተገባ መሆኑንም አመልክተው፤ በዚህም የወጣቶች መዝናኛና የቱሪስት የመረጃ ማዕከል ይገነባሉ፤ አምስቱን የክልሉን ነባር ብሔረሰቦች ታሳቢ ያደረገ ዲዛይን ተሠርቶ የሚተገበር ይሆናል ብለዋል።

እሳቸው እንዳሉት፤ አካባቢውን የሚመስል የአምስቱን ብሔረሰቦች ባሕል የሚያንጸባርቅ መዝናኛ ማዕከል ይገነባል፤ ወጣቶች የሥራ እድል የሚፈጠርበትም ይሆናል። ስፓርታዊ እንቅስቃሴዎች የሚካሄድበት ሥፍራም ተያይዞ ይሠራል፤ ጋምቤላ በብስክሌትና ቮሊቦል ይታወቃል። የሚገነባው ማዕከልም ይህን ሁሉ ታሳቢ ያደረገ የወጣቶች የመዝናኛ ማዕከል ይሆናል። በጀቱ በቱሪዝም ሚኒስቴር የሚሸፈን ይሆናል።

የዛሬ ሳምንት አካባቢ የቱሪዝም ንቅናቄ ሳምንትን ምክንያት በማድረግ የሚመለከታቸውን አካላት ያሳተፈ መድረክ ምክትል ፕሬዚዳንቱ በተገኙበት መካሄዱንም ጠቅሰዋል። በክልሉ ለቱሪስቶች የሚሆኑ ማረፊያ ሥፍራዎች እንዳሉ ገልጸው፣ አንድ ባለኮከብ ሆቴል ብቻ እንዳለም ተናግረዋል። ይህም ለዓለም አቀፍ ቱሪስቱ የሚሆኑ መሠረተ ልማቶች ውስንነቶች ስለመኖራቸው እንደሚያመላክት አስታውቀዋል።

የጋምቤላ ብሔራዊ ፖርክን ለመጠበቅና ለማልማት ከአፍሪካን ፓርክስ ጋር የተደረገው ስምምነት የቱሪዝም ዘርፉን ምን ያህል ይጠቅማል በሚል የተጠየቁት ከፍተኛ ባለሙያው፣ ‹‹አፍሪካን ፓርክ በአንዳንድ ጉዳዮች ሳቢያ አካባቢውን ለቆ እስከወጣበት ጊዜ ድረስ በፈረንጆቹ 2000 አካባቢ የተወሰነ ሥራ ሠርቷል›› ሲሉ አስታውሰዋል። አፍሪካን ፓርክስ በአፍሪካ ፓርኮችን በማስተዳደር ልምዱ አለው ሲሉ ጠቅሰው፣ አሁን በደጋሚ መጥቶ ስምምነትም ተፈርሟል፤ አብዛኛው ሥራ ፓርኩን ማልማት ይሆናል። ሲሉ ገልጸዋል።

በኬንያ፣ በታንዛኒያ የቱሪዝም ዘርፉ የምጣኔ ሀብታቸው የጀርባ አጥንት ከሚባሉት መካከል ነው ሲሉም ጠቅሰው፣ የእኛም ፓርክ ከለማ በዚህ አይነት መልኩ ጥቅም ያስገኛል ብለዋል።

የጋምቤላ ብሔራዊ ፓርክን ለመጠበቅና ለማልማት ከአፍሪካን ፓርክስ ጋር የተደረገው ስምምነት ለክልሉ ቱሪዝም እንቅስቃሴ የሚኖረው ፋይዳ ከፍተኛ መሆኑ በወቅቱ ተጠቁሟል። የድርጅቱ የመጀመሪያ ሥራ የሚሆነው የመሠረተ ልማት ግንባታ እንደሚሆን ተጠቁሟል። ከዚያም ወደዋናው የማልማቱ ሥራ እንደሚገባም ተመላክቷል።

የክልሉ ርእሰ መስተዳደር ወይዘሮ አለሚቱ ኡሞድ ፓርኩ ከሌሎች ክልሎች ፓርኮች ጋር ሲነጻጸር ክልሉ በሙሉ በፓርክ ነው ብሎ መናገር ያስችላል ሲሉ ጠቅሰው፣ የትኛውም የክልሉ አካባቢ ብትንቀሳቀስ የዱር እንስሳት ታገኛለህ። በተለያዩ ምክንያቶች ከእነዚህ እንስሳት አንዳንዶቹ ከክልሉ የራቁበት ሁኔታ አለ፤ እንስሳቱ ከሰዎች እንቅስቃሴዎች በሚመነጩ ድምጾች ሳቢያ ሊርቁ ስለሚችሉ የእንስሳቱን አካባቢ ከሰው እንቅስቃሴ ነፃ ለማድረግ ይሠራል ብለዋል።

‹‹ፓርኩ በጣም ይጎበኛል። የሰላም ችግር ስለነበረ ጎብኚዎች ወደ ክልሉ ለመምጣት ተቸግረዋል። በተለይ ከታኅሣሥ ወር አንስቶ ጎብኚዎች በብዛት ወደ ክልል የሚመጡበት ሁኔታ አለ። ማንም ሰው ቢመጣ ፓርኩን መጎብኘት ይችላል ሲሉ ጠቅሰው፣ የመሠረተ ልማት ዝርጋታ አለመካሄዱንም ተናግረዋል። የተወሰኑ ቦታዎች ላይ መንገዶች አሉ። እነዚያን በመጠቀም መጎብኘት ይቻላል ሲሉም ጠቁመዋል።

ያንን ለማድረግ ክልሉ በቅድሚያ ማስተዋወቅ ላይ መሥራት እንደሚኖርበት ተናግረው፣ ጎብኚዎችን ለመሳብ በድህረ ገጾች፣ በመገናኛ ብዙሃን፣ በብሮሸሮች አማካይነት ፓርኩን ለማስተዋወቅ እየተሠራ ነው ይላሉ፤፡ መሠረተ ልማት መሥራት ከፍ አቅም በላይ ስለሆነ ነው በዚህ ላይ በትኩረት መሠራት ውስጥ የገባነው ብለዋል።

ድርጅቱ ለፓርኩ አስፈላጊ በሆኑ በአስተዳደር፣ ቁልፍ መሠረተ ልማቶች በሆኑት ህንጻዎች እንዲሁም ተሽከርካሪዎችና አውሮፕላን ማረፊያዎች አተኩሮ ይሠራል።

እሳቸው እንዳስታወቁት፤ አሁን በተደረሰው ስምምነት መሠረት መሠረተ ልማቱ ከተዘረጋ ማንም መጥቶ ፓርኩን መጎብኘት ይችላል፤ በክልሉ ፍሬያቸው እንደ መድኃኒትም ምግብም የሚያገለግሉ ዛፎች ሞልተዋል። በውሃ አካላትም አሳን ጨምሮ ልዩ ልዩ ብዝሀ ሕይወቶች አሉ። ወንዞቹ ክረምት ላይ ሲሞሉ ሜዳውን ሁሉ ያጥለቀልቃሉ፤ በጋ ሲሆን እየጎደሉ ሲሄዱ አሳ በብዛት ይመረታል። በዚህ ወቅት ያንን አሳ ለማጥመድ ማህበረሰቡ በብዛት ወንዞች አካባቢ ይሄዳል። ይህም ይህ ሀብት ለቱሪዝም መስህብነት ሊውል እንደሚችል ያመለክታል።

እንደ ክልል ደግሞ የጋምቤላ ከተማን የኮሪደር ልማት ለማካሄድ አቅደናል፡ አሁን ዲዛይን እየተሠራ ነው፤ በክልሉ ዋና ከተማ ጀምረን ወደ ወረዳዎች እንወርዳለን። በዚህ ላይ ውይይት እያደረግን ነው፤ ክልሉን ወደ በኋላ የመለሰው የሰላም መናጋት ነው። ሰላም ለማምጣት ሰፊ ጊዜ ሰርተናል፤ እንደ ሌሎች ክልሎች ልማቱን ለማስቀጠል የሚያስችል ሁኔታ እንደ ሰላሙ ሁሉ ክልሉ ከፈጠረ በኛ አቅም የሚሠሩትን እኛ እንሠራለን፤ በፌዴራል ትኩረት ተሰጥቷቸው የሚሠሩ ካሉ ምቹ ሁኔታ እንፈጥራለን ሲሉ አብራርተዋል።

# ሳምንቱን በታሪክ

## ‹‹ጥላሁን ለምን ለምን ሞተ?››

**ዋስልኝ አየለ**

ፕሮፌሰር እንድሪያስ እ ሸቴ ነገሩን እንደሚያስታውሱት፤ የተማሪዎች እንቅስቃሴ ሲጀመር ንጉሡ ብዙ አልተቆጡም ነበር። እንዲያውም የግጥም ምሽቶች ላይ እየተገኙ ሥርዓተ መንግሥታቸው ሲወቀስና ሲሰደብ ያዳምጡ ነበር። ‹‹ቁጭ ብዬ ስሰደብ አልሰማም›› ብለው የግጥም ምሽቱን መታደሙን አቆሙ። ፕሮፌሰር እንድሪያስ እንደሚሉት፤ ንጉሡ ተማሪዎችን ልጆች ናቸው ይመለሳሉ የሚል ምኞት የነበራቸው ይመስላል።

እየቆየ ሲሄድ ግን ነገሩ ጠነከረ። እንደነዋለልኝ መኮንን እና ጥላሁን ግዛው ያሉ አብዮተኞች አብዮቱን አቀጣጠሉት። የጥላሁን መሞትም የበለጠ አብዮቱን አጋጋለው። በዛሬው ሳምንቱን በታሪክ ዓምዳችን የጥላሁን ግዛውን አሟሟትና ‹‹ጥላሁን ለምን ለምን ሞተ?›› በሚል መገደሉን ተከትሎ የመጡ ነገሮችን እናስታውሳለን።

ይህ ድምጽ በተለምዶ ‹‹የ60ዎቹ ትውልድ›› እየተባለ የሚጠራው የዚያ ትውልድ ተማሪዎች ድምጽ ነበር። ‹‹ጥላሁን ለምን ለምን ሞተ!›› የጥላሁን ግዛውን አገዳደል ፍትሕ የሚጠይቅ የተማሪዎች መፈክር ነበር። ጥላሁን ግዛው የተገደለው ከ55 ዓመታት በፊት በዚህ ሳምንት ታኅሣሥ 19 ቀን 1962 ዓ.ም ነበር። ለመሆኑ ጥላሁን ግዛው ማነው? ለምን ተገደለ? በማን ተገደለ? የሚሉ ጥያቄዎችን የታሪክ ሰነዶችን ዋቢ አድርገን በዛሬው ሳምንቱን በታሪክ ዓምዳችን እናስታውሰዋለን። ከዚያ በፊት እንደተለመደው ሌሎች ዓለም አቀፍና የሀገር ውስጥ የዚህ ሳምንት የታሪክ አጋጣሚዎችን እናስታውስ።

ከ37 ዓመታት በፊት በዚህ ሳምንት ታኅሣሥ 17 ቀን 1980 ዓ.ም ኢትዮጵያ የምሥራቅና መካከለኛው አፍሪካ የእግር ኳስ ሻምፒዮና ዋንጫ (ሴካፋ) ለመጀመሪያ ጊዜ አሸነፈች። ኢትዮጵያ ባስተናገደችውና ስምንት ሀገራት (ኢትዮጵያ፣ ዚምባብዌ፣ ዛንዚባር፣ ኬንያ፣ ታንዛኒያ፣ ኡጋንዳ፣ ዛምቢያ እና ማላዊ) በተካፈሉበት 15ኛው የምሥራቅና መካከለኛው አፍሪካ የእግር ኳስ ሻምፒዮና ዋንጫ (ሴካፋ) ለፍፃሜ የቀረቡት አስተናጋጇ ኢትዮጵያ እና ዚምባብዌ ነበሩ። የወቅቱ የሁለቱ ሀገራት መሪዎች ኮሎኔል መንግሥቱ ኃይለማርያም እና ሮበርት ሙጋቤ ነበሩ። ይህ ጨዋታ በዝነኛው የስፖርት ጋዜጠኛ ደምሴ ዳምጤ ‹‹...ወይኔ! ወይኔ ዳኙ! ዳኙ አገባ!...›› በሚለው አይረሴ ድምጽ ይታወሳል። የዚህን ታሪክ ዝርዝር ባለፈው ዓመት ታኅሣሥ 23 ቀን 2015 ዓ.ም የታተመ አዲስ ዘመን ጋዜጣ ሳምንቱ በታሪክ ዓምድ ላይ ማግኘት ይቻላል።

ከ33 ዓመታት በፊት በዚህ ሳምንት በአውሮፓውያኑ የዘመን ቀመር ዲሴምበር 26 ቀን 1991 (በኢትዮጵያ ታኅሣሥ 17 ቀን 1984 ዓ.ም) የሶቪየት ሕብረት መበታተን በይፋ ታወጀ። እነሆ አሁን ሩሲያ (ራሽያ) በሚለው ስሟ ትጠራለች። በሁለተኛው የዓለም ጦርነት አሸናፊ ከነበሩት ሀገራት አንዷ በመሆን ከአራቱ የዓለም ልዕለ ኃያላን ሀገራት (አሜሪካ፣ እንግሊዝ፣ ፈረንሳይና ሶቪየት ሕብረት) አንዷ የነበረችው ሶቪየት ሕብረት በኋላ ከአሜሪካ ጋር ‹‹ቀዝቃዛው ጦርነት›› የሚባለው ጦርነት ውስጥ ገባች። አሜሪካ የምዕራቡን ዓለም፣ ሶቪየት ሕብረት የምሥራቁን ዓለም አጋር እያደረጉ ጎራ ፈጠሩ። እንዲህ እንዲህ እያለ የቀጠለው የሶቪየት ሕብረት ጉዳይ በ1984 ዓ.ም በይፋ ፈረሰ። እነሆ የሶቪየት ሕብረት መፍረስ በብዙ ፖለቲከኞችና የታሪክ ባለሙያዎች በየአጋጣሚው ሲጠቀስ እንሰማለን።

ከ117 ዓመታት በፊት በዚህ ሳምንት ታኅሣሥ 20 ቀን 1900 ዓ.ም በዳግማዊ አጼ ምኒልክ ዘመነ መንግሥት የመጀመሪያዋ መኪና ወደ አዲስ አበባ ገባች። እነሆ የመጀመሪያዋ መኪና እየተባለችም በታሪክ ትጠቀሳለች።

በዕለቱ በዝርዝር የምናየው የሳምንቱ ታሪክ በንጉሣዊ ሥርዓቱ ጊዜ የግራ ዘመም አራማጅ የነበረውን የጥላሁን ግዛው መገደል እና የነበረውን የተማሪዎች እንቅስቃሴ እናስታውሳለን።

**በግድያው የተቆጡ ተማሪዎች የጥላሁንን አስከሬን ወደ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ (ስድስት ኪሎ) ቅጥር ግቢ በመውሰድ ከአዲስ አበባ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ከመጡ ተማሪዎች ጋር የሀዘኑ ተካፋይ ሆኑ። የጥላሁን ታሪክና የትግል ዓላማ በግጥምና በስድ ንባብ እየተሰማ የሀዘን መግለጫው ዝግጅት ተካሄደ**

ጥላሁን ግዛው የተገደለው ከ55 ዓመታት በፊት በዚህ ሳምንት ታኅሣሥ 19 ቀን 1962 ዓ.ም ነበር። የጥላሁን መገደል ሲሰማ ‹‹ጥላሁን ለምን ተገደለ?›› በሚል በተማሪዎች ከፍተኛ ተቃውሞ ተቀስቅሶ ነበር። ‹‹ጎብር ሕይወቴ›› በሚል ከዓመት በፊት የታተመው የፕሮፌሰር ባህሩ ዘውዴ የግል የሕይወት ታሪካቸው መጽሐፍ ያንን ክስተት ያስታውሳል። የታኅሣሥ ግርግርን በዓይናቸው አይተው እንደነበረው ሁሉ በጥላሁን ግዛው መገደል የተፈጠረውን የአባታቸውን ጭንቀት እና የነበረውን ሁነት አስታውሰዋል። በነበረው ግርግር በአዲስ አበባ ውስጥ ከፍተኛ ውጥረት ነግሶ ነበር፤ ከ9 ዓመታት በኋላ የተከሰተ ሌላኛው የታኅሣሥ ግርግር መሆኑ ነው። በርግጥ ለተማሪዎች አብዮት መቀጣጠል እርሾ የሆነውም ያው የ1953 ዓ.ም የመፈንቅለ መንግሥት ሙከራ ነው።

ወደ ታሪኩ ስንመለስ፤ በኢትዮጵያ የተማሪዎች እንቅስቃሴ የግራ ዘመም ፖለቲከኞች ስብስብ ተጠናክሮ አዞዎች (ክሮኮዳይልስ) የተሰኘ ቡድንን በመፍጠር 1957 ዓ.ም የኢትዮጵያ ተማሪዎች የትግል መርህ ‹‹መሬት ላራሹ›› መሆኑ ይፋ ተደረገ። መጋቢት 4 ቀን 1957 ዓ.ም ‹‹መሬት ላራሹን የምትሹ፤ ተዋጉለት አትሽሹ›› እያሉ ተማሪዎች በአደባባይ ሰልፍ በወጡበት ወቅት የ11ኛ ክፍል ተማሪ የነበረው ጥላሁን በሰልፉ ተሳትፏል።

ጥላሁን ግዛው የ«አዞዎቹ» ዓላማ አራማጅና በኋላም ለመሪነት ለመታጨት የበቃ ወጣት ነበር። በ1961 ዓ.ም በተደረገው ፕሬዚዳንታዊ ምርጫ በመኮንን ቢሻው ቢሸነፍም በቀጣዩ ዓመት ኅዳር 1962 ዓ.ም በተደረገው ፕሬዚዳንታዊ ምርጫ በከፍተኛ ድምጽ ብልጫ አሸንፏል። ጥላሁን የፕሬዚዳንትነት ዘመኑ ቀዳሚ ሥራው የተማሪውን የመናገር፣ የመጻፍና የመደራጀት ነጻነት ይበልጥ ማጠናከር ነበር። ለሁለት ወር ብቻ በፕሬዚዳንትነት የቆየው ጥላሁን የተለያዩ ሃሳቦች እንዲንሸራሸሩ በማበረታታት የሚታወቅ ታጋይ ነበር ይባልለታል።

ታኅሣሥ 19 ቀን 1962 ዓ.ም ምሽት አንድ ሰዓት አካባቢ ከታናሽ ወንድሙ መኮንን ሲሳይ ጋር በመሆን ከስድስት ኪሎ በስተጀርባ አፍንጮ በር በሚባለው አካባቢ ፍቅረኛውን ዮዲት ታዬን ለመሸኘት ወጥተው ታርጋ በሌለው መኪና በተተኮሰ ጥይት ተገደለ።

ሱልጣን አባዋሪ የተባሉ ሰው ‹‹የተማሪው ትግልና የአብዮቱ ደመና›› በሚል ርዕስ አንታዛ መጽሔት ላይ ባቀረቡት ጽሑፍ የጠቀሷቸው ሌተናል ኮሎኔል ፍስሐ ደስታ ስለአሟሟቱ ሲገልጹ፤ ‹‹ስለ ጥላሁን ግድያ የተለያዩ ነገሮች ቢወሩም ... ሐቁ ግን ግድያው የተፈፀመው በንጉሡ ነገሥቱ የክብር ዘበኛ፣ የንጉሱ የቅርብ አጃቢ ወይም አንጋች ክፍል ምክትል አዛዥ በነበሩት በኮሎኔል ጣሰው ሞጃ ትዕዛዝና ከብሔራዊ ጦር ተዛውረው እኔው ራሴ ደብረ ብርሃን ካሰለጠንኳቸው በኋላ የአንጋች ክፍል ባልደረባ በሆኑት ሁለት ወታደሮች ነበር። ለዚሁ ድርጊታቸውም ሁለቱም የምክትል መቶ አልቅና ማዕረግ የተሰጣቸው መሆኑን የድርጊቱ ፈፃሚዎች ነግረውኛል›› ብለዋል።

በግድያው የተቆጡ ተማሪዎች የጥላሁንን አስከሬን ወደ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ (ስድስት ኪሎ) ቅጥር ግቢ በመውሰድ ከአዲስ አበባ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ከመጡ ተማሪዎች ጋር የሀዘኑ ተካፋይ ሆኑ። የጥላሁን ታሪክና የትግል ዓላማ በግጥምና በስድ ንባብ እየተሰማ የሀዘን መግለጫው ዝግጅት ተካሄደ።

ቀጥሎም በተማሪዎች ሰልፍ ታጅቦ በክብርና በጀግንነት በሥላሴ ቤተ ክርስቲያን የቀብሩ ሥነ ሥርዓት ይፈጸም ዘንድ የዩኒቨርሲቲው ተማሪዎች ያደረጉት ጥረት በንጉሡ ጸጥታ ኃይሎች ርምጃ የተጨማሪ ተማሪዎችን ሕይወት ቀጥፎ አስከሬኑ ከተማሪዎቹ ተወሰደ።

የጥላሁን ግዛው አስከሬን ከተማሪዎቹ በኃይል ርምጃ ከተወሰደ በኋላ የቀብር ሥነ ሥርዓቱ ታኅሣሥ 22 ቀን 1962 ዓ.ም መላው ዘመድ አዝማድ በተገኙበት በአካባቢው ተማሪዎች ሰልፍ አጃቢነት በወቅቱ ትግራይ ጠቅላይ ግዛት በማይጨው ሕዝባ ማርያም ቤተክርስቲያን ተፈጸመ።

የኢትዮጵያ ተማሪዎች ንቅናቄም የጥላሁንን መገደል አስመልክቶ ባለ ሰባት ነጥብ የአቋም መግለጫ አወጥቶ ነበር። የመግለጫው ጥቅል መልዕክት፤ በጥላሁን መገደልና መገደሉን ተከትሎም በተከሰተው ተጨማሪ ጥፋት ሁሉ የወቅቱን ገዥ መንግሥት (የንጉሡን ሥርዓት) ተጠያቂ የሚያደርግ ነበር።

የተማሪዎች እንቅስቃሴም የበለጠ ተቀጣጠለ። ‹‹የጥላሁን ገዳዮች እኛንም ግደሉን! ጨርሱን! ተኩስ! እስቲ በል ተኩስ! ፋሽስት!›› የሚሉ መፈክሮችና ቁጣዎች ተጠናክረው ተቀጣጠሉ። ይህ እንቅስቃሴ ተጠናክሮ ቀጥሎ ከሦስት ዓመት በኋላ ደግሞ ኅዳር 29 ቀን 1965 ዓ.ም የጥላሁን ግዛው የትግል አጋር የነበረው ዋለልኝ መኮንንና ፍቅረኛው ማርታ ተገደሉ። አሁንም ተቃውሞውና መፈክሩ ቀጠሉ።

**ጥላሁን ለምን ለምን ሞተ?**
**ዋለልኝ ለምን ለምን ሞተ?**
**ማርታ ለምን ለምን ሞተች?**
**በኃይል በትግል ነው**
**ነፃነት የሚገኘው!**

እያለ ያ ትውልድ ለቀጣይ ትግል ቅስቀሳ ጀመረ። ዝማሬዎች የየሰልፉ ማድመቂያና መቀስቀሻ ሆኑ። ማንነቱን ለሕዝብ መብትና ነፃነት አሳልፎ ሊሰጥ የተዘጋጀ ትውልድ መሆኑን ደጋግሞ ተናገረ። ወደ ጥላሁን ግዛው እንመለስ።

ጥላሁን ግዛው በአሁኑ አወቃቀር ከደቡብ ትግራዩ የራያና አዘቦ አውራጃ ተወላጅ አባቱና እንዲሁም ደግሞ ከሰሜን ወሎዋ የራያ ቆቦ አውራጃ ተወላጇ እናቱ አብራክ የተወለደ የሁለት ራያ ልጅ መሆኑን ዋልታ ላይ የተሰነደ ታሪክ ያሳያል። ጥላሁን የተወለደውና እንዲሁም ሲሞት የተቀበረው አባትዬው አቶ ግዛው አበራ ተድላ ይኖሩበት በነበረው የራያና ዓዘቦ አውራጃ ዋና ከተማ ማይጨው ውስጥ እንደሆነ ወንድሙ ጭምር አረጋግጠዋል። በማይጨው ከተማ የማይጨው ከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት በጥላሁን ግዛው ስም መሰየሙንም የታሪክ ሰነዶች ያሳያሉ።

የጥላሁን ወላጆች ትዳር ሳይሰምር ቀርቶ በፍቺ ለመለያየት እንደተገደዱና እርሱም ገና ከልጅነት ዘመን ዕድሜው ጀምሮ ከእናቱ ጋር ወደ ራያ ቆቦ የሄደበት ሁኔታ ስለመፈጠሩም ታናሽ ወንድሙ ተናግረው እንደነበር ከዓመታት በፊት የተሠራ የዋልታ ዘገባ ያሳያል።

ስለጥላሁን የተጻፉ ሰነዶች እንደሚያሳዩት፤ ጥላሁን ግዛው ከሌሎቹ የኢትዮጵያ ተማሪዎች ዓለም አቀፋዊ የስርነቀል ለውጥ ፍለጋ ንቅናቄ መሪ ተዋንያን የተለየ የሚያደርገው መሠረታዊ ምክንያት፤ በአባቱ ወገን ከትግራይ ታላላቅ መሳፍንቶች መካከል አንዱ ከነበሩትና በተለይም የራያ ዓዘቦ አውራጃ ዋና ከተማ የሆነቺውን ማይጨውን እንደቆረቆሯት ከሚነገርላቸው ከደጃዝማች ተድላ ገብረ ዋህድ ቤተሰብ የተገኘ ሆኖ ሳለ፤ የቀዳማዊ አጼ ኃይለሥላሴን ዘውዳዊ አገዛዝ ታግሎ ስለማስወገድ አስፈላጊነት በመገንዘብ የስርነቀል ለውጥ አቀንቃኝ መሆኑ ነው።

የአሁኑ ትውልድ ምናልባትም ከዚህ ሊማረው የሚገባው ነገር፤ የጋብቻ መተሳሰር፣ የብሔርና የሃይማኖት ወገንተኝነት፣ የራሴ ወገን ነው... የሚሉ ነገሮች የጋራ ዓላማ እንዳይኖር የሚያደርጉ መሆኑን ነው። ለድጋፍም ይሁን ለተቃውሞ የጋራ ዓላማ እንጂ የግል እና የቡድን ፍላጎት የጋራ ሀገር አይገነባም።

ሌላው ልብ መባል ያለበት ነገር፤ በተለምዶ ‹‹የ60ዎቹ ትውልድ›› የሚባሉ የለውጥ አቀንቃኞች ትግላቸው ምን ነበር? እነማን ምን አደረጉ የሚሉትን በወቅቱ ከነበሩ ሰዎች፣ ወይም በወቅቱ የነበረውን ሁነት ጽፈው ያስቀመጡ ሰዎችን ሰነዶች ማየት ያስፈልጋል። ያ ባለመሆኑ ይመስላል በተለይም የእነ ጥላሁን ግዛው እና ዋለልኝ መኮንን ጉዳይ በተለያዩ አወዛጋቢ (ወጥ ባልሆነ) መንገድ ሲከራከሩባቸው ይሰማል። በመሆኑም በዘመኑ የነበሩ ሰዎች የነበረውን ሁነት ሊጽፉልን ይገባል!

ይህ አምድ በተለያዩ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጉዳዮች ዙሪያ ዜጎች ነፃ ሀሳባቸውን የሚሰጡበት ነው:: በዓምዱ ላይ የሚወጡ ጽሁፎች የዝግጅት ክፍሉን አቋም አያመለክቱም::

ፖለቲካ እና ወቅታዊ

# ነፃ ሃሳብ

# ከአዲሱ የአትሌቲክስ አመራር ብዙ እንጠብቃለን!

ልዑል ከካምቦሎጆ

የኢትዮጵያ የኩራት ምንጭ የሆነው የአትሌቲክስ ስፖርት ዛሬም የሀገርና የሕዝብ ኩራት ነው:: ያም ሆኖ ባለፉት ጥቂት የማይባሉ ዓመታት በአግባቡ ባለመመራቱ አስተዳደራዊ ስንክሳሮች በየጊዜው በስፖርቱ ሁለንተናዊ ዕድገት ላይ ትልቅ እንቅፋት እየሆነ ይታያል:: በዚህም ምክንያት በየጊዜው በአትሌቲክስ ፌዴሬሽኑ አመራሮች ላይ የተለያዩ ቅሬታዎች ይሰነዘራሉ::

እነዚህ ቅሬታዎች በየጊዜው እያሽቆለቆለ ከመጣው የአትሌቲክስ ውጤት ጋር ተያይዞ ባለፉት ጥቂት ዓመታት ሕዝብን ያስቆጡ ጭምር ናቸው:: በዚህም የኢትዮጵያ አትሌቲክስ አፍቃሪዎችና የስፖርቱ ተቆርቋሪዎች ስፖርቱን ወደዘመናዊው የአስተዳደር ደረጃ ሊያሻግሩ የሚችሉ የአመራር ብቃቱ ያላቸው ሰዎችን ለማየት ይፈልጋል:: ይሁን እንጂ በሚጠበቀው ልክ የስፖርቱን እድገት ዕውን ሊያደርጉ የሚችሉ አመራሮችን ለማየት ሳይቻል ቆይቷል::

አልፎ አልፎ የመሥራት አቅሙና ፍላጎቱ ያላቸው ሰዎች ብቅ ሲሉም በስፖርቱ ዙሪያ ባለው የመጠላለፍ ፖለቲካ፣ ለግል ጥቅም እና ፍላጎታቸው ብቻ በሚጨነቁ ግለሰቦች ወይም ቡድኖች ሴራ በፍጥነት ከአካባቢው ገለል እንዲሉ ይደረጋል::

በአትሌቲክስ ፌዴሬሽኑ አመራር ዙሪያ ባለፉት ጥቂት ዓመታት ውስጥ የታዩት የአስተዳደር ግድፈቶች ከምንግዜውም የከፉ ነበሩ:: ምክንያቱ የአስተዳደር ዕውቀት እና አቅም ማነስም ይሁን የግል ስሜት እና ፍላጎቶችን መከተል በፌዴሬሽኑ አመራር ዙሪያ ደካማ የውሳኔ አሰጣጦች፣ አቅዶ የመተግበር ችግር፣ እና ግልፅ ያለመሆን እንዲሁም አትሌቶቻችን እና አጠቃላይ ስፖርቱን የሚመለከቱ ችግሮችን አግባብ ባለው መንገድ መፍታት ያለመቻል ችግሮች በተደጋጋሚ ታይተዋል።

እነዚህ ከአስተዳደር ብቃት እና ቁርጠኝነት ማነስ ጋር የተያያዙ ችግሮች የፈጠሯቸው ክፍተቶችም የኢትዮጵያን አትሌቲክስ እድገት ከማደናቀፍ በዘለለ ከጊዜ ወደጊዜ በፌዴሬሽኑ፣ በአትሌቶች፣ በአሰልጣኞች እና በስፖርቱ እውነተኛ ደጋፊዎች ዘንድ መተማመን እንዲጠፋ ሲያደርጉ ታዝበናል::

በፓሪስ ኦሊምፒክ ዝግጅት እና በውድድሩ ወቅት እንዲሁም ከዛም በፊት በነበሩት ጊዜያት በአትሌቲክስ ፌዴሬሽኑ አመራር ዙሪያ አስተዳደራዊ ድክመቶች በስፋት ተስተውለዋል:: ከድክመቶቹ አብዛኞቹ በቀደሙት የአትሌቲክስ ፌዴሬሽን መሪዎች ጊዜም የነበሩ እና ባሉበት ሲንከባለሉ እዚህ የደረሱ ናቸው:: ነገር ግን በጊዜው በነበረው አመራር አንዳንዶቹ ችግሮች እጅግ መስመራቸውን ሲስቱ እንደታዩም ማስተባበል አይቻልም::

ለረጅም ዓመታት ባለበት የቆመው የሀገር ውስጥ ውድድሮች የጥራት ደረጃ፣ ከጊዜ ወደጊዜ እየተባባሰ የመጣው የልምምድ እና የውድድር ማዘውተሪያ ሥፍራዎች እጥረት፣ ዓለም አቀፍ የውድድር መድረኮች በተቃረቡ ቁጥር ከአትሌቶች ምርጫ ጋር በተያያዘ የሚታየው ውዝግብ፣ የአትሌቲክስ ስፖርትን ለሚያስተዳድር ተቋም የጀርባ አጥንት ከሚባሉ ነገሮች መካከል አንዱ የሆነው የመረጃ ቋት አደረጃጀት ዙሪያ በአግባቡ መሥራት ያስፈልጋል።

የሚወጡ የመተዳደሪያ ሕግ እና ደንቦችን ለስፖርቱ ባለድርሻ አካላት እና ለሕዝብ በይፋ አለማስተዋወቅ እና በአግባቡ አለመተግበር፣ እንዲሁም ትኩረት ሊሰጣቸው የሚገባቸውን ጉዳዮች ለይቶ የአጭር እና የረጅም ጊዜ ዕቅድ አውጥቶ ለመተግበር አለመሥራት በዋናነት ሊጠቀሱ ከሚችሉት ችግሮች መካከል ናቸው::

በተዘረዘሩት ችግሮች እንደተከበበ 28ኛ መደበኛ ጠቅላላ ጉባኤውን ባለፈው ሳምንት መጨረሻ ታኅሣሥ 12 እና 13 ቀን 2017 ዓ.ም. በአዲስ አበባ ያካሄደው የኢትዮጵያ አትሌቲክስ ፌዴሬሽን የፕሬዚዳንት እና ሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ አባላት ምርጫ አድርጎ አዳዲስ አመራሮች ወደፊት መጥተዋል::

አዳዲሶቹ የአትሌቲክስ አመራሮች አብዛኞቹ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ ከዚህ ቀደም በአትሌክስ ፌዴሬሽኑ ውስጥ ተሳትፎ የነበራቸው እንደመሆኑ አዲስ ለማለት ቢከብድም ከስፖርቱ ጋር ቅርበት ያላቸው ናቸው:: ይህም የኢትዮጵያ አትሌቲክስ ከምንጊዜውም በከፋ የአስተዳደር ችግር ውስጥ ባለበት በዚህ ወቅት ትልቅ ኃላፊነት ተሰምቷቸው ቢያንስ እየገዘፉ የመጡትን ችግሮች ሊቀንሱ እንደሚችሉ ተስፋ ተጥሎባቸዋል::

**በኢትዮጵያ አትሌቲክስ ውስጥ በተደጋጋሚ እየተከሰተ ያሰለቸ ነገር ቢኖር ለዓለም አቀፍ ውድድሮች የአትሌቶች ምርጫ በሚደረግ ጊዜ የሚታየው ውዝግብ ነው**

አዳዲሶቹ አመራሮች በምርጫው ወቅት ራሳቸውን ሲያስተዋውቁ አብዛኞቹ የፌዴሬሽኑን ችግሮች ጠንቅቀው እንደሚያውቋቸው ታዝበናል:: ይህም ‹‹ችግሩን ማወቅ የመፍትሔው ግማሽ አካል ነው›› እንደሚባለው የስፖርቱን ችግሮች ማወቃቸው ተስፋ እንድንጥልባቸውና ብዙ እንደምንጠብቅባቸው ያደርገናል::

ምክንያቱም ከተመረጡ በኋላ ችግሩ ምንድነው ብለው ለማጣራት የሚያጠፉት ጊዜ ሳይኖር በቀጥታ የሚያውቋቸውን ችግሮች ለመቅረፍ ወደሚያስችለው የመፍትሔ ሃሳብ እና ትግበራ እንዲገቡ ያግዛቸዋል::

ያም ሆኖ እነዚህ አዳዲስ አመራሮች ተጠባቂ ፈተናዎች እንደሚጠብቋቸው ግልፅ ነው:: ኮስተር ያለ የአመራር ብቃታቸውን ለማሳየትም ቁርጠኛ መሆን አለባቸው::

አዲሱ አመራር ውጤታማ ሥራን ለማከናወን የአጭር ጊዜ እና የረዥም ጊዜ ስትራቴጂክ ዕቅዶችን ማዘጋጀት ያስፈልገዋል:: እነዚህን ዕቅዶች ለማዘጋጀትም የአትሌቲክስ ፌዴሬሽኑን ወቅታዊ ሁኔታ በጥልቀት በመፈተሽ ቁልፍ ጥንካሬዎችን፣ ድክመቶችን፣ እድሎችን እና ሥጋቶችን መለየት አለበት።

የአጭር ጊዜ እቅዱ ፈጣን ማሻሻያዎችና የቅድሚያ ትኩረት በሚያስፈልጋቸው በጊዜያዊ የልምምድ እና ውድድር ማዘውተሪያ ችግሮች መፍቻ፣ መቀየር ያለባቸው የአሠራር ሂደቶች፣ የአሰልጣኝነት ሥልጠና መርሃ ግብሮችን ማሳደግ፣ ስፖንሰርሺፕን ማጠናከር፣ በቅርቡ ለሚካሄዱ ዓለም አቀፍ ውድድሮች የሚያስፈልጉ ቅድመ ዝግጅቶች እና ሌሎችም መካተት የሚያስፈልጋቸው ጉዳዮች ላይ ሊያተኩር ይችላልና በነዚህ ጉዳዮች ላይ የስፖርት ቤተሰቡ ለውጥ ማየት ይሻል::

የረዥም ጊዜ ስትራቴጂው ደግሞ የውድድሮች ጥራትን እና የውድድር ማዘውተሪያዎችን ማስፋፋት እና ማዘመን፣ የሥልጠና ተቋማትን ማሳደግ፣ በሁሉም ዘርፎች ለአትሌቶች እድገት ቅድሚያ መስጠት፣ ዘላቂ ዓለም አቀፍ አጋርነትን መፍጠር እና ሌሎችም መካተት የሚያስፈልጋቸው ነገሮች ላይ ሊያተኩር ይችላል።

በሁለቱም ዕቅዶች ውስጥ የሚካተቱት ነገሮች ግልጽ፣ ሊለኩ የሚችሉ ግቦች ያሏቸው እና በጊዜ ሰሌዳዎች የተደገፉ መሆን አለባቸው:: መደበኛ የአፈፃፀም ግምገማ ማድረጊያ ጊዜ ሊኖሯቸውም ይገባል። አፈፃፀሞቹን የሚቆጣጠር ኮሚቴ በማቋቋም የአፈጻጸም መለኪያ ዳታዎችን እና ትንታኔዎችን በመጠቀም የሩብ ዓመት ግምገማን ማድረግ፣ ትግበራውን ለማሳካትም እንደ አስፈላጊነቱ ስልቶችን መቀየር ይቻላል።

ከባለድርሻ አካላት ጋር በተለያዩ መንገዶች አዘውትሮ በመገናኘት እና ግልጽ የሆነ ሪፖርትን በማቅረብም ተጠያቂነትን እና እያደገ ካለው የዓለም የአትሌቲክስ ገጽታ ጋር መጣጣምን የበለጠ ለማረጋገጥ መትጋት ያስፈልጋል።

የጽሕፈት ቤት አሠራርን መፈተሽ እና ማዘመን ሌላው የቤት ሥራ ይሆናል:: የኢትዮጵያ አትሌቲክስ ፌዴሬሽን የዓለም አትሌቲክስ መስፈርቶችን ተከትሎ እንዲራመድ የጽሕፈት ቤቱን አጠቃላይ አሠራር መገምገም እና ማዘመን ግድ ይላል። ይህም ማሻሻያ ማድረግ የሚቻልባቸውን የአስተዳደር፣ የቴክኒክ ወይም የውድድር ዝግጅት፣ የቴክኖሎጂ አጠቃቀም እና የሕዝብ ግንኙነት ሥራዎችን ጠንካራ እና ደካማ ጎን መለስ ብሎ መመልከትን ይጠይቃል።

ከቢሮው አስተዳደራዊ እና ድርጅታዊ መዋቅር ጋር በተያያዘ በሀገር ውስጥ በቢሮው ውሳኔ ማግኘት ለሚገባቸው ጉዳዮች የውሳኔ አሰጣጥ ሂደቶች ውጤታማነት እንዲሁም በዓለም አቀፉ አትሌቲክስ ላይ ለሚደረጉ ለውጦች ፈጣን ምላሽ ለመስጠት በቂ አቅም ያለ መሆኑም መታየት አለበት::

በተለይ ለአትሌቶች የሚሰጡ አገልግሎቶች ቅልጥፍና፣ የውድድር ውጤቶችን በአግባቡ መሰነድ እና ለሚፈልጉት ሁሉ በቀላሉ የሚገኙ እንዲሆኑ ማድረግ፣ አጠቃላይ የዓለም አትሌቲክስም ሆነ የብሔራዊ ፌዴሬሽኖች መተዳደሪያ ሕጎች፣ ደንቦች እና መመሪያዎች እንዲሁም የውድድር ሕጎች እና ሌሎችም ባለድርሻ አካላት ሊያውቋቸው የሚገቡ ለውጦች ሲኖሩ ወቅቱን በጠበቀ መልኩ ማሳወቅ ላይ በትኩረት መሥራት ያስፈልጋል::

እንዳደጉት ሀገራት የፌዴሬሽኑ ጽሕፈት ቤት የሥራ ነፃነት ከተጠያቂነት ጋር ተሰጥቶ በዋና ሥራ አስፈፃሚ ወይም ዋና ዳይሬክተር እንዲመራ ቢደረግም ጥሩ ነው:: የፌዴሬሽኑ ጽሕፈት ቤት ሠራተኞችን የአፈፃፀም አቅም ለማጎልበት እና በዓለም አቀፉ አትሌቲክስ ዙሪያ ከሚደረጉ ለውጦች ጋር እኩል እንዲራመዱ ለማስቻልም የአቅም ግንባታ ሥልጠናዎች በቋሚነት ቢሰጡ ስፖርቱን ከዘመኑ ጋር እንዲራመድ ወሳኝ ነው::

የሀገር ውስጥ ውድድሮችን ዓለም አቀፍ ደረጃውን በጠበቀ መልኩ ማካሄድ ለነገ የሚባል የቤት ሥራ አይደለም:: የኢትዮጵያ አትሌቲክስ ስፖርትን ወደኋላ እየጎተቱት ይገኛሉ ተብሎ ከሚታሰቡ ነገሮች መካከል በዋናነት ትኩረት ተሰጥቶበት ሊሠራበት የሚያስፈልገው የሀገር ውስጥ ውድድሮችን በዓለም አትሌቲክስ ደረጃ ማካሄድ ነው::

በሀገር ውስጥ የሚካሄዱ ውድድሮች በዓለም አትሌቲክስ ደረጃ አለመካሄድ የኢትዮጵያውያን አትሌቶችን በሙሉ በተለይም የአጭር ርቀት እና የሜዳ ላይ ተግባራት ተወዳዳሪዎች ልፋት ተገቢውን እውቅና እንዳያገኝ እያደረገ የሚገኝ ችግር ነው:: ስለዚህ ቢያንስ በዓለም ደረጃ(ወርልድ ራንኪንግ) ነጥብ ለማስመዝገብ የሚረዱ ዋና ዋናዎቹን የሀገር ውስጥ ውድድሮች ውጤት በኤሌክትሮኒክስ የሰዓት መቆጣጠሪያ የሚደገፍ ለማድረግ መሥራት እጅግ አስፈላጊ ነው::

የውድድሮችን ውጤቶች በዘመናዊ እና ዓለም አቀፉን መለኪያ በሚያሟላ መልኩ አለመያዝ በአህጉራዊ እና ዓለም አቀፋዊ ውድድሮች ላይ ለተሳትፎ የሚያበቁ ውጤቶችን (የዓለም ደረጃዎች ነጥብ) በማስመዝገቡ ረገድ የሚኖረው አሉታዊ ተፅዕኖ ከፍተኛ መሆኑን እዚህ ጋር ማስታወስ ተገቢ ይሆናል::

የዓለም አትሌቲክስ እ.አ.አ. በዲሴምበር 2022 ዓ.ም. ለብሔራዊ ፌዴሬሽኖች በላከው መልእክት የትኛውም ዓይነት ውድድሮች በዓለም አትሌቲክስ የውድድር ካላንደር ላይ እንዲመዘገቡ እስካልተደረጉ እና ውጤታቸው በአወዳዳሪው አካል እስካተላከለት ድረስ ውጤቶቹ በድረ ገፁ ላይ እንደማይሰፍሩ እና ለማንኛውም የስታትስቲክስ ዓላማው (የመግቢያ ደረጃዎች፣ የዓለም ደረጃዎች፣ ከፍተኛ ዝርዝሮች፣ ሪከርዶች፣ ወዘተ) እንደማይጠቀማቸው አሳውቋል።

መልዕክቱ ከተላከ በኋላ ባለፉት ሁለት ዓመታት በኢትዮጵያ አትሌቲክስ ፌዴሬሽን በኩል ለዓለም አትሌቲክስ የተላከ ብቸኛ የውድድር ውጤት እ.አ.አ. ከጁላይ 02 እስከ 06/2024 የተካሄደው የኢትዮጵያ ከ20 ዓመት በታች ቻምፒዮና ውጤት ነው::

ስለዚህ ፌዴሬሽኑ በዓመቱ ውስጥ የሚያደርጋቸውን ውድድሮች በዓለም አትሌቲክስ የውድድር ካላንደር ላይ እንዲመዘገብ በማድረግ እና ውጤቶችን በሰዓቱ በመላክ የአትሌቶቹ ልፋት ዓለም አቀፍ ዕውቅናን እንዲያገኝ የመሥራት ኃላፊነትም እንዳለበት መዘንጋት የለበትም::

የመረጃ ቋት የማደራጀት ጉዳይ የሁሉም የስፖርት ፌዴሬሽኖች ችግር ነው:: የመረጃ ቋት የአትሌቲክስ የጀርባ አጥንት ነው:: በአግባቡ የተደራጀ እና ወጥነት ያለው የመረጃ ቋት ያለመኖር ደግሞ የኢትዮጵያ አትሌቲክስ አንዱ ድክመት ነው:: የአትሌቶችን ምዝገባ፣ ፕሮፋይሎችን እና የሀገር ውስጥ የውድድር ውጤቶችን የሚያጠቃልል የተማከለ ዲጂታል የመረጃ ቋት ማዘጋጀት ለአንድ ሀገር አትሌቲክስ ፌዴሬሽን አስፈላጊነቱ ከፍተኛ ነው።

ለአሰልጣኞች እና የፌዴሬሽን ባለሥልጣናት የአትሌቶችን አፈፃፀም፣ እድገት እና ተሳትፎን በመከታተል በመረጃ የተደገፈ ውሳኔ እንዲወስኑ ጠቃሚ መረጃዎችን ይሰጣል። በደንብ የተደራጀ የመረጃ ቋት ግልፅነትን ያሳድጋል፣ የውድድር ውጤቶችን ወጥ በሆነ መልኩ ያሳያል፣ ሪኮዶችን በአግባቡ ለመለየት፣ የአትሌቶችን ጥንካሬ እና ድክመት እንዲሁም ወቅታዊ ሁኔታዎችን ለመገምገም፣ የእድሜ ማጭበርበርን ለመቆጣጠር፣ እና የረጅም ጊዜ የአትሌቶችን እድገት ሂደት ለማወቅም ይረዳል።

ከሁሉም በላይ በስፖርቱ ውስጥ የላቀ ተጠያቂነትን፣ ፍትሃዊነትን እና የአሠራር ቅልጥፍናን ያጎለብታል:: ይህን ክፍተት ለማስተካከል ፌዴሬሽኑ የሚዲያ እና ሕዝብ ግንኙነት ክፍሉን የድረ ገፅ ማልማት እና ማዘመን እንዲሁም የአትሌቲክስ መረጃዎቹን በአግባቡ ማዘጋጀት በሚችሉ ባለሙያዎች ጥምረት ማጠናከር ይኖርበታል::

የአትሌቶች ምርጫ አዲሱ አመራር ለውጥ ሊያመጣበት የሚገባ ዋናው ጉዳይ ነው:: በኢትዮጵያ አትሌቲክስ ውስጥ በተደጋጋሚ እየተከሰተ ያሰለቸ ነገር ቢኖር ለዓለም አቀፍ ውድድሮች የአትሌቶች ምርጫ በሚደረግ ጊዜ የሚታየው ውዝግብ ነው::

ይህ የሚሆንበት ምክንያት ደግሞ ፌዴሬሽኑ ግልጽ የሆነ የመምረጫ መስፈርት በማስቀመጥ አስቀድሞ ለባለድርሻ አካላት እና ለሕዝብ ወቅቱን በጠበቀ መልኩ በይፋ የማሳወቅ ሥራውን ችላ ስለሚለው ነው:: አንዳንዴ መስፈርት ቢወጣም መስፈርቱ በይፋ ሳይገለጽ ከጀርባ የግል ፍላጎቶች እየተጫኑት ችግሩን ሲያባብሰው ይታያል::

ይህን ችግር ለአንዴ እና ለመጨረሻ ጊዜ መቅረፍ የሚቻለው ሁሉንም የስፖርቱን ባለድርሻ ባሳተፈ ምክክር ወጥ እና ግልፅ የመምረጫ መስፈርት ሲወጣ ነው:: ሁሉንም ገዢ የሆነ የምርጫ መስፈርቶች ከወጡ በኋላም በፌዴሬሽኑ ድረ-ገጽ፣ የማህበራዊ ግንኙነት ገፆች እና በተለያዩ ሚዲያዎች አትሌቶች ለዓለም አቀፍ ውድድሮች ለመመረጥ ዝግጅት ከመጀመራቸው በፊት በደንብ መተዋወቅ አለባቸው::

ሁሉም አትሌቶች እና አሰልጣኞች ሙሉ በሙሉ እንዲረዷቸው ለማድረግም መስፈርቶቹ በብዙ ቋንቋዎች ተደራሽ መሆናቸውን ማረጋገጥም በጣም አስፈላጊ ነው። በተጨማሪም የምርጫ ሂደቱ ለይግባኝ ሂደቶች ክፍት መሆን አለበት። መስፈርቶቹን ቀድሞ ማሳወቅ አትሌቶች የሚጠበቅባቸውን እንዲያውቁ ስለሚያደርግ ያለመግባባቶችን እምቅ አቅም ይቀንሳል:: በአትሌቲክስ ማህበረሰቡ ውስጥም መተማመንን ያሳድጋል።

አዳዲሶቹ የኢትዮጵያ አትሌቲክስ ፌዴሬሽን መሪዎች እነዚህን የቤት ሥራዎች በትክክል በመምራት ስፖርቱ በዓለም አቀፍ አትሌቲክስ ግንባር ቀደም ደረጃውን ጠብቆ እንዲጎለብት የማድረግ አቅም አላቸውና የስፖርት ቤተሰቡ ከእነሱ ብዙ እንደሚጠብቅ አውቀው በትጋት ሊሠሩ ይገባል::

በስፖርቱ ዙሪያ ያሉትን ችግሮች በሚቻለው መንገድ ለመቅረፍ ከመሞከር ባሻገር የጠቅላላ ጉባኤው አደረጃጀት ላይ፣ አዎንታዊ እና አሉታዊ ሚናዎቹም ላይ ውይይት የሚደረግበት መድረክ ቢፈጠር መልካም ነውና አዲሱ አመራር ጊዜ ወስዶ እንዲያስብበት ተስፋ እናደርጋለን::

# ዓለም አቀፍ

## በሱዳን ጦርነቱ ከተቀሰቀሰ በኋላ የመጀመሪያው ርዳታ ወደ ካርቱም ገባ



ጦርነቱ ከተቀሰቀሰ ከሁለት ዓመት ገደማ በኋላ ለመጀመሪያ ጊዜ የምግብ ርዳታ የጫኑ ተሽከርካሪዎች ወደ ሱዳኗ መዲና ካርቱም ገቡ። በሱዳን ጦር እና በፈጥኖ ደራሽ ኃይሉ ደጋፊ ኃይሎች መካከል እየተደረገ ባለው የደም አፋሳሽ ጦርነት ምክንያት ሱዳን በዓለማችን እጅግ የከፋ የረሃብ ቀውስ ውስጥ እንደምትገኝ የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት አስታውቋል።

ርዳታ የጫኑ ተሽከርካሪዎች ታኅሣሥ 17 ቀን 2017 ዓ.ም ወደ ደቡባዊ ካርቱም ሲገቡ በርካቶች "በሳቅ እና በደስታ እንባ ታጅበው ነበር" ሲሉ የረድዔት ሠራተኛ የሆኑት ዱአ ታሪክ ገልጸዋል። የርዳታ ኤጀንሲዎች የፀጥታ ስጋቶች እንዲሁም ተፋላሚ ወገኖች በሚያደርጓቸው የመንገድ መዝጋቶች ጋር በተያያዘ ወሳኝ የሆኑ የርዳታ አቅርቦቶችን እያስተጓጎሉ ነው በማለት ሲወቅሱ ቆይተዋል።

ያለፈው ሐሙስ ወደ መዲናዋ የገባው ርዳታ እንዲደርስ የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት ኤጀንሲዎች እና የሱዳን ማኅበረሰብ ቡድኖች ከሱዳን ጦር እና ከፈጥኖ ደራሽ ኃይሉ ጋር ድርድር አካሂደዋል። "በእንባ ታጅበን ነበር፣ የደስታ እንባ፣ ይህንን ለማድረግ የደከምንበት እና የጥረታችን እንባ፤ አስገራሚ ክስተት ነበር" ሲሉ የሱዳን የሰብዓዊ የረድዔት ድርጅት ጋር የሚሠሩት ታሪክ ለቢቢሲ ኒውስ ደይ ፕሮግራም ተናግረዋል።

ርዳታው 28 የጭነት መኪኖች እንዳካተተ ተገልጿል። ከርዳታው ውስጥ አምስቱን የጭነት መኪና የላከው ዩኒሴፍ "ሕይወት አድን" የምግብ እና የጤና አቅርቦቶችን ለአልባሻየር ሆስፒታል እና በካርቱም ለሚገኙ ሌሎች የጤና ማዕከላት ማድረስ መቻሉን ገልጿል።

"ካርቱም ውስጥ ይህ ርዳታ በጣም ያስፈልገናል። በከፍተኛ ሁኔታ ስንጠብቀው ነበር። ይህንንም ለማድረግ በርካታ መንገዶችን እና ዘዴዎችን ሞክረናል። በሀገሪቱ ውስጥ ያለውን የረሃብ ተፅዕኖ ለመቀነስ ብቸኛው መንገድ እንዲህ ያሉ ርዳታዎች ናቸው" ብለዋል።

ከቀናት በፊት አንድ ገለልተኛ የምግብ ዋስትና ባለሙያዎች ቡድን ሱዳን ወደ "ከፋ የረሃብ ቀውስ" እየገባች ነው ሲል አስጠንቅቆ ነበር። ረሃብ ወደ አምስት አካባቢዎች የተዛመተ ሲሆን 24 ነጥብ 6 ሚሊዮን ወይም ግማሽ ያህሉ ሕዝብ አስቸኳይ የምግብ እርዳታ እንደሚያስፈልገው ቡድኑ ገልጿል።

ጦሩ እና ፈጥኖ ደራሽ ኃይሉ ከሦስት ዓመታት በፊት በጋራ መፈንቅለ መንግሥት ቢያደርጉም ነገር ግን በመሪዎቹ መካከል በተፈጠረ የሥልጣን ሽኩቻ ሀገሪቱ የርስ በርስ ጦርነት ውስጥ ከገባች 20 ወራትን አስቆጥሯል። በሱዳን የአሜሪካ ልዩ መልዕክተኛ ቶም ፔሪየሎ በጦርነቱ እስከ 150 ሺህ ሰዎች ሳይገደሉ እንዳልቀሩ ባለፈው በግንቦት ወር ተናግረው ነበር።

በሱዳኑ ጦርነት ምክንያት ከ11 ሚሊዮን በላይ ነዋሪዎች ከቤት ንብረታቸው ተፈናቅለዋል። በጦሩ እና በፈጥኖ ደራሽ ኃይሉ መካከል እየተደረገ ያለውን ጦርነት ለማስቆም የተደረጉ የሽምግልና ጥረቶች ፍሬ ሳያፈሩ ቀርተዋል ሲል የዘገበው ቢቢሲ ነው።

## ኦሮሚያ ክልል

ለወ/ሮ ኬራት አደም

ባሉበት

በፍርድ ባለመብት በእርስዎ እና በፍርድ ባለ እዳ አንዋር አደም መካከል ስላለው የአፈጻጸም ክርክር ጉዳይ አስመልክቶ በውሳኔ አመልካች የፍርድ ባለ እዳ ንብረት የሆነው ቤት ከዚህ በፊት ለቀለብ ታግዶ የነበረው በአሁኑ ጊዜ ፍርድ ቤቱ በፍርድ ባለ እዳ ላይ ሰጥቶት የነበረውን እገዳ ተነስቶ ቤቱ በወ/ሮ ገነት አደም መታገዱን አመልክተዋል ይህንን አውቀው ሀሳብ ካለዎት ለቀነ ቀጠሮ 25/04/2017 ዓ.ም በ4፡30 ሰዓት ላይ ቀርበው እንዲገልጹ ሆኖ ካልቀረቡ ግን በሌሉበት ይህ ሂደት የሚቀጥል መሆኑን የአዳማ ከተማ ከፍተኛ ፍርድ ቤት አዟል፡፡

**በአዳማ ከተማ ከፍተኛ ፍርድ ቤት የቤተሰብ እና ህጻናት ጉዳይ ችሎት**

በከሳሽ አቶ ቸርነት ከበደ እና በተከሳሽ ደረጀ ብዙወርቅ መካከል ያለው የፍትሐብሔር ክርክር ስማቸው ከላይ የተጠቀሰው ተከሳሽ በአዳማ ከተማ ከፍተኛ ፍ/ቤት መከሰሳቸውን አውቀው በ28/04/2017 በ8፡20 ቀርበው እንዲከራከሩ ያልቀረቡ ከሆነ ደግሞ ፍርድ ቤቱ በሌሉበት አከራክሮ የሚወስን መሆኑን የአዳማ ከተማ ከፍተኛ ፍርድ ቤት አዟል፡፡

**የአዳማ ከተማ ከፍተኛ ፍርድ ቤት**

የባለንብረቱ ስም በከልቻ ትራንስፖርት አ/ማህበር ሰሌዳ ቁጥር 3-14074 ኢት ከላይ የተጠቀሰው የተሽከርካሪ ባለንብረት ሊብሬ ጠፋብኝ ብለው በቀን 07/04/2017 ዓ.ም አመልክተዋል፡፡ በዚሁ መሰረት የመኪና ሊብሬውን ወድቆ ያገኘ ወይም በሌላ ምክንያት ይዤዋለሁ የሚል ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት ቀን ጀምሮ በ15 ቀን ውስጥ የፍ/ቤት ማሳገጃ ትዕዛዝ እንዲያቀርቡ እያስታወቅን በተባለው የጊዜ ገደብ ውስጥ ካላቀረቡ ለአመልካች ተለዋጭ ሊብሬ የምንሰጥ መሆኑን እናስታውቃለን፡፡

**በኦ/ክ/መ የምስራቅ ሸዋ ዞን ትራንስፖርት ኤጀንሲ**

ከሳሽ አቶ ጊርማ ከበደ ተከሳሽ ወ/ሮ ኢፍቱ ለማ ፈይሳ ተከሳሽ ወ/ሮ ኢፍቱ ለማ ፈይሳ የሚባሉት ተከሳሽ መከሰሳቸውን አውቀው በዚህ ማስታወቂያ ጥሪ ለቀጠሮው ቀን ለ24/04/2017 ዓ.ም በ5፡00 ሰዓት ቀርበው እንዲከራከሩ ካልቀረቡ በሌሉበት ክርክር እንደሚካሄድ እንዲያውቁ ሲል በሸገር ከተማ ከ/ፍ/ቤት የቡራዩ ክ/ከተማ ወረዳ ፍ/ቤት 2ኛ ቤተሰብ ችሎት አዟል፡፡

**በሸገር ከተማ ከፍተኛ ፍ/ቤት የቡራዩ ክ/ከተማ ወረዳ ፍርድ ቤት**

## ትግራይ ክልል

በአቶ ክፍሎም ገብሩ በየነ ስም የተመዘገበ የሰሌዳ ቁጥር ትግ-03-05151 የሞተር ቁጥር 5L-4879963 የሻንሲ ቁጥር LH172-0032466 ሞዴል KG-LH172V-SRPDS-G ሰሌዳ ስለጠፋቸው ምትክ እንዲሰጣቸው አመልክተዋል፡፡ በዚህም መሠረት ሰሌዳውን ወድቆ ያገኘ ወይም በሌላ ምክንያት ይዤዋለሁ የሚል ካለ በ15 ቀን ውስጥ የፍ/ቤት ማሳገጃ ይዞ እንዲቀርብ ይህ ባይሆን ግን ለአመልካች ተለዋጭ ሰሌዳ የምንሰጥ መሆኑን እናስታውቃለን፡፡

**በት/ብ/ክ/መ/ የሽረ-እ/ስላሰ ከተማ የአሽከርካሪ እና ተሽከርካሪ የብቃት ማረጋገጫ ጽ/ቤት**

## አዲስ አበባ አስተዳደር

በከሳሽ/አመልካች/ፍ/ባለመብት አፍሪካ ኢንሺራንስ እና በተከሳሽ/ተጠሪ/ባለእዳ አቶ አማን ከማል መካከል ስላለው የፍ/ብሔር ክርክር ጉዳይ ከሳሽ ፍ/ቤቱ በሰጠው ትእዛዝ ተከሳሽ በፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት የንግድና ኢንቨስትመንት ምድብ 3ኛ ባ/ኢ ችሎት እየታየ መሆኑን በዚህ ጋዜጣ ማስታወቂያ ጥሪ አውቀው መልሱን በጽሁፍ በ24/4/2017 ዓ.ም 8፡00 ሰዓት ይዘው እንዲቀርቡ ፍ/ቤቱ አዟል፡፡

**የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ንግድና ኢንቨስትመንት ምድብ ችሎት**

የባለንብረት ስም አብድልሰመድ ቃሲም ሁሴን የሰሌዳ ቁጥር አአ 02-01-B63175 የተሽከርካሪው አይነት አውቶሞቢል የሻንሲ ቁጥር SCP10-0466381 ሞዴል UA-SCP10-AHPNK-L የሞተር ቁጥር 1SZ-1242063 የሊብሬ ቁጥር 219290/412574/569905 ከላይ የተጠቀሰው የተሽከርካሪ ባለንብረት የባለቤትነት ማረጋገጫ ደብተር/ሊብሬ ጠፋብኝ ብለው በ16/4/2017 ዓ.ም አመልክተዋል፡፡ የባለቤትነት መታወቂያ ደብተሩን ወድቆ ያገኘ ወይንም በሌላ ምክንያት ይዤዋለሁ የሚል ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት ቀን ጀምሮ በ15 ቀን ውስጥ የፍ/ቤት ማሳገጃ ትዕዛዝ እንዲያቀርቡ እያስታወቅን፣ በተባለው ጊዜ ገደብ ውስጥ ካልቀረቡ ለአመልካች ተለዋጭ ሊብሬ ወይንም መታወቂያ ደብተር የምንሰጥ መሆኑን እናስታውቃለን፡፡

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የአሽከርካሪና ተሽከርካሪ ፈቃድና ቁጥጥር ባለሥልጣን የጉለሌ ቅ/ጽ/ቤት**

በከሳሽ/አመልካች /ፍ/ባለመብት፡- ህብረት ኢንሹ አ.ማ በተከሳሽ/ተጠሪ/ባለዕዳ፡- መንድህና ኢንዱስትሪ ኃ/የተ/የግ/ማ መካከል ስላለው የፍትሐብሔር ክርክር ጉዳይ ፍ/ቤቱ በሰጠው ትዕዛዝ ተከሳሽ በፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት ንግድና ኢንቨስትመንት ምድብ 1ኛ ባ/ኢ ችሎት እየታየ መሆኑን በዚህ ጋዜጣ ማስታወቂያ ጥሪ አውቀው መልሱን በጽሁፍ ለ23/04/2017ዓ.ም በ3፡30 ሰዓት በሬጅስትራር በኩል እንዲያቀርቡ እና ክስ ለመስማት ለ24/04/2017 ዓ.ም 1ኛ ባ. ኢን ችሎት እንዲያቀርቡ ፍ/ቤቱ አዟል፡፡

**የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ንግድና ኢንቨስትመንት ምድብ ችሎት**

የባለንብረት ስም አሰፋ ብርሃኑ ከበደ የሰሌዳ ቁጥር አአ 02-01-B16405 የተሽከርካሪው አይነት ደረቅ ጭነት ከ11 ኩንታል ያነሰ የሻንሲ ቁጥር MROHR29G302032239 ሞዴል KUN25L-CRMSHW የሞተር ቁጥር 2KD-5139340 የሊብሬ ቁጥር 357091 ከላይ የተጠቀሰው የተሽከርካሪ ባለንብረት የባለቤትነት ማረጋገጫ ደብተር/ሊብሬ ጠፋብኝ ብለው በ16/4/2017 ዓ.ም አመልክተዋል፡፡ የባለቤትነት መታወቂያ ደብተሩን ወድቆ ያገኘ ወይንም በሌላ ምክንያት ይዤዋለሁ የሚል ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት ቀን ጀምሮ በ15 ቀን ውስጥ የፍ/ቤት ማሳገጃ ትዕዛዝ እንዲያቀርቡ እያስታወቅን፣ በተባለው ጊዜ ገደብ ውስጥ ካልቀረቡ ለአመልካች ተለዋጭ ሊብሬ ወይንም መታወቂያ ደብተር የምንሰጥ መሆኑን እናስታውቃለን፡፡

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የአሽከርካሪና ተሽከርካሪ ፈቃድና ቁጥጥር ባለሥልጣን የንፋስ ስልክ ላፍቶ ቅ/ጽ/ቤት**

ከሳሽ ወ/ሮ አረጋሽ ተፈራ

ተከሳሽ 1. ወ/ሮ አሚና መሀመድ
2. ወ/ሮ መኪያ ሰማን
3. አቶ ፉአድ ሰማን
4. አቶ ሰይድ ሰማ

ከሳሽ ወ/ሮ አረጋሽ ተፈራ ተከሳሽ እነ አሚና መሀመድ መጥሪያ ለማድረስ ላገኛቸው አልቻልኩም ሲሉ ያመለከቱ በመሆኑ ተከሳሽ እነ አሚና መሀመድ ያሉበትን የሚያውቅ ወይም ራሳቸው ካሉ 24/04/2017 ዓ.ም ለሆነው ቀጠሮ በ4፡00 ሰዓት አ/አ/ከ/የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት አዲስ ከተማ ምድብ ችሎት እንዲቀርቡ ፍ/ቤቱ አዟል፡፡

**የአዲስ አበባ ከተማ የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት አዲስ ከተማ ምድብ ችሎት**

በከሳሽ/አመልካች፡- ወ/ሮ መሰረት መኮንን እና ተከሳሽ/ተጠሪ፡- አቶ ያለው አለምነው ታደሰ መካከል በፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት አቃቂ ቃሊቲ ምድብ 2ኛ ቤተሰብ ችሎት ባለው ክርክር ጉዳይ ተከሳሽ/ ተጠሪ በ30/04/2017ዓ.ም በ3፡30 ሰዓት ስላለው ቀጠሮ በችሎት እንዲቀርቡ ፍ/ቤቱ አዟል፡፡

**የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት**

የባለንብረት ስም መብራቱ አባተ እና ጓደኞቻቸው ዳሽን ቢራ ጅምላ ንግድ ሕብረት ሽርክና ማህበር የሰሌዳ ቁጥር አአ 03-01-A87715 የተሽከርካሪው አይነት ደረቅ ጭነት ከ11 ኩንታል ያነሰ የሻንሲ ቁጥር MAT374415K-SL00694 ሞዴል 207D1/31 የሞተር ቁጥር 497SP27PRY664126 የሊብሬ ቁጥር 178126 ከላይ የተጠቀሰው የተሽከርካሪ ባለንብረት የባለቤትነት ማረጋገጫ ደብተር ሊብሬ ጠፋብኝ ብለው በ16/4/2017 ዓ.ም አመልክተዋል፡፡ የባለቤትነት መታወቂያ ደብተሩን ወድቆ ያገኘ ወይንም በሌላ ምክንያት ይዤዋለሁ የሚል ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት ቀን ጀምሮ በ15 ቀን ውስጥ የፍ/ቤት ማሳገጃ ትዕዛዝ እንዲያቀርቡ እያስታወቅን፣ በተባለው ጊዜ ገደብ ውስጥ ካልቀረቡ ለአመልካች ተለዋጭ ሊብሬ ወይንም መታወቂያ ደብተር የምንሰጥ መሆኑን እናስታውቃለን፡፡

**በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የአሽከርካሪና ተሽከርካሪ ፈቃድና ቁጥጥር ባለሥልጣን የካ ቅ/ጽ/ቤት**

# ስፖርት





# ከእግር ኳስ አስቂኝ አጋጣሚዎች...

**ቦጋለ አበበ**

እግር ኳስ ቲያትር ነው፣ ለዚያም ነው የዓለም ሕዝብ ተወዳጁ መዝናኛ የሆነው። እግር ኳስ ቲያትር ነው የሚባለው በምክንያት ነው። ያልተጠበቁና ፈፅሞ ይሆናሉ ያልተባሉ ተዓምራት የሚፈፀሙበት መድረክ ነውና። እግር ኳስ በጥሩ ደራሲ የተፃፈ ቲያትር ተደርጎ የሚቆጠረው አዝናኝ፣ አስቂኝ፣ አስከፊና አስቆጪ የማይረሱ ታሪኮችን በዘጠና ደቂቃ ፍልሚያ ማስኮምኮም በመቻሉም ነው ቀዳሚው ተመራጭ ስፖርት የሆነው።

ፊፋ ተጫዋቾች ጎል ካስቆጠሩ በኋላ ማልያቸውን አውልቀው ደስታቸውን እንዳይገልፁ ከ2004 ጀምሮ መከልከሉ ይታወቃል። ይህን የፈፀሙ ተጫዋቾች ከዚያን ጊዜ ጀምሮ ቢጫ ካርድ ሲመለከቱ ኖረዋል። ፊፋ ይህን ሕግ ሲያወጣ ማልያ አውልቆ ደስታን መግለፅ የስፖርት ሥነምግባር አይደለም ብሎ በማሰብ ሲሆን በዋናነት ተጫዋቾች ማልያቸውን አውልቀው ደስታቸውን ሲገልፁ በጨዋታ የሚባክን ሰዓትን ለመቀነስ በማሰብ ነው።

በደስታ የሰከሩና ስሜታቸውን ለመግለፅ የተቸገሩ በርካታ ተጫዋቾች ይህን ሕግ ጥሰው ማልያ አውልቀው ደስታቸውን በመግለፅ የቢጫ ካርድ ሰለባ ሲሆኑ ማየት የተለመደ ነው፡፡ እግር ኳስ ፈገግ ካለባቸው አጋጣሚዎች አንዱ የሆነው ክስተትም የተፈጠረው ከዚሁ ሕግ ጋር በተያያዘ



ነው።

ጊዜው ሩቅ አይደለም እኤአ 2013 ነው፣ ተጋጣሚዎቹ የጣሊያኑ ክለብ ዩቬንቱስና ፔስካራ ናቸው። አሮጊቶቹ ሴሪ ኤውን በመምራት የስኩዴቶው ሻምፒዮን ለመሆን ይህ ጨዋታ የመጨረሻቸው ነው። ተጋጣሚያቸው ፔስካራ በበኩሉ ከሊጉ ላለመውረድ ቱሪን ላይ የመጨረሻውን ትግል የሚያደርግበት ወሳኝ ጨዋታ ነው። ጉሴፔ ሪዞ በሠራው ጥፋት 72ኛ ደቂቃ ላይ በቀይ ካርድ ሲወገድ ዩቬ ፍፁም ቅጣት ምት አግኝቶ አማካኙ ሚርኮ ቩሲኒች አስቆጥሮ መምራት ቻለ። ይህ ሞንቴኔግሯዊ ተጫዋች ፍፁም ቅጣት ምቱን አስቆጥሮ ማልያውን አውልቆ ደስታውን በመግለፁ ቢጫ ካርድ ተመለከተ። ብዙ ሳይቆይም ቩሲኒች ለክለቡም ለራሱም ሁለተኛ ግብ ከመረብ ማሳረፍ ቻለ። አሁን ግን ከደቂቃዎች በፊት እንዳደረገው ማልያውን አውልቆ ደስታውን ለመግለፅ አልቻለም። ምክንያቱም በሁለት ቢጫ ካርድ ከሜዳ ተወግዶ ቡድኑን በቀሪዎቹ ደቂቃዎች ዋጋ ሊያስከፍል ነው።

ልብስ እያውለበለበ ካልሆነ በቀር ደስታውን የገለፀ የማይመስለው አማካኝ ግን ዳግም ቢጫ ካርድ የማይመለከትበትን አንድ መላ ወዲያው ዘየደ። ከላይ ከለበሰው ማልያ (ቲሸርት) ይልቅ ቁምጣውን አውልቆ በእጁ በማወዛወዝ ሜዳውን በሩጫ እያካለለ ደስታውን ገለፀ።

የጨዋታው ዳኛ ማልያውን አውልቆ ደስታውን ለገለፀ ተጫዋች ቢጫ ካርዳቸውን መምዘዝ የለመዱትና ቀላሉ ሥራቸው ነው። ቁምጣውን ላወለቀ ተጫዋች ቢጫ ካርድ መምዘዝ ግን ሕጉ ላይ አልተቀመጠምና ያላቸው አማራጭ እንደማንኛውም ተመልካች በድርጊቱ ፈገግ ማለት ነበር። የተጫዋቹ ድርጊት ብዙዎችን ዘናና ፈገግ ከማድረጉ ባሻገር በዚያች ግብ ባስቆጠረባት ቅፅበት የሕግ ክፍተቱን በፍጥነት ማሰቡ አስገርሟቸዋል። የወቅቱ የዩቬ አሠልጣኝ አንቶኒዮ ኮንቴ ግን “ይህ እብድ ሌላ ጣጣ ሳያመጣብኝ” ያሉ ይመስላሉ፣ የተጫዋቹን ድርጊት እንደተመለከቱ ወዲያው ቀይረው ከሜዳ አስወጥተውታል። የተጫዋቹ ድርጊት ሊያስቀጣ ይገባል አይገባም በሚል በወቅቱ ብዙዎችን አከራክሯል፡፡ ያም ሆነ ያ አጋጣሚና የተጫዋቹ ድርጊት ግን ሁሌም ፈገግ ከሚያደርጉ የእግር ኳሱ ታሪኮች አንዱ ሆኖ ይታወሳል፡፡


## INVITATION To BID

No.Maya/Muni/GR-01/2024/25 and Maya/Muni/GR-02/2024/25

Maya City Finance office invites registered contractors of Category GC-2 and RC-1 and above with their Professional and above trade license open tenders for road work contractors in 2017. Therefore, we are asking bidders who meet the below criteria to compete.

| No | The Lines | Km | Bid ref .no |
|---|---|---|---|
| 1 | Aweday-Gobe Chala,-H/Maya<br>Aweday-Nagaya-Haro Adi<br>Aweday-Fandisha And Dengego-H/Adi | 71.55 | Maya/Muni/GR-01/2024/25 |
| 2 | Bate-Tinike-Finkile-Ganda Terre and Bate-Damota, Damota-Ifa Bate-Ganda Mude | 56.74 | Maya/Muni/GR-02/2024/25 |

To All Contractors of Category GC-2 And RC-1 and Above With Renewed License Valid For The Year 2017 E.C

1. Maya City Finance Office invites registered contractors of category GC-2 and RC-1 and above with their professional and above trade license valid for the year 2017 EC. Registered for VAT and having tax clearance certificate and any relevant professiona1 practice certificate and its trading license, submit sealed bids for providing the necessary labor, materials and equipment for the construction of the following Maya City Haramaya Lake Side Recreation Center.
2. Evidence of /being/registered at Ethiopia Public Procurement and Property Disposal Agency (PPPDA) Supplier List.
3. Bidding will be conducted in accordance with the open national tendering procedures contained in the Public Proclamation of The Federal Governments of Ethiopia and is open to all eligible bidders.
4. Interested eligible bidders may obtain further information from Maya City Finance Office.
5. The bidders shall submit one mother envelop wax sealed bidding documents this shall be produced in different wax sealed envelopes and shall be signed stamped and clearly labeled as original and Copy 1 and Copy -2 financial and technical document failure to do so would entail rejection of the bid.
6. The financial document shall be submitted to Maya City Administration Finance Office before deadline for bid submission. Late bid shall be rejected automatically.
7. A complete set of bidding documents in English may be purchased by interested bidders at the address below and up on payment of a non-refundable fee of Ethiopian birr 2000 (two thousand birr) at working hours. The method of the payment will be on Sinke bank.
8. The bid must be delivered to the address below on/before dead line and must be accompanied by a bid security in the form of CPO or in cash Ethiopian 500,000 (five hundred thousand birr) to the address of Maya City Finance. Late Bids Shall Be Rejected.
9. The deadline of bid submission shall be at 2:00 PM afternoon on the 21st working day starting from the 1st announcement made on newspaper. The bid will be opened on the same date of submission at 2:30 PM afternoon in the presence of the bidders or their authorized representatives who choose to attend at the address below.
10. The Maya City Administration Finance office reserves the right to reject any or all bids and to annul the bidding process and reject all bids at any time prior to contract award without thereby any liability of the bidders.

**Telephone 0985846796/0942241606**

**Oromia Regional State Maya City Administration Finance Office**



## የጨረታ ማስታወቂያ
## የጨረታ ቁ. ኢአጽ/ግንአዳ/005/2017

የኢትዮጵያ መድን ድርጅት የተለያዩ ዓይነት የወረቀት ህትመቶችን በጨረታ አወዳድሮ ማሳተም ይፈልጋል::

ስለሆነም ከዚህ በታች የተገለጹትን መስፈርቶች የሚያሟሉ አቅራቢዎች በጨረታው እንዲሳተፉ ተጋብዘዋል፡፡

1- በጨረታው የሚወዳደሩ ተጫራቾች በዘርፉ ሕጋዊ የታደሰ የንግድ ሥራ ፈቃድ ያላቸውና በመንግስት ግዥና ንብረት አስተዳደር ኤጀንሲ የአቅራቢዎች ዝርዝር ውስጥ ለመመዝገባቸው ከድረ-ገጹ (Website) አትመው ከጨረታ ሰነዱ ጋር ማያያዝ ይኖርባቸዋል፡፡

2- ተጫራቾች በተጨማሪ እሴት ታክስ /VAT/ ከፋይነት የተመዘገቡ፣ የግብር መለያ ሰርተፊኬት ያላቸው መሆኑን የሚያረጋግጥ የምስክር ወረቀት እና ታክስ ክሊራንስ ማቅረብ አለባቸው፡፡

3- ተጫራቾች የማይመለስ ብር 500 (አምስት መቶ ብር) በመክፈል የጨረታ ሰነዱን ይህ ማስታወቂያ በጋዜጣ ከወጣበት ቀን ጀምሮ ለገሐር በሚገኘው የድርጅቱ ዋና መስሪያ ቤት 1ኛ ፎቅ ቢሮ ቁጥር 108 ድረስ በመቅረብ መግዛት ይችላሉ፡፡

4- ተጫራቾች ብር 350,000.00 (ሦስት መቶ ሐምሳ ሺ) የጨረታ ማስከበሪያ በባንክ የክፍያ ማዘዣ (CPO) ወይም ለዘጠና ቀናት የሚቆይ ቅድመ ሁኔታ ያላስቀመጠ የባንክ ዋስትና ከጨረታ ሰነዱ ጋር አያይዘው ማቅረብ አለባቸው::

5- ተጫራቾች የመወዳደሪያ ሠነዳቸውን በታሸገ ኤንቨሎፕ በማድረግ ለገሐር በሚገኘው የድርጅቱ ዋና መስሪያ ቤት 1ኛ ፎቅ ቢሮ ቁጥር 108 በተዘጋጀው ሳጥን ውስጥ ጥር 09 ቀን 2017 ዓ.ም. እስከ ቀኑ 8፡00 ሰዓት ድረስ ማስገባት ይኖርባቸዋል፡፡ ጨረታው ተጫራቾች ወይም ሕጋዊ ወኪሎቻቸው በተገኙበት በእለቱ ማለትም ጥር 09 ቀን 2017 ዓ.ም. በኢንተርፕራይዙ አገልግሎት ጽ/ቤት የስብሰባ አዳራሽ በ8፡30 ይከፈታል፡፡

6- መሥሪያ ቤቱ የተሻለ አማራጭ ካገኘ ጨረታውን በሙሉም ሆነ በከፊል የመሰረዝ መብቱ የተጠበቀ ነው::

7- ለተጨማሪ ማብራሪያ በስልክ ቁጥር 011-5512400 የውስጥ መስመር 217/262 ወይም በቀጥታ 011-5504931 መጠየቅ ይቻላል፡፡

## የኢትዮጵያ መድን ድርጅት